**Ethiopian Evangelical Baptist Church**
2822 S. Jupiter Road
Garland, TX 75041
**Telephone:** 214-703-0100
**Fax:** 214-703-0161

# ኦሪት

# ዘፍጥረት

ክፍል አንድ ምዕራፍ ፩ - ፵፫

Part one Chapter 1 - 43




በኢትዮጵያዊያን ወንጌላዊት ባፕቲስት
ቤተ ክርስቲያን
ለቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት
ሕብረቶች የተዘጋጀ

## ጥናት አንድ

## እግዚአብሔርን በፍጥረት ውስጥ ማየት

**የምንባብ ክፍል ዘፍ 1፡ 1-25**

**ዓላማ፦** እግዚአብሔር ብቸኛ ፈጣሪና የፍጥረት ባለቤት እርሱ ብቻ እንደሆነ አውቀን እንድናከብረው እንድናመሰግነው።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ለአንድ ሰው ስለ እግዚአብሔርን ገልጾ ማድረግ ቢያስፈልግህ እንዴት ብለህ ነው በራስህ አባባል እግዚአብሔርን የምትገልጸው?

2. በቁጥር 1 ላይ "እግዚአብሔርን ምድርንና ሰማይን ፈጠረ" ብሎ ይጀምራል።

    - ስለ እግዚአብሔርን ማንነት ማብራሪያ ክፍሉ አለመስጠቱ ለምን ይመስልሀል?
    - ከዮሐንስ 1፡1-3 ጋር ይህ ሃሳብ እንዴት ይገናኛል?
    - በዚህ ቁጥር ላይ የተጠቀሰው እግዚአብሔር "ስም" በዕብራይስጡ ምን ይባላል?

3. "ምድርም ቅርጽ የለሽ ነበረች" እና "ጨለማምም ምድር ሸፍኖ ነበር" ብሎ ይነግረናል

    - በመሠረቱ እግዚአብሔር ቅርጽ የሌለው ነገር ይፈጥራል ብለህ ታስባለህ?
    - ወይንስ በቁ.1 እና ቁ.2 መካከል የተፈጠረ ሌላ ክስተት የሚኖር ይመስልሀል?

4. በቁ. 1 መንፈስ ቅዱስ "ይረብብ ነበር" ብሎ ሲል ምን ማለቱ ነው?
    - ከዘዳ. 32፡11፣ እና ኢሳ. 31፡5 የሚገናኘው እንዴት ነው?

5. ከቁ.3-5 ድረስ እግዚአብሔር ያለውና፣ የተከናወነውን ነገር በዝርዝር ተወያዩበት?

    - ጳውሎስ (በ2ቆሮ. 4፡6) ከጻፈው ሃሳብ ጋር የሚገናኘው እንዴት ነው?

6. ከቁ.6-8 እግዚአብሔር በሁለተኛው ቀን የፈጠረው ምንድነው?

    - እንዴትስ አድርጎ ነው የፈጠርው?
    - ይህስ ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት ምን ያስተምርሃል?

7. ከቁ.9-10 እግዚአብሔር ያደረገውና፣ የጠራው ምንድነው?

    - የብስንና ባሕርን ከአሁን በኋላ ስትመለከት ምን እንድታስተውል ያደርገሃል?

8. ከቁ.11-12 እግዚአብሔር ትእዛዝ የሰጠው ለማነው?

- ምድሪቱ ለተሰጣት ትእዛዝ የሰጠቸው ምላሽ የተገለጸው እንዴት ነው?

9. ፍጥረት እግዚአብሔርን መስማት ብቻ ሳይሆን የታዘዘውን ነገር ወዲያ ይፈጽማል፣

- እግዚአብሔር ሰውን ሲያዘው ይህ "የመታዘዝ" ባህርይ ይታይበታል?
- ሰው እግዚአብሔርን የማይሰማውና የማይታዘዘውስ ለምን ይመስልሃል?

10. ከቁ.14-18 እግዚአብሔር የፈጠራቸው ብርሃናቶች ስማቸው እነ ማን ነው?

- እነዚህ ብርሃናትስ የሚሰጡት አገልግሎት ምንድነው ነው?

11. ከቁ.18-25 እግዚአብሔር የፈጠራቸው ፍጥረቶች በስንት ይከፈላሉ?

- በባህርና በየብስ የተፈጠሩትን ፍጥረቶች እነማን እንደሆኑ በዝርዝር ተወያዩበት፣

12. በመደጋገም እግዚአብሔር "ይሁን አለ ሆነም" የሚለውን አባባል በማጤን ስለ እግዚአብሔርን የምትረዳው እውነት ምንድነው?

13. በመደጋገም "መልካም ነው" ከሚለው አባባል የምትማረው መንፈሳዊ ቁም ነገር ምንድነው ?

14. ሰው ፍጥረትን በማስተዋል ከተመለከተ ስለ እግዚብሔር የሚረዳው እውነት ምንድነው? ሮሜ 1፡19-20 ያለውን ሃሳብ በማነጻጸር ተመልከት

## ጥናት ሁለት

## የሰው መፈጠር

**የምንባብ ክፍል ዘፍ 1፡ 26-31**

**ዓላማ፦ እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው በምሣሌው እንደሆነና ሰውም ከእግዚአብሔር በምድር ላይ የተሰጠው ሥልጣንና እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ለመገንዘብ።**

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ.26-27 መሠረት ሰውን በአፈጣጠሩ ከሌሎቹ ፍጥረታት የተለየ የሚያደርገው እንዴት ነው?

2. እግዚአብሔር "ሰውን በመልካችን እንደ ምሣሌያችን እንፍጠር" ሲል ምን ማለቱ ነው?

   - የእግዚአብሔር መለኮታዊ ኃይልና መለኮታዊ ባህርይ ልዩነታቸው እንዴት ነው?

   - በ2 ጴጥ.1፡2-3 መሠረት የትኛውን የእግዚአብሔርን ባህርይ እንድንመስል ነው የተጠራነው?

3. በቁ.27 መሠረት እግዚአብሔር ሌሎችን ከፈጠረ በኋላ ሰውን የፈጠረው ለምን ይመስልሃል?

   - ለአዳምና ሔዋን እግዚአብሔር ሥልጣን የሰጣቸው በማን ላይ ነው?

   - አዳምና ሔዋን በእነዚህ ፍጥረታት የተሰጣቸው ሥልጣን እንስከምን ድረስ ነው?

4. በቁ.28 እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን የባረካቸው ምን ብሎ ነው?

5. በቁ.29 እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን የሰጣቸው የምግብ ዓይነት ምንድነው?

   - ሰው ሥጋ መብላት የጀመረው መቼ ነው? (ዘፍ.9፡1-6)

6. በቁ.30 እግዚአብሔር ለሌሎቹ ፍጥረታት የሰጠው የምግብ ዓይነትስ ምንድነው?

7. በፍጥረት ሥራ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ያስተዋልከውንና የተረዳኸውን እውነት አጠር በማድረግ አካፍል?

8. የሰው አፈጣጠር ከፍጥረት ሁሉ የከበረ እንደሆነ መገንዘብህ፣ ስለ ሌሎች ወይም ስለአንተ ያለህን አመለካከት በምን መልኩ ሊቀይረው ይችላል?

9. እግዚአብሔር አንተን በአምሣሉ መፍጠሩ ካንተ ስለሚጠብቀው ነገር ምን እንደሆነ ይህ ክፍል ያስተምርሃል?

ጥናት ሦስት

## ጥናት ሦስት

## የሰው ኃላፊነትና አደራ

**የምንባብ ክፍል ዘፍ 2፡ 1-17**

**ዓላማ፦** እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው፣ ሰው ለእግዚአብሔር ክብር እንዲኖርና፣ የተሰጠውንም የአምላክ አደራ በሚገባ እስከ መጨረሻው ድረስ በታማኝነት መፈጸም እንዴት እንዳለበት ለመረዳት ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቁ1-2 እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ያደረገውና የባረከው ምንን ነው?
2. "ከስራው ሁሉ አረፈ" ብሎ ሲል ምን ማለት ነው?
   - በዚህ ክፍል መሠረት ሰንበት የምን ምልክት እንደሆነ ትገነዘባለህ?
   - ሰንበትን ሰው የማክበሩ ውጤት ምን ሊሆን ይገባል ብለህ ታስባለህ?
3. ከቁ.4-6 በምድር ላይ አልነበረም ብሎ የሚነግረን ስለ ምንድን ነው?
   - በምድር ላይ የሜዳ ቡቃያና፣ ተክል ያልኖረበት ሁለት ምክንያት ምንድነው?
   - በምድር ላይ ዝናብ የዘነበው ታዲያ መቼ ነው ብለህ ትገምታለህ?
4. ቁ.7 እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው በምን መንገድ ነው?
   - በመፈጠር ሰውን ከሌሎች ፍጥረታት ልዩ የሚያደርገው ምንድነው?
5. በቁ.8 እግዚአብሔር ሰውን በገነት ያሰቀመጠበት ሁለት ምክንያት ምንድን ነው?
   - ከቁጥር 15 ጋር በማገናዘብ ስለ ስራ የምትማረው እውነት ምን ይመስላል?
6. በቁ.9 ላይ የተጠቀሱት ዛፎች ዓይነታቸውና ሲበሉ የሚያመጡት ውጤት ምንድነው?
   - "የሕይወት ዛፍና፣ የእውቀት ዛፍ" ብሎ ሲል ምን ማለቱ ነው?
   - ሁለቱን ዛፎች በራዕይ 2፡ 7 እና 22፡ 14 ጋር የሚያገናኛቸው ሃሳብ ምንድነው?

7. ከቁ.10-14 ከኤደን ገነት የሚፈሱትን የወንዞቹን ስም ስራና ግለጽ?

- ከራዕይ 22፡ 1-2 ይህ ሃሳብ የሚገናኘው እንዴት ነው?

8. ከቁ.15-17 እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠው ትእዛዝ ምንድነው?

- እግዚአብሔር "መልካምና ክፉ" የምታበቅለውን ዛፍ በኤደን ለምን አስቀመጣት?
- ሰው ሁልጊዜ የተከለከለ ነገር የሚያምረው ለምንድነው? ብዙ የተፈቀደለት እያለው?

9. የሰው አፈጣጠርና ለሰው የተሰጠውን ክብር ልዩ የሚያደርገው ከክፍሉ የተማርከው ምንድነው?

- ይህስ ስለ ተሰጠህ ሕይወት ምን ጥንቃቄ እንድታደርግ ያስገነዝብሃል?

10. እግዚአብሔር ሰውን ኤደን ገነትን መኖሪያ አድርጎ ሲሰጠው ከምን ጋር ነው የሰጠው?

- ይህስ ስለ ሃላፊነትና ስለ መታዘዝ ምን ያስተምርሃል?

11. በኤደን ገነት ውስጥ የምናያቸው ነገሮች፣ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ውስጥ ማየትህ ምን እንድታስተውልና፣ እንዴት ጌታን እንድታመሰግን ያደርግሃል?

## ጥናት አራት
## ሰውና አስፈላጊው እውነት

**የምንባብ ክፍል ዘፍ** 2፡ 18-25

**ዓላማ፦** እግዚአብሔር የሰውን ጉደለት ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ የጎደለበትንም ሊያሟላ የሚችል እርሱ ብቻ እንደሆነ አውቀን በትዕግስትና በእምነት እግዚአብሔርን እንዴት መጠበቅ እንደሚገባን ለመረዳት።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ 18 ላይ እግዚአብሔር የተናገረውና ሊያደርግ ያሰበው ነገር ምንድነው?
2. እግዚአብሔር "ሰው ብቻውን መሆኑ መልካም አይደለም" ሲል ምን ማለቱ ነው?
   - የዚህስ ጥያቄ (ሃሳብ) ከም.1፡ 28 የሚገናኘው በምን መልኩ ነው?
3. "የሚስማማውን እረዳት አበጅለታለሁ" ሲል ይህ ስለ እግዚአብሔር ምን ያስተምረናል?
4. ከቁ.19-20 እግዚአብሔር፣ ወደ አዳም ያመጣውና፣ ያመጣበት ምክንያት ምንድነው?
5. እግዚአብሔር እራሱ ስም ማውጣት ሲችል አዳም ስም እንዲያወጣ ያደረገበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
   - አሁንም የዚህ ጥያቄ (ሃሳብ) ከም.1፡ 28 የሚገናኘው በምን መልኩ ነው?
6. ቁ.21-22 ላይ እግዚአብሔር በአዳም ሕይወት ውስጥ ያደረጋቸው አራት ነገሮች ምንድናቸው?
7. እግዚአብሔር ሔዋንን ከአዳም አጥንት የፈጠረበት ዋና ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
   - የዚህስ ጥያቄ (ሃሳብ) ከም.1፡ 23 የሚገናኘው በምን መልኩ ነው?
8. በቁ.24 መሠረት "ሰው እናትና አባቱን ይተዋል ከሚስቱ ጋርም ይጣበቃል" ሲል ምን ማለቱ ነው?
9. አዳምና ሔዋን የማይተፋፈሩበት ምክንያት ለምንድነው?
   - ይህስ ካሁን ከምንኖርበት ሕይወት ጋር የሚዛመደው በምን መልኩ ነው?
   - የዚህስ ጥያቄ (ሃሳብ) ከም.3፡ 7 ጋር የሚገናኘውስ በምን መልኩ ነው?
10. ከዚህ የጥናት ጊዜ እግዚአብሔር ለአዳም ያሳየው ቸርነትና ፍቅር የተገነዘብከው ምንድነው?

11. አዳም ለሚያስፈልገው ነገር እግዚአብሔር እራሱ አስቦ ማዘጋጀቱና ማምጣቱ በእግዚአብሔር ላይ ስለመታመን ይህ ክፍል ምን ያስተምርሃል?

12. ከዚህ ክፍል ጥናት ስለ እግዚአብሔር የተረዳህው እውነት በኑሮዬ ላይ የሚያመጣው ለውጥ አለ ብለህ የምትገምተውን ሃሳብ ካለ አጠር አድርገህ አካፍል?

## ጥናት አምስት

## ከክፉው ፈተና መሸሽ

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 3፡ 1-7

ዓላማ፦ እግዚአብሔር የሰጠንን ትእዛዝት መፈጸም እንዳንችል የማይተኛ ባላጋራ እንዳለንና፣ በመንገዳችንም የሚያመጣውን የተለያዩ ፈተናዎች ተረድተን፣ እንዴት በአሸናፊነት መኖር እንደምንችል ለመገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ.1 ላይ ስለ እባብ ባህርይ የተገለጸው እንዴት ነው?
2. በቁ.1 እና በራዕይ 12፡7-9 የተጠቀሰው እባብ ግንኙነታቸው ምን ይመስልሃል?
3. በቁ.1 ላይ እባቡ ለሔዋን ያቀረበው ጥያቄ ምንድነው?
   - እባቡ ይህን ጥያቄ የጠየቀው ለምን ይመስልሃል?
   - ይህ ጥያቄ፣ በሰው ልጆች ሕይወት ታሪክ ውስጥ ያመጣው ለውጥ ምን ይመስልሃል?
4. ከቁ.2-3 ሔዋን ከእባቡ ለቀረበላት ጥያቄ የሰጠችው ምላሽ እንዴት ነው?
   - ከምዕራፍ 2፡16-18 ትእዛዝ ጋራ ሲተያይ፣ የተቀነሰ ወይም የተጨመረ ሀሳብ አለ?
   - ትንሽ መጨመር ወይም መቀነስ የሚያስከትለው አደጋ ምን ይመስልሀል?
5. ከቁ.4-5 ሠይጣን ለሔዋን የመለሰላት በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው?
   - “መሞት እንኳን አትሞቱም” ይህ አባባሉ ጥቂት እውነትነት አለው? ወዲያው ሞቱ?
   - “አይናችሁ እንደሚከፈት” ይህስ አባባል ጥቂት እውነትነት አለው? ቁ.“7” ተመልከት
   - “መልካምና ክፉውን በማወቅ” ይህስ አባባሉ? ቁ.22 ይመልከቱ
6. ሠይጣን እውነት፣ መቆርቆር እና ሀዘኔታ ባለው መንገድ ሔዋንን የፈተናት ለምን ይመስልሃል?
7. ሠይጣን በእኛም ሆነ በሌሎች በእንዲህ ዓይነት ዘዴ ሊመጣ ይችላል? ዘዴዎቹን ግለጽ?
8. በቁ.6 መሠረት ፍሬው ለሔዋን እንዴት ሆኖ ነው የታያት?
   - ሔዋን ድሮ የምታየውና የምታውቀው ፍሬ ነበር፣ ድንገት አሁን አዲስ የሆነባት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
9. የቁ.6 ሃሳብ ከ1ዮሐ.2፡15-16 የሚመሳሰልበት መንገድ እንዴት ነው?

- ይህስ እውነት በአሁን ጊዜ ለእኛ የሚያስተምረን እንዴት ነው?

10. በምዕ.2፡16-17 ስለ ፍሬው እግዚአብሔር ትእዛዝ የሰጠው ለማን ነበር?

    - ትእዛዙን የተቀበለ አዳም ከሆነ፣ ሔዋን የሰጠችውን ፍሬ እንዴት ሊበላ ቻለ?

11. የአዳምና የሔዋን አይን የተከፈተው መቼ ነው?

    - ሔዋን ፍሬውን የበላች ጊዜ አይኗ ለምን ወዲያው አልተከፈተም?
    - ስለ እግዚአብሔር አሰራር ይህ እውነት ምን ያስተምረናል?
    - የአይናቸው መከፈት ውጤቱስ ምን ሆነ?
    - ይህስ ስለ ኃጢአት ክፉነት ምን ያስገነዝበናል?
    - እራቁትነታቸውን "በቅጠል ሸፈኑ" በአሁን ጊዜ ሰው እራቁትነቱን የሚሸፍነው በምንድነው?

12. በዚህ ጥናት መሠረት ለሔዋን መውደቅ የመጀመሪያ ምክንያት የሆነው ምንድነው?
13. ሰይጣን በአሁኑ ጊዜ ሰውን ሊያስት ወይም ሊፈትን የሚችለው እንዴት ነው?
14. ሠይጣን በቀላሉ የሰውን ልብና ሀሳብ እንደሚሰርቅ ስትመለከት ፣በዚህ
    ወጥመድ እንዳትያዝ በየዕለቱ ምን ማድረግ እንደሚገባህ ይህ ክፍል ያስተምርሃል?

## ጥናት ስድስት

## ለእግዚአብሔር ቃል መገዛት

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 3፡ 8-24

ዓላማ፦ እግዚአብሔር የሰጠንን ትእዛዝት አለመፈጸም በእኛም ሆነ በሌሎች ላይ ሊያመጣ  የሚያስችለውን ጉዳት እንዴት እንደሆነ ለመገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ.8 ላይ አዳምና ሔዋን የተሸሸጉት ለምንድነው?
   - ሰውን የእግዚአብሔር መገኘት እንዲሸሽ የሚያደርገው ለምን ይመስልሃል?

2. በቁ.9 ላይ እግዚአብሔር አዳምን እያወቀ "የት ነህ" ያለው ለምን ይመስልሃል?

3. በቁ.10 አዳም ለእግዚአብሔር የመለሰው ሦስት ሃሳቦች ምንድናቸው?

4. በቁ.11 እግዚአብሔር አዳምን የጠየቀው ሁለት ጥያቄዎች ምንድናቸው?
   - አሁንም እግዚአብሔር መልሱን እያወቀ አዳምን መልሶ ለምን ጠየቀው?
   - ሌሎች ሰዎች ስህተት ሰርተው ስታገኝ ብዙ ጊዜ ማድረግ የሚቀናህ ምንድነው?

5. ከቁ.12-13 አዳምና ሔዋን ስለ ፈጸሙት በደል ምላሻቸው እንዴት ነበር?
   - ይህስ ስለ ሰው ባህርይ የሚያስተምረን እውነት እንዴት ነው?
   - ስለ ተፈጸመው በደል እግዚአብሔርስ ከእኛ የሚጠብቀው ምንድን ነው?

6. ከቁ14-15 እግዚአብሔር በእባቡ ላይ ያስተላለፈው ፍርድ በስንት ይከፈላል?
   - ይህ ፍረድ የተላለፈው በእባብ ላይ ነው ወይስ በሰይጣን?
   - በቁ.15 ላይ "በዘርህና በዘሯ መካከል" ሲል፣ ስለ የትኛው ዘር ነው?
   - "እርሱ እራስህን፣ አንተም ተረከዙን ትቀጠቅጣለህ" ብሎ ሲል ምን ማለቱ ነው?

7. በቁ.16 ላይ በሴቲቱ ላይ የተላለፉት ሁለቱ የፍርድ ዓይነቶች ምንድን ናቸው?
   - "ፍላጎትሽም ወደ ባልሽ፣ እርሱም የበላይሽ" ይሆናል ብሎ ሲል ምን ማለቱ ነው?

- ከዚህስ በፊት አዳምና ሔዋን የነበራቸው የሥልጣን ተዋረድ እንዴት ነበር?
- የሥልጣን ተዋረዱ እንዲከሰት ያደረገው የሔዋን ኃጢአት ነው ማለት ነው?

8. ከቁ14-19 እግዚአብሔር በአዳም ላይ ያስተላለፈው ፍርድ በስንት ይከፈላል?

- አዳም ይህ ከፍተኛ ፍርድ የደረሰበት ማንን በመስማቱ ነው? “17”
- እኛስ አንዳንዴ ከእግዚአብሔር ይልቅ የቅርብ ሰዎችን የምንሰማበት ጊዜ ይኖራል? ለምን?

8. ከቁ.20-21 የተከናወኑት ነገሮች ምንድናቸው?

- የሔዋን የመጀመሪያ ስሟ ማነው? ”2፡23”
- የሁለቱስ ስም ትርጉም ምንድነው?

10. እግዚአብሔር ባለበሳቸውና እነርሱ በለበሱት ልብስ (2፡7) ያለው ልዩነት እንዴት ነው?

- ይህስ በአሁኑ ጊዜ የሚያስተምረን ምሣሌያዊ እውነት እንዴት ነው?

11. ከቁ.22-24 የኪሩቤል አስፈላጊነት ለምንድነው?

- ይህስ ስለ እግዚአብሔር ምሕረት ምን ያስተምርሃል?

12. እግዚአብሔርን አለመታዘዝ የሚያመጣው ጠንቅ ይህ ጥናት ምን እንደሆነ ያስተምርሃል?

13. ምንም ነገር ቢያስከፍልህ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ከምን መራቅ ያስፈልግሃል?

14. አንተ ወይም ሌሎች በበደል ውስጥ ብትገኙ በቅድሚያ ሊወሰድ የሚገባው እርምጃ ምን ይመስልሃል?

15. ስለ እግዚአብሔር ምሕረትስ ይህ ጥናት የሚያስተምርህ እንዴት

## ጥናት ሰባት

## ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 4፡ 1-16

ዓላማ፦ ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ማናቸውም መሥዋዕት ሁሉ በእምነትና እርሱ በሚወደው መንገድ ብቻ እንደሆነ መገንዘብ እንድንችል።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቁ.1-2 ለአዳምና ለሔዋን የተወለዱት ልጆች እነማን ናቸው? የስማቸውስ ትርጉም?
2. ቁ.2 አቤል እና ቃየል የተሰማሩበት የስራ መስክ የተገለጸው እንዴት ነው?
3. ከቁ.2-4 ወንድማማቾቹ ለእግዚአብሔር ያቀረቡት መሥዋዕት ምንድነው?
4. እግዚአብሔር የቀረበለትን መሥዋዕት የተቀበለው እንዴት ነበር?
5. እግዚአብሔር የቃየልን መሥዋዕት ያልተቀበለው ለምንድነው?
    - ይህ ሃሳብ፣ ከዕብ. 11፡4 እና ከ1ዮሐ. 3፡12 ጋር እንዴት ይገናኛል?
    - እግዚአብሔር በአሁኑ ጊዜ የማይቀበለው መሥዋዕት ምን ይመስልሃል ?
6. ከቁ.5-6 እግዚአብሔር ቃየንን ሊጠይቀው ያስፈለገው ዋነኛው ምክንያት ምንድነው?
7. ከቁ.6-7 እግዚአብሔር ቃየንን የመከረው እንዴት ብሎ ነው?
    - ይህስ እውነት ስለ እግዚአብሔር ባህርይ ምን ያስተምርሃል?
8. “ኃጢያት በደጅህ ታደባለች አንተ ግን ንገስባት” ሲል ምን ማለቱ ነው?
9. በቁ.8 መሠረት ቃየን ያደረገው ምንድነው?
    - በአዲስ ኪዳን ሰው፣ ሰውን ገደለ የሚያሰኘው መቼ ነው?
10. በዚህ ክፍል መሠረት የቃየን ትልቁ ስህተት ምንድነው ብለህ ታስባለህ?
11. የእግዚአብሔርን ቃል መተላለፍ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? “5-8”

12. ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ነገር ሁሉ እንዴት ሊሆን ይገባል? “ዕብ.11፥4”

13. ቃየን የራሱን መሥዋዕት ትቶ የወንድሙን በማየቱ ችግር ውስጥ ወደቀ፦

- የራሳችንን መሥዋዕት ብቻ መመልከት የሚጠቅመው ለምንድነው?
- የሌሎችን መሥዋዕት ካየን ልናስተውልና ልናደርገው የሚገባን ነገር ምንድነው?

## ጥናት ስምንት

## ኃጢአት፦ የሚያጠፋ እሳት

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 4፥16 - 5፥32

ዓላማ፦ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ የሚያጠፋ፣ ሕይወታችንንም በብዙ መልኩ የሚያውክ መሆኑን በመገንዘብ እግዚአብሔርን በመታዘዝ እና በመፍራት እንድንኖር ለመገንዘብ።

ማስገንዘቢያ፦

የአስጠኚው ማስታወሻ፦ እስከዛሬ ያየነው የዝፍጥረት መጽሐፍ ክፍል፣

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር መልካም አድርጎ መፍጠሩን (ዘፍ. 1፥39)
- አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በጣሱ ጊዜ በአለማችን ውስጥ የነበረው ሰላምና ስርዓት መደፍረሱን (ዘፍ. 3፥7-21)
- በአዳምና በሔዋን የጀመረው ኃጢአት፣ በእነሱ አላበቃ ብሎ ወደ ልጆቻቸው  እንደተዛመተ፣ እና ነፍስ  ማጥፋት የሚባል ለመጀመሪያ ግዜ ወደ አለማችን እንደገባ፣
- በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን እግዚአብሔር በኃጢአት ከእርሱ እየኮበለለ ያለውን ሰው ራሱ ሊያድነው ቃል እንደገባ  አሳይቶናል። የጥናቱን አንድነት እና አላማ ለመጠበቅ እነዚህን አሳቦች በጥናታችን ውስጥ ማዛመድ አንዘንጋ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ. 16 ላይ "ቃየንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ" ሲል ምን ማለት ይመስልሃል?

2. የዛፍ ፍሬ ቀጥፎ  በመብላት የተጀመረው ኃጢአት፣ ነፍስ ከማጥፋት አልፎ፣ አሁን የደረሰው የት ነው?

3. ከቁ.16- 24 ያለው ክፍል የቃየንን ትውልድ እየዘረዘረ ሲሄድ፣ ኃጢአትም እንዴት እየሰፋና እየከበደ እንደሔደ ያሳየናል።

   - በቁ.19 መሠረት በቃየን ዘሮች መካከል የተጀመረው ጸያፍ ነገር ምንድን ነው?

4. በቁ. 23 ላይስ የተገለጸው ከፉ ነገር ምንድን ነው?

   - ይህስ ኃጢአት እየሰፋና እየከበደ ስለመሄዱ ምን ያስገነዝብሀል?

5. እስከ አሁን ካየነው በመነሳት፣ ኃጢአት ሊቆም የማይችለው ለምንድን ነው? (ኃጢአት ለምን በአዳምና በሔዋን ብቻ አልቆመም?)

   - ከጊዜው ፈተና ለማምለጥ የእግዚአብሔርን ቃል ስንጥስ፣ የአንዱው ጥፋታችን ውጤት የት ሊያደርሰን ይችላል ብለህ ታስባለህ?

5. ዘፍ. 4፥25- 5፥32 ያለው ክፍል፣ ስለ ሴት መወለድና ስለ ዘሮቹ ይዘረዝራል። በቃየን እና በሴት ዘሮች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

- በዚህ ክፍል ውስጥ የሴት ዘሮች ኃጢአት እንዳደረጉ የሚናገርበት ቦታ የለም፣ ይህ ማለት ግን ኃጢአት የሌለባቸው ፃድቃን ናቸው ማለት ነው?
- ካልሆነ ግን ከክፍሉ ምን ማስረጃ እናገኛለኝ?

6. እስከ ምዕራፍ 5 ድረስ በነፍሰ ገዳዮች እጅ የሞቱ ሁለት ሰዎችን ቢዘግብም፣ የእድሜ ገደባቸው አልቆ ስለሞቱ ሰዎችና እድሜ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚናገረው በዚህ ክፍል ላይ ነው?

    - ሞትን ምን አመጣው? በዘፍ. 2፡17 ካለው ክፍል ጋር እንዴት ነው የሚገናኘው?
    - ሞት ለሰው ልጅ በረከት ነው ወይስ መርገም?
    - ሞት የሚባል ነገር ባይኖር ኖሮ ሰው ሊገጥመው የሚችለው ችግር ምንድን ነው?

*ለአስጠኚው፦ ሞት የሚባል ነገር ባይኖር ኖሮ፣ ሰው ስለ ኃጢአቱ የሚሞትለት ባልኖረ ነበር! ሞት ቅጣት ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ስለ ሰው ደህንነት ሲል ያዘጋጀው ነገር መሆኑን አንዘንጋ።(ዘፍ.3፡23)*

7. በ5፡28 ላይ ላሜሕ "እግዚአብሔር በረገማት ምድር" ማለቱ በጊዜው ለነበሩት ሰዎች የኑሮ ሁኔታ የሚገልጸው ምንድን ነው? ምዕ. 3፡ 17-19 ያለውን አወዳድሩ።

8. በዘፍ. 1፡39 እግዚአብሔር ሁሉን መልካም አድርጎ መፍጠሩን ሲገልጽ፣ ምዕ 2 አዳምና ሔዋን ስለተሰጣቸው መልካም የመኖሪያ ቦታ ይገልጻል።

    - ኃጢአት ከመግባቱ በፊትና በኋላ ያለውን የኑሮ ልዩነት ግለጽ።

9. ኃጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር የሚለያይ ክፉ ጋሬጣ ነው (ኢሳ. 59፡1-3)!

    - ይህን ጋሬጣ ሰው በራሱ ኃይል/ ጽድቅ ሊገታው ካልቻለ፣ ያለው ተስፋ ምንድን ነው?
    - እግዚአብሔርስ ለሰው ልጅ የሰጠው ተስፋ ምንድን ነው (ዘፍ. 3፡15)?

## ጥናት ዘጠኝ

## ክፉውንም ደጉንም የሚያይ እግዚአብሔር

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 6፥1-22

ዓላማ፦ በዚህ ምድር ስንኖር፣ የበላይ ተመልካች እግዚአብሔር እንዳለን አውቀን፣ ኑሮአችንን በአግባብ እንዴት አድርገን መምራት እንዳለብን ለመገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከባለፈው ጥናታችን በመነሳት፣ በምዕራፍ 4 እና 5 ላይ የተዘረዘሩት ሁለት ዘሮች እነማን ናቸው?
   - በሁለቱ ዘሮች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
2. በዛሬው የንባብ ክፍል መጀመሪያ ላይ፣ የሰውና የእግዚአብሔር ልጆች ብሎ የሚጠራው እነማንን ነው?
   - ለመሪው፦ እንደ ጌታችን ትምሕርት “መላእክት አያገቡም አይጋቡም” ማር.12፥25
   - እግዚአብሔር “መንፈሴ በሰው ልጆች ላይ ለዘላለም አይኖርም” እንዲል ያደረገው ምክንያት ምንድን ነው?
3. “ኔፊሊም” የሚባሉት ሰዎች ከየት የመጡ ናቸው? ምንስ ይመስላሉ?
   - ዘኁ. 13፥33 ላይ ያለውን በማየት ያወዳድሩ።
4. ቁ. 5፣11-12 እግዚአብሔርም የተመለከተው ምንድነው?
   - ከዘፍ. ምዕ. 3 ጀምሮ የሰው ልጅ ሕይወት የተለወጠው እንዴት ነው?
5. እግዚአብሔር የሰውን ክፋት ማየቱ እንዲወስድ ያስገደደው እርምጃ ምንድን ነው?(ቁ.6-7እና 13)
6. ከቁ.8-9 በመመልከት እግዚአብሔር በዚህ ሁሉ አመጽ ውስጥ ሌላ የተመለከተው ነገር ምንድነው?
   - እግዚአብሔር ሁልጊዜ በአመጽ ውስጥ ምን እንዳሉት ይህ ክፍል ያስገነዝበናል?
7. በቁ.12 እግዚአብሔር ያየው ምንድን ነው? በእግዚአብሔርስ ዕይታ፣ በኃጢአት የወደቀው ሰው ምን ያህሉ ነው? (ሮሜ 3፥23 ጋር እንዴት ይመሳሰላል ብለህ ታስባለህ?)
   - ኖህ “አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ” ሲል ምን ማለት ነው?
8. ኖህ፣ እግዚአብሔርን በመፍራት እና በቅንነት መሄዱን እግዚአብሔር ማየቱ እንዲወስድ ያደረገው እርምጃ ምንድን ነው? (ቁ. 13-22 ያለውን ያገናዝቡ)!

9. እግዚአብሔር ኃጢአትን አይቶ መፍረዱ፣ የሰውንም ፈሪሃ እግዚአብሔር ቆጥሮ መካሱን መረዳትህ በሕይወትህ እንዴት መመላለስ እንደሚገባህ ያስተምርሃል?

10. በቁ 18 ላይ እግዚአብሔር "ቃል ኪዳኔንም ከአንተ ጋር አቆማለሁ" ብሎ ለኖህ ቃል ሲገባለት፣ ስለ ምን ቃል ኪዳን ነው የሚናገረው? (ዘፍ. 3፡15 ጋር የተጠቀሰውን ቃል ኪዳን ያስታውሱ)

11. በኖህ ዘመን የነበሩት ሰዎች እግዚአብሔር እስከሚቆጣ ድረስ ኃጢአትን ሲያደርጉ፣ ማስተዋል ያቃታቸው ለምን ይመስልሃል? (ማቴ. 24፡37-39 ያለውን ያገናዝቡ)።

- እግዚአብሔር የሰውን አካሄድ አይቶ ሳይታሰብ በድንገት የሚቀጣ፣ እንዲሁም በድንገት የሚያድን መሆኑ የሚያስገነዝብህ ነገር ምንድን ነው?

12. እግዚአብሔር የሰውን ልብ እና ኩላሊት የሚያይ እና የሚመረምር አምላክ እንደ መሆኑ መጠን፣ ዛሬ እግዚአብሔር በድንገት ዋጋ ሊሰጥ ቢነሳ፣ እንደ ኖህ በፊቱ ሞገስ እናገኝ ይሆን?

- ሳይታሰብ ድንገት እግዚአብሔር ለአድራጎታቸው ምላሽ የሰጣቸውን እነዚህን ሰዎች ያስተውሉ፦
    - ሉቃ. 1፡5-13 ዘካሪያስ
    - ዘፍ. 19፡1-29 ሎጥ፣ የሰዶምና የጎሞራ ሰዎች

## ጥናት አስር

## የእግዚአብሔር ፍርድ!

**የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 7፡1-24**

**ዓላማ፦** እግዚአብሔር ታጋሽ እና ምህረቱ የበዛ አምላክ እንደ መሆኑም መጠን፣ እንዲሁም ኃጢአትንም የሚቀጣ አምላክ መሆኑን ተረድተን፣ በእግዚአብሔር ፊት፣ በፍጹም ፍርሃትና መታዘዝ መኖር እንደሚገባን ለመገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ዘፍ. 5 32 እና ዘፍ. 7፡6፣ 11ን በመመልከት እግዚአብሔር ኖህ መርከብን እንዲሰራ ባዘዘው ጊዜ እና የጥፋት ውሃን ባመጣበት ጊዜ መካከል ምን ያህል የጊዜ ልዩነት ይኖራል ብለህ ትገምታለህ?

2. በዚህ የጊዜ ገደብ መካከል ኖህ መርከብ ከመስራት ሌላ ምን እያደርገ የኖረ ይመስልሃል? (2ኛ ጴጥ. 2፡ 5 ምን ፍንጭ ይሰጥሃል?)

3. እግዚአብሔር ኃጢአትን ያደርጉ የነበሩትን የኖህ ዘመን ሰዎች፣ እንደሚያጠፋቸው ከዘመናት በፊት ቢናገርም፣ መቶ አመት ያህል የታገሰው ለምን የመሰልሃል?

   - በ1ኛ ጴጥ 3፡19-20 ያለው ክፍል "የእግዚአብሔር ትዕግስት በቆየ ጊዜ" የሚለው ሐረግ ምን ሃሳብ ይሰጣል?

   - እግዚአብሔርስ የሚታገሰው ለምን ይመስልሃል?

4. ዛሬ በሕይወት ዘመናችን ውስጥ ሰዎች ክፉና ጸያፍ የሆነ ነገር ሲያደርጉ (እኛም ስናጠፋ) እግዚአብሔር ፈጥኖ የማይቀጣ እና የማይፈርደው ለምንድን ነው?

5. በቁ.2-4 ባለው ክፍል መሠረት እግዚአብሔር ሊያጠፋ የፈለገው እንሰሳዎችንም ጭምር ነው። ዘፍ 6፡ 7 እንዲሁም 7፡4፣ 21-22 ያለውን ይመልከቱ።

   - እግዚአብሔር በእንሰሳዎችም ጭምር እንዲቆጣ ለምን አስፈለገው?

     - (ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር አዳም በረገመው ጊዜ የሆነውን ያስታውሱ)።

   - እግዚአብሔር ሊፈርድ ሲነሳ ስህተታችን ምን ያህል ብዙ ነገር ሊያጠፋ እንደሚችል ይህ እውነት ያስገነዘበናል?

6. ኖህና ቤተሰቡ እንዲሁም ወደ ከጥፋቱ የተረፉት እንሰሶች ሁሉ ወደ መርከቡ ከገቡ በኃላ በሩን የዘጋው ማነው? ኖህ ለምን አልዘጋውም?

   - እግዚአብሔር ዝናቡን እያዘነበ ባለበት ጊዜ ሰዎቹ ንስሃ ቢገቡስ ኖሮ፣ እግዚአብሔር ይቅር ይላቸው ነበር ብለህ ታስባለህ?

   - ይህስ በአሁኑ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ጸጋና ስለ ሚመጣው የፍርድ ጊዜ ምን ያስተምረናል?

7. ኖህ ጽድቅን ይሰብክ በነበረበት ዘመን በጊዜው የነበሩት ሰዎች ያደርጉ የነበረው ነገር ምንድን ነው?

   - (ማቴ 24፡33-34 ያለውን ያገናዝቡ።)

8. ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ዛሬ በዘመናችን ካለው ሁኔታ ጋር እንዴት ይመሳሰላል?

- በተለይ ሰዎች የወንጌል ጽድቅ ሲሰበክላቸው እና ክርስቶስን አንቀበልም ሲሉ የሚያስገነዝብህ ነገር ምንድን ነው?
- የእግዚአብሔር ፍርድ በሚገለጥበት ጊዜስ ንስሃ መግባት ቢፈልጉ የሚድኑ ይመስልሃል? ለምን?

9. እኛም እንደ ኖህ በዚህ ዘመን እግዚአብሔር የሚጠብቅብን ነገር ምንድነው?

ኖህ የጽድቅ ኑሮ በመኖሩ ቤተሰቡን አተረፈ፣ እኛስ ቤተሰቦቻችንን ለማትረፍ ምን ማድረግ ይገባናል?

## ጥናት አስራ አንድ

## እግዚአብሔርን በትግስት መጠበቅና መታዘዝ

**የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 8፡1-24**

ዓላማ፡- የማይመስል ሁኔታ እንኳን ውስጥ ብንሆን እግዚአብሔር የተናገረውን በጊዜው እስኪፈጽመው ድረስ በትዕግስት መጠበቅ እንዴት እንዳለብን እንድንገነዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ.1 መሠረት እግዚአብሔር ያሰበው ስለምድነው?
   - መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አሰበ ሲል ምን ማለቱ ነው?
   - ከቁ.1-2 እግዚአብሔር ማሰቡ ያስገኘው ውጤት የተገለጸው እንዴት ነው?

2. ከቁ.3-5 የተገለጸው ሃሳብ የተዘረዘረው እንዴት ነው?
   - እግዚአብሔር ውሃውን ከመቅጽፈት አላደረቀውም፣ ይህ ስለ እግዚአብሔር አሰራር ምን ያስተምረናል
   - ይህስ እውነት በአሁን ግዜ ስለ እግዚአብሔር አሰራር የሚስተምረን እንዴት ነው?

3. ከቁ.6-12 ክፍል የተገለጹት ሁለት እንስሶች ምድናቸው?
   - ሁለቱም እንስሶች የተሰጣቸው ሃላፊነት ምንድን ነበር?
   - ከሁለቱ ሃላፊነቱን በሚገባ የተወጣው የቱ ይመስልሃል? ምክንያትህን አስረዳ ?
   - ይህስ ሃሳብ ሃላፊነትን ስለ መቀበልና መፈጸም ምን ያስተምረናል?

4. ቁ.4 መርከቢቱ በተራራ ላይ ካረፈችበት እና፣ ቁ.14 ኖህ ሙሉ ለሙሉ ምድር መድቁረን እስካየበት ምን ያህል ግዜ ይመስልሃል ?
   - በዚህ ግዜ መሃል ለኖህ ምን ዓይነት ፈተና በሃሳቡ ሊገጥመው ይችላል ብለህ ታስባለህ ?
   - በእንደዚህ ዓይነት ሰዓት ኖህ ካደረገው እኛ ልንማረው የሚገባው ምንይመስልሃል?

5. ከቁ.15-19 እግዚአብሔር ኖህን የተናገረውን እና ኖህም ያደረገው ምንድነው?
   - በእንደዚህ ዓይነት ሰዓት እኛስ ከኖህ ልንማረው የሚገባን ምንድነው?
   - ከምዕ 7፡ 16 በማነጻጸር ተመልከቱት

6. በቁ.20 ኖህ ያደረገውን ነገር በቅደም ተከተል ምድነው? ከሌላው ነገር መጀመሪያ ይህን ማድረጉ ስለኖህ ህይወት ምን ያመለክታል?

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር ከዚያም ሊላው ሁሉ ተከታይ ስለመሆኑ ምን ያስገነዝበናል?
- ከሚያደርግልን ነገር በላይ እግዚአብሔርን ስለማስበለጥ ምን ያስተምረናል?

7. በቁ.21 ለዚህ ዓይነቱ አምልኮና መሥዋዕት የእግዚአብሔር ምላሽ እንዴት ነበር?
    - እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትና የሚቀበለው አምልኮም ሆነ ምስዕዋት ከምን የተነሳ ይመስልሃል?

8. በቁ.22 ላይ በዝርዝር ተጽፎ የምንመለከተው ምንድንነው?
    - ከዚህ ቀደም ጊዜያትና ወቅታት የሉም ነበረ ማለት ነው?
    - ስለ መዝራትና ማጨድ በአዲስ ኪዳን የተገለጸው እንዴት ነው?(ገላ.6፡7-9፣2ቆሮ.9፡6-7)
    - የጊዜያት መቀያየር ከሰው ሕይወት ጋር የሚያመሳስለው እንዴት ነው?(መክ. ምዕ. 3)

9. ይህ ክፍል ስለመታዘዝ እና ስለ መጽናት የሚያስተምርህ እንዴት ነው?

10. ስለ እግዚአብሔር ታማኝነትስ ይህ ክፍል ምን ያስተምረናል?

10. በነገር ሁሉ እድትጸና ሊረዳህ የሚያስችልህ እውነት ከዚህ ክፍል ምንድነው?

## ጥናት አስራ ሁለት

## እግዚአብሔር የቃልኪዳን አምላክ ነው

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 9፡1-10፡1-19

ዓላማ፡- እግዚአብሔር ለሰው ቃል ኪዳን የሚሰጥና የሰጠውንም ኪዳን የሚጠብቅ አምላክ እንደሆነ አውቀን በእምነትና በድል ሕይወት መኖር እንዴት እንደሚገባን ለመንገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቁ.1-2 እግዚአብሔር ለኖህና ለቤተሰቡ የተናገረውን ምንድን ነው?
   - ይህስ ሃሳብ ከዘፍ.1፡28 የሚመሳሰልበት መንገድ እንዴት ነው?
   - እግዚአብሔር በዚህ ቦታ ድጋሚ መናገር ለምን አስፈለገው?
2. በቁ.3 መሠረት ለሰው የተሰጠው ምግብ ምን ዓይነት ነው?
   - ይህ የምግብ ዓይነት ከዘፍ.1፡29-30 ካለው ጋር ምግብ ያለው ልዩነት ምንድነው?
   - በአሁን ጊዜ አዲስ ኪዳን ስለ ምግብ የሚያስተምረን እንዴት ነው?
     - (ማር.7፡15፣ 1ጢሞ 4፡4፣ 1ቆሮ.8፡8፣ ሮሜ 14፡6፣)
   - አዲስ ኪዳን ምግብንስ በተመለከተ የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድነው?
     - (ሮሜ 14፡1-4፣ 1ቆሮ.8፡9-14)
3. ከቁ. 4-5 እግዚአብሔር የከለከለው ምግብ ምንድነው? የከለከለበትስ ምክንያት?

   እግዚአብሔር ደምን እንዳይበሉ መከልከሉ ምን ምስጢር እንዳለው ለመግለጽ ነው?
4. በቁ.6 ላይ የሚናገረው ስለምንድነው? ቅጣቱ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያትስ?
   - ይህ ሃሳብ ከምዕ. 4፡10-12 የሚመሳሰልበት መንገድ እንዴት ነው?
5. ከቁ.8-10 እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባው ለማንና ለማን ነው?
   - በቁ. 11 ላይ የተገለጸው የቃልኪዳኑ ዓይነት ምንድንነው?
6. በቁ.12-17 እግዚአብሔር ለቃልኪዳኑ ማረጋገጫ የሰጠው ምልክት ምንድነው?
   - ቃልኪዳኑ ፍጥረትን ሁሉ ማካተቱ፣ ስለ እግዚአብሔር ምን ያስተምረናል?
   - እግዚአብሔር የቃል ኪዳን አምላክ ስለመሆኑ ምን ያስተምረናል?

7. ከቁ.18-19 እና በምዕ.7፡16 መካከል የምትመለከተው ምስጢር ከአለ ግለጽ?

- ይህስ እውነት ስለ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ምን ያስተምርሃል?
- በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ታምኖ መኖርስ የሚያመጣው ውጤት ምንድንነው?

8. ከእንግዲህ ወዲህ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ ታምኖ ለመኖር እንድትችል ይህ ክፍል እንዴት ያስተምርሃል?

## ጥናት አስራ ሦስት

## ገበናህን አትግለጥ

**የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 9፡ 20-29**

**ዓላማ፡- ትንሽ ስህተት በሰው ሕይወት ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ ምን እንደሚመስል እንድንረዳና በስህተት ውስጥም የሚገኙትን ሰዎች እንዴት ልንረዳ እንደሚገባ እንድንገነዘብ።**

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ.20 ስለ ኖህ ሙያና ስለ ተከለው ነገር የተገለጸው እንዴት ነው?
   - ኖኅ ወይን ጠጅ የመጠጣቱ ውጤት ያስከተለው ችግር ምድነው? (21)
   - በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እራቁታቸውን ሆኑ ተብለው የተገለጹ ሰዎች እነማንቸው?
   - እራቁታቸውን የሆኑበትም ምክንያት አስረዳ?
2. ቁ.20-21 እና ያዕቆብ 1፡12-15 የሚያመሳስለቸው ሃሳብ ምንድነው?
   - ኖኅን የመሰለ ታላቅ የእምነት ሰው ትንሽ በምትመስል ነገር መሳቱ ለአንተ የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድነው?
   - የኖኅ ስህተት በአሁኑ ጊዜ በእንዴት ዓይነት መንገድስ ሊከሰት ይችላል?(ምሣሌ ስጥ)
3. የኖኅ እራቁትነት በልጆቹ መሃል የፈጠረው ነገር ምንድነው?
   - በካም፣ በሴምና ያፌት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
4. በአሁኑ ጊዜ የእራቁትነት ምሣሌ ምንድነው?
   - እራቁቱን የሆነ ሰው ቢያጋጥመን መውሰድ የሚገባን እርምጃ ምንድነው?
   - ይህስ ሃሳብ ከገላትያ 6፡1- እና ከዘፍጥረት 3፡ ጋር የሚያገናኝበት መንገድ አለን?
5. ከቁ.25-29 የኖኅ ልጆች ድርጊት ያስከተለው ውጤት ምንድነው?
6. ኖኅ በልጆቹ ላይ የተናገረው ቃል ትርጉሙ ምን ይመስልሃል?
7. ትንሽ ስህተት፣ ምን ዓይነት አደጋ ላይ ሊጥልህ እንደሚችል ይህ ክፍል ያስተምርሃል?
   - ከእንደዚህ ዓይነቱስ አደጋ ለመዳን፣ ምን ማድረግ ያለብህ ይመስልሃል?
8. የሌሎችን ገበና በመሸፈንና በመግለጥ የሚገኘውን ውጤት ይህ ክፍል እንዴት አስተምሮሃል?
9. ከእንግዲህ ወዲህ የሰውን ገበና ለመሸፈን ምን ማድረግ አለብህ?
   - የሰውንስ ገበና የምትሸፍነው በምንና በምን ዓይነት መንገድ ነው?

## ጥናት አስራ አራት

## የሚጸናው የእግዚአብሔር ሃሳብ

**የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ.10፡ 1-ዘፍ.11፡32**

**ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ከአንድ ቤተሰብ ጀምሮ የመላውን ዓለም ታሪክ የሚቆጣጠርና የሚገዛ አምላክ እንደሆነ አውቀን በታማኝነት መኖር እንዴት እንደሚገባን ለመረዳት።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ቁ.1-2 መሠረት በአሁኑ ዘመን ላለው ትውልድ መገኘት አስተዋጾ ያደረጉት እነማን ናቸው?
   - አንድ ቤተሰብ ምድርን ሁሉ መሙላት መቻሉ ስለ እግዚአብሔር አሰራርና ባህርይ ምን እንማራለን?
   - እግዚአብሔር በቤተሰብም ሆነ በሕብረተሰብ ላይ ዓላማ እንዳለው መመልከታችን በግላችንም ይሁን በጋራ ስለምንወስዳቸው ውሳኔዎች ምን ያስተምራለን?
2. በምዕ.11፡1 መሠረት የነበረው የዓለም ቋንቋ ስንት ነበር?
   - በምዕ.10፡ 5, 20, 31 መሠረትስ?
   - የትኛው ታሪክ የሚቀድም ይመስልሃል የምዕ.10 ወይንስ 11?
3. 11፡2-5 ሰዎች እርስ በርሳቸው የተነጋገሩትና፣ የንግግራቸው ዓላማስ ምን ነበር?
   - የምናደርገውን ነገር የምናደርገው ለምድነው ብለን ራሳችንን መጠየው አስፈላጊ መሆኑን ከዚህ ታሪክ እንማራለን?
4. ሊሰሩት ያሰቡትን ከተማ ዓይነት የገለጹት እንዴት ነው?
   - ወደ ሰማይ የሚደራስ ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? 9፡1
   - ይህ ሃሳብ ከኢሳያስ 14፡ ጋር የሚገናኘው በምን መልኩ ነው?
5. 11፡5-9 እግዚአብሔር ያሰቡትን እንዳይፈጽሙ የከለከላቸው ለምን ይመስልሃል?
   - አንድን ነገር ስናቅድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለ መጠየቅ ምን ያስተምረለን?
6. ቁ.6 "ያቀዱትን ሳይፈጽሙ" የሚለውን አባባል እንዴት ትረደዋለህ?
7. በቁ.7 ላይ እግዚአብሔር የተናገረው ምን ብሎ ነው?
8. ከቁ.10-26 መሠረት እግዚአብሔር የዓለምን ህዝብ ታሪክ ወዴት ሲመራው ትመለከታለህ?
   - ይህስ ሃሳብ ከሐዋርያት ምዕ... የሚመሳሰልበት መንገድ እንዴት ነው?
   - ከምስቅልቅል ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር መልካም ነገር ማውጣት እንደሚችል ምን ተረዳህ?

9. ያንተንም ሆነ የዓለምን ታሪክ ሂደት በበላይነት የሚቆጣጠር ማን እንደሆነ ይህ ክፍል እንዴት ያስተምርሃል ?

10. የእግዚአብሔርንስ ፈቃድ በሕይወትህ መረዳትህና መፈጸምህ ከምን እንደሚያድንህ ይህ ክፍል ያስተምርሃል?

11. እግዚአብሔር ላንተም ሆነ ለቤተሰብህ ትልቅ ዓላማ እንዳለው መረዳትህ በሕይወትህ በምን ረገድ ለውጥ የሚያመጣ ይመልሃል?

## ጥናት አስራ አምስት

## <u>እግዚአብሔርን መታዘዝ</u>

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ.12፡1-9

ዓላማ፡- እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ መታዘዝ ብለን ስንል ምን ማለት እንደሆነና በተጨማሪም እግዚአብሔርን ስንታዘዝ የሚያስከተለው በረከት ምን እንደሆነ ለመገንዘብ ነው።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ.1 ላይ እግዚአብሔር ለአብራም የሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው?

- ለአብራም የተሰጠው ትዕዛዝ ከባድ ነው እንድትል ያስቻለህ ምክንያት አለ?
- እንደ አብራም ድንገተኛ ትዕዛዝ ቢቀርብልህ መልስህ ምን የሚሆን ይመስልሃል? ለምን?

2. የእግዚአብሔር ትዕዛዝ በአሁን ጊዜ በምን ዓይነት መንገድ ሊገለጥ ይችላል?

- <u>*“ወደ ማሳይህ ምድር ውጣ”*</u> የሚለው ሃሳብስ ምንን የሚይጠይቅ ይመስልሃል?

3. ከቁ.2-3 እግዚአብሔር ለአብራም የሰጠው የተስፋ ቃል ምንድነው?

- የእያንዳንዱን ሃሳብና ትርጉም፣ ከእኛም ጋር ሊገናኝበት የሚችልበትን መንገድ በዝርዝር ተነጋገሩበት

4. ከቁ.3-6 አብራም ትዕዛዙን ከሰማ በኋላ ያደርገው ምንድነው?

- ይህስ እውነት ስለ አብራም ባህርይ ምን ያስገነዘበናል?
- ከአብራም አወጣጥ <u>*“ይዞ ባይወጣ”*</u> ጥሩ ነበር የምትለው ነገር ምንድን ነው? ለምን?

5. በቁ.7 ላይ እግዚአብሔር ለአብርሐም የሰጠው ተስፋ ምንድነው?

- ምድሪቱ ግን በማን ተይዛ ነው የምንምለከተው? (ቁ.5 መጨረሻን ይመልከቱ)
- ይህስ እውነት ስለ እግዚአብሔር አሰራር የሚያስተምረን እንዴት ነው?
- አብራም እግዚአብሔርን ታዞ ባይወጣ ምን ምን ዓይነት በረከት ይቀርበት ነበር?
- በዚህ ሃሳብ መሠረት መታዘዝ <u>የሚያመጣውና የሚያስቀረው</u> በረከት ምን ይመስልሃል?

6. ከቁ.8-9 አብራም በተደጋጋሚ ያደረገው ነገር ምንድነው?

- አብራም መሠዊያ የሚሰራበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
- እኛስ በአሁን ጊዜ የምንሰራው መሠዊያ ምን ዓይነት ነው?
- መቼ መቼስ ነው መሠዊያ የምንሰራው?

7. ይህ ክፍል መታዘዝ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ አስተምሮሃል?
8. የመታዘዝ ውጤት ምን እንደሆነ ይህ ክፍል አስተምሮሃል? የአለመታዘዝስ?
9. እግዚአብሔር እንደ አብራም ድንገት ትዕዛዝ ቢያቀርብልህ ዝግጁ የምትሆን ይመስልሃል?
10. አልተዘጋጀሁም ካልክ፣ የምትዘጋጅበት መንገድ በእንዴት መልኩ የሚሆን ይመስልሃል?

## ጥናት አስራ ስድስት

## <u>እግዚአብሔርን በሁሉ መታመን</u>

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ.12፡10-20

ዓላማ፡- የፍርሃት አስከፊ ገጽታ ምን እንደሚመስልና በተጨማሪም ሰው ከፍርሃት ነጻ ወጥቶ ጤናማ ሕይወት ለመኖር የሚችልበትን መንገድ ለመገንዘብ ነው።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ.10 ላይ የተገለጸው ሃሳብ ምንድን ነው?
   - ይህን ሃሳብ (ከም.26፡1-6) አነጻጽረህ ተመልከት፦
   - በዚህ ሃሳብ መሠረት አብራም ሊወስደው ይገባ የነበረው እርምጃ ካለ ግለጽ? ለምን?
2. ከቁ.11-14 የአብራም የፍርሃት ምክንያት ምንድን ነው?
   - ለፍርሃቱስ መፍትሄ ብሎ ያቀረበው ምክንያት ምንድንነው?
3. ቁ.2-3 በመመልከት አብራም ከፍርሃቱ ነጻ ለመውጣት ምን ማድረግ ነበረበት?
4. ከቁ.14-17 እነ አብራም ወደ ግብጽ ሲገቡ ያጋጠማቸው ምንድነው?
   - ይህ ሃሳብ (ከም.26፡8-11) ጋር የሚመሳሰለው በእንዴት ዓይነት መንገድ ነው?
   - የምንዘራው ስህተት ውጤት እስከ የት ሊደርስ እንደሚችል ይህ ክፍል ያስተምርሃል?
5. በቁ.17 ላይ እግዚአብሔር ያደርገው ነገር ምንድን ነው?

   እግዚአብሔር በፈርኦን ላይ ይህን መቅሰፍት ያመጣበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
6. ከ18-20 ፈርኦን የተናገረውና ያደረገው ምንድን ነው?

   ይህስ እውነት ስለ እግዚአብሔር ባህርይና ስለ ሰው ድካም ምን ያስተምረናል?
7. በዚህ ክፍል መሠረት የችግሩ ዋነኛ መንስኤ ሆኖ ያገኘኸው ነገር ምንድነው?
8. የፍርሃት ውጤት የሚያስከትለው መዘዝ ምን እንደሆነ ይህ ክፍል አስተምሮሃል
9. ከፍርሃት ነጻ ለመውጣት ማድረግ የሚገባህ ተቀዳሚው ተግባር ምን እንደሆነ ተምረሃል?
10. በአሁን ጊዜ አንተስ የምትፈራበት ነገር አለህ? እንዴትስ ነጻ ልትወጣ ትችላለህ?
11. ከዚህ ፍርሃትህስ ነጻ መውጣት የሚገባህ ለምን እንደሆነ ይህ ክፍል አስተምሮሃል?

## ጥናት አስራ ሰባት

## <u>የእግዚአብሔርን በረከት መመልከት</u>

**የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ.13፡ 1-18**

**ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም እንድንኖርና በተጨማሪም የሕይወት ውሳኔዎቻችን ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት ሊሆኑ እንደሚገባ ለመገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ.2 ላይ ስለ አብራም የተጠቀሰው ሃሳብ ምንድነው?
    - የአብራም ብልጽግና መሠረት ምንድነው? (ዘፍ.12፡1-3)

2. ከቁ.3-4 አብራም ከየት ተነስቶ ወዴት ሄደ?
    - አብራም ወደዚህ ስፍራ ሊመጣ የፈለገበት ምክንያት ለምንድነው?
    - “የእግዚአብሔርን ስም ጠራ” ብሎ ሲል ምንማለቱ ነው?
    - ከአብራም ሕይወት ላንተ የምትወስደው ትምሕርት (ከዚህ ሃሳብ) ምንድን ነው?

3. ከቁ. 5-7 ላይ የተከሰተው ችግር ምንድነው?
    - ለተከሰተው ችግር የአብራም መፍትሄ ምንድን ነበር?
    - ከአብራም ባህርይ አንጻር ለሎጥ የመጀመሪያውን ምርጫ ከመስጠቱ ምን ትገነዘባለህ?
    - የአብራምን ዓይነት ምሣሌ በአሁን ጊዜ በምን መንገድ ተግባራዊ ማድረግ እንችላለን?

4. ከ10-13 ሎጥ ምርጫውን መሠረት ያደረገበት ዋና ምክንያት ምንድን ነው?
    - በቁ.13 መሠረት በሎጥ ምርጫ ውስጥ ያልተካተተ መሠረታዊ ሃሳብ ምንድነው?
    - አንድን ነገር መርጠን ከመወሰናችን አስቀድሞ የሎጥ ሕይወት ምን እንድናስተውል ያስገነዝበናል?

5. ከ14-17 አብራም ግጭቱን በሰላም በመፈጸሙ ምክንያት ያገኘው በረከት ምንድንነው?
    - በዚህ ሃሳብ መሠረት ከሁለቱ ያተረፈ ማነው? ምክንያቱስ?

6. በቁ.18 አብራም ያደረገው ምንድነው?
    - ይህን ሃሳብ ከ13፡4 ጋር ተመልከትና ከአብርሐም መልካም ባህርይ የተማርከውን ግለጽ

7. ይህ ክፍል የራሳህን መብት ትተህ ሌሎችን ማስቀደም ያስተማረህ እንዴት ነው?

- ይህንን እውነትስ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስከትለው በረከት ምንድነው?
- በአሁኑ ጊዜስ ይህንን ሃሳብ በተግባር ለመፈጸም ምን ማድረግ እንዳለብህ ያስተምርሃል?

8. በቁ.10 እና 14 መሠረት ሁለቱም (አብራምና ሎጥ) እንደተመለከቱ ይነግረናል፦
   - በሁለቱም እይታ ውስጥ ያለው መሠረታዊ ልዩነት ምንድነው?
   - እግዚአብሔር የሚያሳየህን በረከት ለማየት እንድትችል ምን ማድረግ እንደሚገባህ ይህ ክፍል ያስተምርሃል?

## ጥናት አስራ ስምንት

## ምርኮን ማስመለስ

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ.14፥1-16

ዓላማ፡- እግዚአብሔር በጠላት የተወሰደን የእኛንም ሆነ የሌሎችን ምርኮ እንደሚያስመልስል አውቀን በእምነት ወጥተን እንዴት ድልን ለመንጎንጸፍ እንደምንችል ለመገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቁ.1-10 የተከናወነውን ነገር ሁሉ በዝርዝር ተነጋገሩበት?
2. በቁ.11 ላይ በሰዶምና ገሞራ ሕዝብ ላይ የተፈጸመው ድርጊት ምንድን ነው?
3. በቁ.11 ላይ በነገሥታቱ ተማርከው ከተወሰዱት ውስጥ እነማን ይገኙበታል?
   - የሎጥ መማረክን በተመለከተ እና በምዕ.13፥10-11 ጋር ምን የምትመለከተው እውነት አለ?
4. ከ13-16 አብራም ስለ ሎጥ መማረክ ከሰማ በኋላ ያደረገውን በዝርዝር ተነጋገሩበት?
   - አብራም ሎጥን ተዋግቶ ላለመስለቀቅ ምን ምክንያት ማቅረብ ይችል ነበር?
   - በዚህ ሃሳብ መሠረት ከአብራም የተገነዘብከው ልዩ ባህርይ ምንድን ነው?
5. በአሁኑ ጊዜ ምን ምን ዓይነት ምርኮ በጠላት ሊወሰድብን ይችላል?
   - ምርኮን ለማስመለስ ከመውጣት በፊት ምን ማድረግ እንዳለብን ይህ ክፍል ያስተምረናል?
   - ምርኮን ለማስመለስ ቆርጠን ከተነሳን እስከ ምንስ ድረስ መጓዝ እንዳለብን ይህ ክፍል በተጨማሪ ያስገነዝበናል? (ቁ.16-17)
6. ምርኮን ማስመለስ የምንችልበት ዋነኛ መሳሪያ ምንድንነው?
   - ከኤር.29፥12-14 ጋር የዚህ ጥያቄ መልስ የሚገናኘው በምን መልኩ ነው?

7. እግዚአብሔር የእኛንም ሆነ የወገኖቻችንን ምርኮ ይመልሳል ብለህ ታምናለህ?

8. ይመልሳል ብለህ የምታምን ከሆነ ከአሁን ጀምሮ ምን ማድረግ የሚገባህ ይመስልሃል?

## ጥናት አስራ ዘጠኝ

## የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር

**የምንባብ ክፍል፦** ዘፍ.14፡17-24

**ዓላማ፡-** የሌሎችን ምርኮ ለማስመልስ ስንተጋ ሊያጋጥመን የሚችለውን ፈተናና በረከት ምን እንደሆነ አውቀን በእምነት እንዴት እንደምንጸና ለመገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቁ.17-18 አብራምን ሊቀበሉ የወጡ ሁለት ነገሥታቶች እነማን ናቸው?
2. ከሁለቱም ነገሥታት የተለየ ነው የምትለው ማነው? ለምን?
3. በቁ.18 የተገለጠው የመልከ ጼዲቅ አገልግሎት ምንድነው?
   - መለከ ጼዲቅ እንጀራና የወይን ጠጅ ያወጣው ለምንድን ነው?
4. መልከ ጼዲቅ ሁለት ስም አለው፣ የስሙ ትርጉም ምን እንደሆነ ግለጽ? (ዕብ.7፡2)
5. አብራምን የባረከው ምን ብሎ ነው? ይህ ስለ መልከ ጼዲቅ ምን ያስረዳል (ዕብ.7፡6-7)
6. አብራም አስራትን ለመከ ጼቅዲ ሰጠው፣ይህ ስለ መልከ ጼዲቅ ምን ያሳያል? (ዕብ.7፡4-10)
7. መልከ ጼዲቅ የማን ምሳሌ ነው? ከክርስቶስ ጋር የሚመሳሰልበት መንገድስ? (ዕብ.20-21)
8. ከቁ.22-24 የሰዶምን ንጉሥ ለአብራም የተናገረው ምንድን ነው?
   - አብራም አልወስድም ያለበት ምክንያት ለምንድን ነው?
   - አብራም ለአንዱ ንጉሥ እሺ ለአንዱ እንቢ ማለቱ ምን ያስተምርሃል?
9. ምርኮህን ጌታ ከመለሰልህ በኋላ ከምን ፈተና እንድትጠበቅ ይህ ክፍል አስተማረህ? (21)
10. የሌሎች ምርኮን ስታስመልስ የሚገጥምህ በረከት ምን እንደሆነ ክፍሉ አስተማረህ? (18-20)

## ጥናት ሃያ

## ቃል ኪዳንን እግዚአብሔር ሃሳብ

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ.15፡ 1-21

ዓላማ፡- እግዚአብሔር ከአንድ ቤተሰብ ጀምሮ የመላውን ዓለም ታሪክ የሚቆጣጠርና የሚገዛ አምላክ እንደሆነ አውቀን በታማኝነት እንዴት ማገልገል እንደሚገባን ለመገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ምዕ.14ን በማሰብ እግዚአብሔር ለአብርሐም የተገለጠበት ምክንያት ለምንድነው?

2. በ15:1 እግዚአብሔር ለአብርሐም የተገለጠበት መንገድና የተናገረው ምንድነው?
   - "እኔ ያንተ ጋሻ ነኝ" ሲለው ምን ማለቱ ይመስልሃል? ለምንስ ያለው ይመስልሃል?
   - በአሁኑ ጊዜስ እግዚአብሔር ለእኛ ጋሻ የሚሆንበት መንገድ እንዴት ነው?

3. ከቁ.2-3 አብርሐም ለእግዚአብሔር ያቀረበው ጥያቄ ምንድነው?
   - በአብርሐም ጥያቄ ውስጥ የምትመለከተው ምን ነገር አለ?
   - እግዚአብሔር የተናገረውና ያለንበት ሁኔታ የሚጋጭበት ጊዜ አለን? ምሣሌ ስጥ

4. ከ4-5 እግዚአብሔር የተናገረውና ያደረገው ምንድነው?
   - እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ሰው ምንም ሳይኖረው ትልቅ ተስፋ የሚሰጠው ለምንድነው?

5. በቁ.6 መሠረት አብርሐም ለተነገረው ተስፋ የሰጠው ምላሽ እንዴት ነበር?
   - አብርሐም የተሰጠውን ተስፋ ማመኑ ያመጣው ውጤት ምንድንው?
   - እግዚአብሔር የተናገረውን ማመን ጥቅሙ ምንድነው?
   - የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ በረከት መሆኑን እያወቅን መታዘዝ ለምን ያቅተናል?

6. በቁ.8 አብርሐም እግዚአብሔርን ጥያቄ የጠየቀበት ምክንያት ለምንድን ነበር?

7. ከቁ.9-10 ያለውን ሃሳብ በመመልከት አብርሐም እንዲያደርግ የታዘዘው ምንድነው?
   - አብርሐም የጠየቀው ጥያቄና እንዲያደርግ የታዘዘው ነገር ምን ግኑኝነት አለው?

8. ቁ.11 አብርሐም የሚያባረረው ምንድነው?
   - በአሁን ጊዜ ለእኛ የሚያስተላልፈው መንፈሳዊ ትርጉም ምን አለ?

9. በቁ.12 ላይ የተከሰተው ሃሳብ ምንድነው?

- ከባድ እንቅልፍና ድንጋጤ በአብራም ላይ የመጣበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
- ይህ ሃሳብ የእግዚአብሔርን ተስፋ ከመጠበቅ አንጻር ምን ያስተምረናል?

(ቁ.11ን በተጨማሪ ተመልከቱ)

10. ከቁ.13-16 ከእግዚአብሔር ለአብራም የተነገረው ቃል ምን እንደሆነ በዝርዝር ተወያዩበት

- እግዚአብሔር ለአብራም ስለዘሩ አስቀድሞ ትንቢት የነገረው ለምንድነው?
- "የአሞራውያን በደል ገና አልተፈጸምና" ብሎ ሲልስ ምን ማለቱ ነው?

11. በቁ.17 ላይ የተከናወነውን በዝርዝር ተነጋገሩበት

- የምድጃና ጢስና የእሳት ነበልባል በመስዋዕቱ መካከል ማለፉ ትርጉሙ ምንድነው?

12. በጥንት ጊዜ ቃል ኪዳን የሚገቡ ሰዎች በመሥዋዕቱ መሃል ማለፍ ይገባቸው ነበር፣ በዚህ ሃሳብ መሠረት፦

- አብርሐም በመሥዋዓቱ መሃል ሳያልፍ ተመልካች ብቻ ሆኖ መቀመጡ ለምን ይመስልሃል?
- ይህስ ሃሳብ ከዕብራውያን 6፡17-18 ጋር የሚገናኝበት መንገድ እንዴት ነው?

ቃል ኪዳን ከዚህ ቀደም (2-3) አብርሐም ጥያቄ ጠይቆ ምን አግኝቷል?

- ይህ ስለ አብርሐም አስተዋይነት ምን ያስተምረናል?
- እኛስ ከአብርሐም ልንወስደው የሚገባን ትምሕርት ምንድንነው?

## ጥናት ሃያ አንድ
## በትዕግስት መጠበቅ

**የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ.16፡ 1-6**

**ዓላማ፦** እግዚአብሄርን እስከመጨረሻው ድረስ ታማኝ ሆኖ አለመጠበቅ የሚያስከትለው ውጤት ምን እንደሆነ አውቀን በትዕግስት እንዴት መጠበቅ እንዳለብን ለመገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በምዕራፉ መጨረሻ ላይ እንደተዘገበው ይሄ ታሪክ ሲፈጸም አብራም የሰማንያ አምስት አመት ሰው ነበር። በዚህ መሰረት፦

   - እግዚአብሔር አብራምን ከአገሩ እንዲወጣ ካዘዘው ጊዜ አንስቶ ምን ያህል አመታት አልፈዋል?
   - ይህንን ያህል አመታት እግዚአብሔርን በትዕግስት ሲጠብቁ፣ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አለማግኘታቸው ሊያመጣ የሚችለው ምን ነገር ሊኖር ይችላል?

2. በቁ. 1 ላይ "ሦራ ግን ለአብራም ልጅ አልወለደችለትም ነበር" በማለት "ግን" የምትለውን አያያዥ ቃል ተጠቅሞ ም. 15 እና 16ን ሊያነጻጽር እንዳለ ያሳየናል። በዚህ መሰረት፦

   - እግዚአብሔር በም. 15 አብራም ተስፋ ቆርጦ በነበረ ጊዜ የሰጠው ተስፋ ምን ነበረ?
   - በም 16 ፡1 መሰረት፣ እግዚአብሔር የሰጠው ቃል እስከዚህኛው የሕይወታቸው እድሜ ድረስ አለመፈጸሙን የሚያሳየው እንዴት ነው?

3. ከቁ. 2-4 ባለው ክፍል መሰረት፦

   - ሦራ የእግዚአብሔን ተስፋ ከመጠራጠር አልፎ፣ ተስፋ መቁረጧን የሚያሳይህ ምን ነገር አለ?
   - አብራምስ ተስፋ እንደቆረጠ የሚያመላክተን ነገር ምንድን ነው?

4. አብራም እና ሦራ በእግዚአብሔር ተስፋ መቁረጣቸው ወደ ምን አይነት ሁኔታ ነው የመራቸው?

5. በቁ. 2 መሰረት ሦራ ለአብራም የሰጠችው መንፈሳዊ የሚመስል ምክር ምንድን ነው?

   - በአሁንስ ዘመን ሰዎች ጥፋታቸውን ለመደበቅ መንፈሳዊ አስመስለው ለማቅረብ ሲሞክሩ ይታያሉ ትላለህ? በምን መልኩ?

6. በቁ. 4 እና 5 መሰረት፣ ሦራ እና አብራም ተማክረው በፈጸሙት ስህተት፦

   - በሦራ እና በአጋር መካከል የተፈጠረው ችግር ምንድን ነው?
   - በሦራ እና በአብራም መካከል የተፈጠረው ችግር ምንድን ነው?

   - ዛሬስ እስከመጨረሻው ድረስ ታማኝ ሆኖ አለመጠበቅ በሕይወታችን ምን ሊያስከትል ይችላል?

7. በቁጥር 6 መሰረት፦

- አብራም ለሦራ የፈቀደላት ነገር ምንድን ነው? ይህስ በእግዚአብሔር ፊት መልካም ነው ትላለህ?
- ሦራስ በተፈቀደላት መሰረት በአጋር ያደረገችው ምንድን ነው?
- ይሔ ክፍል በቤተሰብ ውስጥ ያለውን ሰላም ኃጢአት እንዴት ሊያደፈርሰው እንደሚችል ያሳይሃል ወይ? ከሆነስ ምን ማድረግ ነው ያለብህ?

8. የአጋር ከከእመቤቷ መኮብለሏ በእነ አብራም ቤት ሊያመጣ የሚችለው ችግር ምንድን ነው? ሦራስ እንዳቀደችው ሆነላት ወይ?

9. ዛሬ በተማርነው መሰረት በተስፋ መቁረጥ የምትወስደው እርምጃ በሕይወትህ ሊያመጣ የሚችለው ችግር ምንድን ነው?

10. አይነት ስህተት ለመቆጠብ ምን ዓይነት እርምጃ እንድትወስድ ያስገነዝብሃል?

## ጥናት ሃያ ሁለት
## እግዚአብሔር ያያል

**የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ 16፡7-16**

**ዓላማ፦** የተጎዳንን እና የተበደልን በሚመስለን ጊዜ ሁሉ የሚያይ እና የሚፈርድ እግዚአብሔር እንዳለ አውቀን በተሰማራንበት መስክ ሁሉ በታማኝነት እንድናገለግል ማበረታታት።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ. 7 መሰረት የእግዚአብሔር መልእክ አጋርን ያገኛት የት ነው?
    - መልአኩስ አጋርን የጠራት ማን ብሎ ነው?
    - አጋር በራሷ ፈቃድ ኮብልላ ከባርነት ነጻ ለመውጣት ብትነሳም፣ እግዚአብሔር ግን ማን እንደሆነች ነው የሚያውቃት?
2. ባለፈው ጥናታችን መሰረት አጋር ከእመቤቷ እንድትኮበልል ያደረጋት ምክኒያት ምን ነበር?
3. በቁ 9 ላይ አጋር መበደሏን እና መገፋትዋን አይቶ መልአኩ ወደ እመቤቷ እና ወደ ጌታዋ እንድትመለስ ያዘዛት ለምን ይመስልሃል?
    - ምንም ብትገፋ እና ብትጨቆን፣ የአጋር ኮብልሎ መሄድ ትክክል ነው?
    - በ 1ኛ ጴጥ 2፡18-19 ባለው መሰረት በዚህ አይነት ስቃይ የሚያልፍ አገልጋይ ለጌታው መገዛት ያለበት እንዴት ነው?
4. ከላይ ባየነው መሰረት፣ መልአኩ አጋር ወደ ሦራ እንድትመለስ እና እንድትገዛ ያዘዛት ለምንድን ነው?
5. በቁ 10- 12 ባለው መሰረት፦
    - አጋር ከሦራ በታች ተመልሳ ስትገዛ እንደሚያደርግላት የሰጣት ተስፋ ምንድን ነው?
    - የተገፉትን እና የተጨቆኑትን እግዚአብሔር እንደሚያይ ይሔ ክፍል የሚያስረዳህ እንዴት ነው?
6. በቁ. 13 ላይ አጋር እግዚአብሔርን የጠራችው ማን ብላ ነው?
    - የስሙስ ትርጉም ምንድን ነው?
    - አጋር እግዚአብሔርን ለምን በዚህ ስም ጠራችው?
7. በቁ. 15- 16 መሰረት፣ አጋር ለሦራ ሄዳ በተገዛች ጊዜ ያደረገላት ምንድን ነው?
8. ይህ ክፍል የበላይ ለሆኑ ሰዎች በታማኝነት እና በታዛዥነት መገዛት በሕይወታችንን ስለሚያመጣው በረከት ምን ያስተምረናል?
9. ይህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር ባህርይ ያስተማረህ ምንድን ነው?

10. እግዚአብሔር ማየት ብቻ ሳይሆን መፍረዱን ማወቅህ ለወደፊቱ ችግርህ ምን እንድታደርግ ያስተምርሃል?

## ጥናት ሃያ ሶስት

## በእግዚአብሔር ተስፋ አይቆረጥም!

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ.17: 1-27

ዓላማ፡- የሕይወት ገጠመኞቻችን ምንም ያህል ተስፋ አስቆራጭ ቢሆኑም፣ በእግዚአብሔር ተስፋ እንደማይቆረጥ እና በእርሱ ታምነን እስከመጨረሻው መኖር እንዳለብን ማሳሰብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በምዕራፍ 16 የሆነውን እና በቁ.1 ላይ ያለውን በመደገፍ አብረሃም በምን ሁኔታ ውስጥ እያለ ነበር እግዚአብሔር የተገለጠለት?

2. እግዚአብሔር ለአብራም በተገለጠለት ጊዜ "እግዚአብሔር አብራምን" አለው እያለ በዚህ ክፍል የሚናገረው ስንት ጊዜ ነው? (ቁ. 2፣ 9፣ 15፣ 19 ተመልከቱ)።

3. በቁ. 1 ላይ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ንግግሩ፣ እኔ "ኤልሻዳይ ነኝ" በማለት ራሱን ለአብራም የገልጻል፣ በዚህ መሰረት፦

   - ኤልሻዳይ ምን ማለት ነው?
   - አብራም በዚህ ሁኔታ እያለ እግዚአብሔር ኤልሻዳይ መሆኑን መግለጽ ለምን አስፈለገው?

4. ከቁ.4-8 ባለው ክፍል እግዚአብሔር ለአብራም እንደገና ቃል ኪዳን ሲሰጥ እናያለን።

   - እግዚአብሔር የሰጠው ቃል ኪዳኖች ምንድን ናቸው?
   - እግዚአብሔር ለአብራም በዘፍ. 12፡1-5 ባለው ክፍል ላይ ከሰጠው ተስፋ የሚለይበት ነገር አለ ብለህ ታስባለህ?
   - እግዚአብሔር የአብራምን ስም የቀየረው ወደ ምንድን ነው፣ የስሙስ ትርጉም ምን ማለት ነው?

5. እግዚአብሔር አብርሃም የሰባ አምስት አመት ሰው ከነበረበት ጊዜ አንስቶ የዘጠና ዘጠኝ አመት ሰው እስከሚሆን ድረስ ከሚስቱ ልጅ አላገኘም።

   - አብርሃም ልጅ ሳያገኝ ተስፋ ብቻ ማግኘቱ በልቡ ሊያሳድር የሚችለው ምንድን ነው?
   - በቁ. 17 መሰረት የአብርሃም ምላሽ የሚያሳይህ ምንድን ነው?

6. ከቁ. 9-14 ባለው እግዚአብሔር፣ በሁለተኛው ንግግር የግርዘትን ስርአት ይሰጣል።

- መገረዝ ምንድን ነው? እንዲገረዙ የታዘዙት እነማን ናቸው?
- የመገረዝ ትዕዛዝስ ለምን አስፈለገ፣ ሰዎቹስ በመገረዛቸው የሚያሳዩት ምንድን ነው? (ቁ. 11 ተመልከቱ)።
- ዛሬ በአዲስ ኪዳን፣ አማኞች የእምነታቸው ምልክት እንዲሆን እንዲያደርጉት የታዘዙት ምን ነገር አለ?

7. እግዚአብሔር ከቁ. 15-18 ለአብርሃም በሰጠው ንግግር ያለው ነገር ምንድን ነው?

- እግዚአብሔር የሦራ ስም እንዲቀየር ያለው ለምንድን ነው?
- አብርሃም እግዚአብሔርን ከማመን እንዲጠራጠር ሊያደርገው የሚችል ምን ምን ነገሮች አሉ?
- በቁ. 17 -18 ባለው አብርሃም ተስፋ መቁረጡን የሚያሳይ ምን ነገር አለ?

8. ከቁ.19- 21 ባለው፣ ለአብርሃም ተስፋ መቁረጥ እግዚአብሔር የሰጠው የተስፋ ቃል ምንድን ነው?

- በቁ. 19 እግዚአብሔር "በእውነት" ብሎ መናገር ለምን ያስፈለገው ይመስልሃል?
- እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውስ ቀጠሮ ለእስከመቼ ነው? ቀጠሮ መስጠትስ ለምን አስፈለገው?

9. ከቁ. 22-27 ባለው ክፍል አብርሃም እግዚአብሔር ለሰጠው ንግግር መልስ ይሰጣል። በዚህ መሰረት፣

- አብርሃም ለእግዚአብሔር ምላሽ የሰጠው በምንድን ነው?
- አብርሃም ተስፋ ቆርጦ በነበረበት ሰአት፣ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ማድረጉ የሚያስገነዝበን ምንድን ነው?
- አብርሃም የነበረበት ሁኔታ ምንም ከባድ እና ተስፋ አስቆራጭ ቢሆንም፣ ከዚህ ሁሉ በኃላ በእግዚአብሔር ማመኑን እና መበርታቱን በሮሜ 4፥ 18-21 ያለው ቃል እንዴት ያሳየናል?
- አንተስ ተስፋ ስትቆርጥ እና ኃጢአትን አድርገህ ለማጥፋት ስትፈተን ማድረግ ስላለብህ ነገር የሚያሳስብህ ምንድን ነው?

## ጥናት ሃያ አራት
## ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም!

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 18፡1-15

ዓላማ፦ የምናልፍባቸው ከባድ የሕይወት ገጠመኞቻችን የእግዚአብሔርን ችሎታ እንድንጠራጠር እንኳን ቢያደርጉንም እግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ከቶ እንደሌለ ማስገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በዘፍ 17፡22-27 ባለው ጥናታችን የተመለከትነው ነገር ምንድን ነው?
   - በቁ. 24 መሰረት አብርሃም እግዚአብሔር ያዘዘውን ነገር የፈጸመው መቼ ነው?
   - በዘፍ. 18፡1 መሰረት በዛሬው ጥናታችን ያነበብነው ታሪክ የተፈጸመው መቼ ነው ማለት ነው?
   - ባለፈው ጥናታችን ላይ  አብርሃም እግዚአብሔር ያዘዘውን ሲፈጽም
     - እግዚአብሔር ለአብርሃም ያደረገለት ነገር ምንድን ነው?
     - ይህስ ስለመታዘዝ ምን ያስተምርሃል?

2. በቁ. 2-5 ባለው ክፍል ውስጥ የሆነው ነገር ምንድን ነው?
   - ከቁ. 3-5 ባለው ክፍል ላይ በነጠላ እና በብዙ ቁጥር እየለዋወጠ የተናገራቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
   - በነጠላ የሚናገረው እነማንን ነው፤ በብዙ ቁጥርስ?
   - በምዕራፍ 19፡1 መሰረት ለአብርሃም ከተገለጡት ሶስት ሰዎች ውስጥ ሁለቱ ምን ነበሩ?
   - ከሶስቱ አንደኛው ከአብርሃም ጋር እየደጋገመ የሚነጋገረው ማን ነው? (ቁ. 10፣ 13፣ 17፣ እና 20ን ይመልከቱ)።
   - እግዚአብሔር ለአብርሃም የተገለጠለት እንዴት ነው?

3. አብርሃም በቁ. 3 ላይ በተናገረው መሰረት በሰው ሁኔታ የተገለጠለት እግዚአብሔር እንደሆነ ያውቅ ነበረ ብለህ ታስባለህ?

4. በቁ. 5 መሰረት ለአብርሃም የተገለጡለት መላዕክት እና እግዚአብሔር ልክ እንደ ሰው መስተንግዶ ሲቅርብላቸው ለመስተናገድ መፍቀዳቸው፣ ስለ እግዚአብሔር ምን ያስተምርሃል?

   ለአስጠኚው፦ እግዚአብሔር ታላቅ ሆኖ ሳለ ትሁት ሆኖ ልክ እንደ ሰው ይመላለሳል። እግዚአብሔር ታላቅ ቢሆንም ሰው ፍቅሩን በሚገልጥለት መንገድ ሁሉ ለመገልገል ፈቃደኛ ነው።

5. አብርሃም ከቁ. 6-8 ባለው ክፍል ለእግዚአብሔር ያደረገው መስተንግዶ ምንድን ነው?

6. ከቁ. 9-10 ባለው እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ያደረገው ንግግር እና የሰጠው ተስፋ ምንድን ነው?
    - በቁ. 10 ላይ እግዚአብሔር ለአብርሃም በቀጠሮ የሰጠው ተስፋ በዚሁ ቀን ድጋሚ ሲነገረው ይሔ ስንተኛ ጊዜ ነው? (ዘፍ. 17፡21 እንዲሁም 18፡14 ተመልከት)።

7. በቁ. 11-12 ባለው መሰረት፣ በሣራ አይን እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ እንዳይሆን ሊያደርጉ የሚችሉ ምን ነገሮች አሉ?

8. በቁ.13 መሰረት እግዚአብሔር አብርሃምን የጠየቃቸው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?
    - በቁ. 12 ላይ ሣራ በድንኳን ውስጥ ሆና በልቧ የሳቀችውን ሳቅ እግዚአብሔር እንዴት አወቀ?
    - እግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት እና በልባችን እንኳን የምናስበውን እንደሚያውቅ ማወቅህ ዛሬ በሕይወትህ ሊያመጣ የሚገባው ለውጥ ምንድን ነው ትላለህ?

9. በቁ. 14 ላይ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ምንድን ነው?

10. በዛሬው ትምህርት ስለ እግዚአብሔር የተማርከውን አስረዳ።

## ጥናት ሃያ ስድስት

## ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም!

**የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 19፡ 1-38**

**ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ጽድቅን የሚወድ፣ ኃጢአትን የሚቀጣ መሆኑን በማወቅ፣ ክፋት እና ጥፋት በበዛበት ዓለም ውስጥ፣ ተለይቶ እግዚአብሔርን በመፍራት እንድንኖር ማበረታታት።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ. 1-2 ባለው መሰረት ሎጥ ወደ ከተማ የገቡትን መላዕክት ወደ ቤቱ እንዲገቡ እና እንዲስተናገዱ መለመኑ፣ ስለ ሎጥ ምን ያስተምረናል?

- ሎጥ ወደ ቤቱ ያስገባቸው ሰዎች መላዕክት እንደሆኑ እውቀት ነበረውን?

2. መላዕክቱ በውጭ እናድራለን ሲሉ እቤቱ እንዲገቡ ሎጥ የለመናቸው ለምን ይመስልሃል?
   - በሎጥ አስተሳሰብ፣እንግዶቹ በውጭ ቢያድሩ ሊገጥማቸው የሚችለው ምንድነው?
3. እቤቱ ለመጡት የከተማው ሰዎች ሎጥ የሰጠው ምላሽ ምንድን ነው? (ቁ. 7-8)።
   - ይህስ ስለ ሎጥ ሕይወት የሚያሳይህ ነገር ምንድን ነው?
4. 2ኛ ጴጥ 2፡7-8 ያለውን በማንበብ፣ ሎጥ ምን አይነት ሰው ነበር? የሚኖረውስ በምን ዓይነት ሰዎች መካከል ነበር?
   - በአከባቢው የነበሩት ሰዎች ዕለት ዕለት ዓመጻ እያየ መኖሩ ሎጥን ምን አድርጎታል?
5. በዘፍ 19፡1-11 መሠረት የሰዶም ሰዎች ምን አይነት ሰዎች ነበሩ ትላለህ?
   - ከሎጥ ባህርይ ጋር የሚቃረኑ ስንት ባህሪያትን ልትጠቅስ ትችላለህ?
   - ሎጥ ወንድ ያላወቃቸውን ልጆቹን ሊሰጣቸው ፈልጎ ፈቃደኛ ለምን አልሆኑም?
   - ዛሬስ የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት "ግብረ ሰዶም" እያልን የምንጠራው ለምንድነው?
6. እግዚአብሔር ወደ ሎጥ ቤት በመጡት ሰዎች ላይ እና ለሎጥ ያደረገው ምንድን ነው (ቁ. 10-11)
   - በከተማይቱስ ላይ?
7. ሎጥ እግዚአብሔርን እየፈራ መኖሩ ያተፈው ነገር ምንድን ነው?
8. በቁ. 12፣ እንዲሁም ከ18-22 ባለው ክፍል እግዚአብሔር ለሎጥ ምህረቱን የገለጸው እንዴት ነው?
9. በዚህ ዘመን ግብረ ሰዶም እየጨመረ እና እንደትንሽ ነገር መቆጠሩ፣ ምን ያሳስብሃል?
10. በ2ኛ ጴጥ 2፡ 7-8 ባነበብነው መሰረት ሎጥ በሰዶም ሰዎች ኃጢአት አልተሳበም።
    - ከቁ 30-38 ያለውን በመመልከት ስለ ሎጥ ልጆች ምን ትላለህ?
    - እንደዚህ ያለውን ኃጢአት የተማሩት ከየት ነው ትላለህ?

11. የሰዶምን ሰዎች እግዚአብሔር ሲያጠፋ፣ የሎጥን ልጆች የተዋቸው ለምን ይመስልሃል?

- ይህስ እግዚአብሔር ለሎጥ ምህረት ማድረጉን ምን ያህል ያሳያል ትላለህ?

12. ከዛሬው ትምህርት እግዚአብሔርን ስለመፍራት ምን ትማራለህ?

13. ስለሌሎችስ ኃጢአት ምን ማደርግ እንዳለብህ ያስተምርሃል?

14. የኃጢአትስ ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ያስተምርሃል?

## ጥናት ሃያ ሰባት
## በቅንነት መመላለስ

**የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ 20፡1-18**

**መግቢያ፦** ብዙ ጊዜ በቅንነት መኖር እንደ ሞኝነት ስለሚቆጠር ሰዎች “አራዳ” መሆንን ይመርጣሉ። በእርግጥም በኑሮአችን ብልህ እና አስተዋይ መሆን መልካም ነገር መሆኑ የማይካድ ቢሆንም ከሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ግን ቅኖች እንድንሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይመክራል። ከዚህም ባሻገር እግዚአብሔር በቅንነት የሚመላለሱትን ከክፉ እንደሚጠብቃቸው ይነግረናል።

**ዓላማ፦** የእግዚአብሔር ቃል በሕይወታችን እንዲኖረን ከሚመክረን ባህርያት አንዱ ቅንነት መሆኑን በማወቅ፣ በቅንነት እንድንመላለስ ማበረታታት።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ 1-2 ባለው መሰረት አብርሃም፣ በጌሬራ ላሉት ሰዎች፣ ሳራን ማን እንደሆነች አድርጎ ነው ያስተዋወቀው?

2. በቁ. 10-11 ባለው መሰረት፣ አብርሃም ሳራን “ሚስቴ ናት” በማለት ፈንታ እህቴ ናት ብሎ ያስተዋወቀው ለምንድን ነው?

3. አብርሃም ሳራን እህቴ ናት በማለቱ ዋሽቶአል ወይ? (ቁ.12ን ተመልከቱ)
    - ሳራ የአብርሃም እህት መሆኗ እርግጥ ቢሆንም፣ ሚስቱ መሆኗን አለመናገሩ ትክክል ነው ብለህ ታስባለህ ወይ?

4. አብርሃም ሚስቱ እንደሆነች ሰዎች ቢያውቁ እንደሚገድሉት ማሰቡ ተገቢ ነው ወይ?
    - ይህስ ፍራቻ እግዚአብሔር በዘፍ 12፡1-5 ባለው ክፍል እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን የተስፋ ቃል መዘንጋቱንና በእግዚአብሔር አለመተማመኑን ምን ያህል ያሳያል?
    - ከዚህም በላይ ከዚህ ቀደም በግብፅ አገር ተመሳሳይ ነገር ማድረጉን በዘፍ 12፡10-20 ተመልከቱ።

5. እስካሁን ከተመለከትነው በመነሳት፣ የጌሬራ ንጉስ አቢሜሌክ በቁ.2 መሰረት ሳራን ለሚስትነት መውሰዱ ጥፋት ነው ወይ?

6. በቁ. 4-5 ባለው መሰረት አቢሜሌክ “በልቤ ቅንነት እና በእጄ ንጹህነት ይህንን አደረኩ” ሲል ምን ማለቱ ነው?
    - ቅንነትስ ምን ማለት ነው?

7. በቁ. 6 መሰረት እግዚአብሔር አቢሜሌክ ኃጢአት እንዳያደርግ የከለከለው ለምንድን ነው?
    - ይህስ ለቅን ሰዎች እግዚአብሔር የሚጠነቀቅ መሆኑን ምን ያህል ያሳያል?
    - ስለ እግዚአብሔር ቅን ፈራጅነት ምን ያስተምራል?

8. አቢሜሌክ በቁ. 14-16 ባለው መሰረት ሳራን ለአብርሃም ከመመለስ ሌላ ያደረገለት ሶስት ነገሮች ምንድን ናቸው? ይህስ ስለ አቢሜሌክ የሚነግረን ነገር ምንድን ነው?

9. በዘፍ 12 ላይ አብርሃም ተመሳሳይ ጥፋት ባጠፋ ጊዜ፣ ፈርዖን ለአብርሃም ከግብጽ ምድር እንዳስወጣቸው ይታወሳል (ዘፍ 12፥18-20 ይመልከቱ)።

- በዚህ ክፍል አቢሜሌክ ለአብርሃም ያደረገለትን በማወዳደር ስለ አቢሜሌክ መልካምነት ምን ትማራለህ?

10. ቅኑ አቢሜሌክ እግዚአብሔር እንዳዘዘው እና ከታዘዘውም በላይ ደግ ስራ በመስራቱ እግዚአብሔር ያደረገለት ምንድን ነው? ከቁ. 17-18

11. ዛሬ ባየነው መሰረት፣ ስለ ቅንነት ምን እንማራለን? እንዴትስ በቅንነት ልንመላለስ እንችላለን? ከዚህም በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ በምሳ 11፥3 ላይ ስለ ቅንነት የሚናገረውን ተመልከት።

## ጥናት ሃያ ስምንት
## የእግዚአብሔር ታማኝነት

**የምንባብ ክፍል፦** ዘፍ 21፡1-34

**መግቢያ፦** መጽሐፍ ቅዱስ አጽንቶ ከሚናገራቸው የእግዚአብሔር ባህሪያት አንዱ የእግዚአብሔር ታማኝነት ነው። እግዚአብሔር ተስፋ ከሰጠ ወይንምቃል ከገባ፣ ያለውን ነገር በታማኝነት ይፈጽማል። ለዚህም ነው በአንድ ሥፍራ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር "የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና" የሚለው (ዕብ. 10፡23)። በዛሬው ጥናታችን እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ እንዴት እንደፈጸመ በመመልከት ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት እናጠናለን።

**ዓላማ፦** እግዚአብሔር ለቃሉ የታመነ መልካም አምላክ መሆኑን በማወቅ፣ በዕለት ተዕለት ኑሮአችን እግዚአብሔርን አምነን እና በእርሱ ተማምነን እንድንኖር ማበረታታት።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ 1 ላይ ክፍሉ ሲጀምር "እግዚአብሔር እንደተናገርው ሳራን አሰበ" ይላል። እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ምንድን ነበረ? (ዘፍ 18፡9-10 ያለውን ያወዳድሩ)።

2. በምዕራፉ የመጀመሪያ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ብቻ ሶስት ጊዜ ደጋግሞ እግዚአብሔር መናገሩን እና እግዚአብሔር የገባውን ቃል መፈጸሙን ይናገራል።

   - በዚህ ሊያሳስበን የፈለገው ነገር ምን ይመስልሃል?

3. በዘፍ 18፡11-12 ባለው ክፍል መሰረት እግዚአብሔር ለሳራ እና ለአብርሃም ልጅ ሊሰጣቸው ቃል በገባ ጊዜ፣ ሳራ ባለማመን እንድትስቅ ያደረጋት ነገር ምንድን ነው?

4. ምንም እንኳን በሰው የተፈጥሮ ሁኔታ መሰረት አብርሃም እና ሳራ ልጅ ለመውለድ የማይችሉበት ሁኔታ ላይ ቢሆኑም፣ አብርሃም ግን እግዚአብሔርን በእምነት እንዲጠብቅ ያደረገው ነገር ምንድን ነው? (ሮሜ 4፡19-21 ያለውን ተመልከት።)

5. እግዚአብሔር በሰው አቅምና ሁኔታ ሊደረግ የማይችል ነገር አደርጋለሁ ብሎ ቃል ሲገባ እንድናምን እና ተስፋ እንድናደርገው የሚያደርገን ነገር ምንድን ነው? (ዘፍ 18፡14 ላይ እግዚአብሔር ለሳራ የሰጣትን መልስ ያወዳድሩ)።

6. በቁ 8-13 ባለው መሰረት፣ ሳራ እንዳዘዘችው፣ አጋርን እና እስማኤልን ለማስወጣት አብርሃም ባመነታበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር አብርሃምን ያዘዘው እና የሰጠው የተስፋ ቃል ምን ነበር?

7. እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል ከሰማ በኃላ አብርሃም ልጁን ለማሰናበት ያልከበደው ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?

8. እግዚአብሔርስ ስለ እስማኤል የገባውን ቃል ፈጽሟል ትላለህ?

   - በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እግዚአብሔር ስለ እስማኤል በሰጠው ተስፋ ታማኝ እንደሆነ የሚያሳይ ክፍል አለ ወይ? በሌላስ ክፍል? (ዘፍ 25፡12-18 ያለውን ያወዳድሩ)።

9. በም 21፡22-34 ባለው ክፍል የአገሩ ንጉስ አብርሃምን በመፍራት ከአብርሃም ግር ቃል ኪዳን እንዳደረገ ይነግረናል።

   - ንጉሱ የሠራዊት አለቃውን አስከትሎ መጥቶ ከአብርሃም ጋር ቃል እንዲገባ ያደረገው በአብርሃም ሕይወት ምን ስላየ ነው?

10. በዘፍ 15፡1-2 ባለው ክፍል እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ምንድን ነበር?

- የአቢሜሌክ አብርሃምን መፍራት ከዚህ የተስፋ ቃል ጋር የሚያገናኘው ነገር ምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ለቃሉ ታማኝ ሆኗልን?

11. እንደገና ሮሜ 4፡19-21 ያለውን ክፍል በመመልከት በእግዚአብሔር የተስፋ ቃልና በእምነት መካከል ያለው ዝምድና ምንድን ነው ትላለህ።

    - ከዚህም ባሻገር ዕብ 11፡1-3 ያለውን ተመልከቱ።

12. በዛሬው ጥናታችን መሰረት በሕይወታችን፣ በስራችን፣ እንዲሁም በአገልግሎታችንና በምንሰማራበት በየትኛውም መስክ ሳንፈራ ለእግዚአብሔር እንደ እግዚአብሔር ቃል እንድንኖር ሊያበረታታን የሚገባው ነገር ምንድን ነው?

## ጥናት ሃያ ዘጠኝ

## በፈተና መጽናት

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ 22፡1-24

**መግቢያ፦** በኃጢአት ሊጥለን እና ሊያጠፋን በሚመጣ ፈተና ውስጥ እንዳንገባ ተግተን ልንጸልይ እንደሚገባን ግልጽ ቢሆንም (ማቴ 26፡31)፣ ሊያበረታንና የተፈተነ ማንነት እንዲኖረን ሊያጠራን ከሚመጣ ፈተና ግን በጸሎትም ይሁን በሌላ መንገድ ማምለጥ አንችልም፤

**ዓላማ፦** እግዚአብሔር ለቃሉ የታመነ መልካም አምላክ መሆኑን በማወቅ፣ በዕለት ተዕለት ኑሮአችን እግዚአብሔርን አምነን እና በእርሱ ተማምነን እንድንኖር ማበረታታት።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ 1 ላይ ክፍሉ ሲጀምር "እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው" ይላል። በውኑ እግዚአብሔር ሰውን ይፈትናል? ለምን?

2. በያዕ. 1፡3 "ማንም ሲፈተን፦ በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም።" ይላል።

   - ይህ ክፍል በዘፍ 22፡1 ላይ ካለው ክፍል ጋር አይጋጭም ወይ? የማይጋጭ ከሆነ፣ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

3. በያዕ. 1፡14 መሰረት ሰው የሚፈተነው ምን ሲሆን ነው?

   - በቁ. 15 መሰረት እንዲህ ያለው ፈተና የሚያስከትለው ምንድን ነው?

   - በእንደዚህ አይነቱስ ፈተና ሰው እንዳይወድቅ ሊያደርጋቸው ከሚገቡት ነገሮች አንዱ ምንድን ነው? (ማቴ 26፡31 አንዱ መልስ ሊሆን እንደሚችል አስብ)።

4. በዘፍ 22፡2 መሰረት እግዚአብሔር አብርሃምን የፈተነው እንዴት ነው?

   - አብርሃምስ የሰጠው መልስ ምንድን ነው

5. አብርሃም ልጁን ሊሰዋ ተነስቶ ሳለ፣ በቁ 5 ላይ ለአገልጋዮቹ፣ እኔና ልጄ ሰግደን እንመለሳለን ብሎ ሲነግራቸው እናያለን።

   - አብርሃም ልጁን ሳይሰዋ ለመመለስ አስቦ ነበር ማለት ነው? በቁ. 8 ላይ አብርሃም ያለውን አወዳድር።

6. በዘፍ 21፡12 ላይ እግዚአብሔር አብርሃምን "በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል" ሀሎት ሳለ፣ በዚህ ክፍል ላይ ግን ይስሐቅን መስዋዕት እንዲያደርገው እግዚአብሔር ለአብርሃም ጥያቄ አቅርቦለታል።

   - "እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርስ በእርሱ ይጋጫል" ሳይል አብርሃም እንዲታዘዝ ያደረገው ነገር ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? (ዕብ 11፡17-19 ያለውን ተመልከት)።

7. በቁ. 10-12፣ አብርሃም ልጁን ለመሰዋት እጁን ባነሳበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር መልአክ ለአብርሃም ያለው ምንድን ነው?

   - በዚህ ክፍልስ መሰረት እግዚአብሔር አብርሃምን የፈተነው ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?

8. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ባየነው መሰረት አብርሃም ከቤተሰቡ እና ከእግዚአብሔር በይበልጥ የሚወደው ማንን ነው?

- ይህስ በዘዳ 6፡5 ላይ እንደተጻፈው እግዚአብሔር ከአብርሃም የሚፈልግበትን ማድረጉን ምን ያህል ያሳያል?

9. በቁ 13 የሆነው ነገር ምንድን ነው?

    - አብርሃም በቁ. 8 ላይ ከነገረው ነገር ጋር እንዴት ይሔዳል?

10. አብርሃም ለእግዚአብሔር መስዋዕትን ካቀረበ በኋላ መልአክ እንደገና ጠርቶት ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ምንድን ነው (ቁ. 16-18)?

11. በዚህ ምዕራፍ ላይ አብርሃም ከመታዘዝ ሌላ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘበት ምን ምን ባህሪያቶች ታያለህ?

12. በዚህ ክፍል መሰረት አብርሃም እግዚአብሔር ያቀረበለትን ፈተና አልፎአል ወይ?

13. ዛሬ ከተማርነው በመነሳት፣ እግዚአብሔር ሰውን ለምን ይፈትናል ብለህ ታስባለህ? በፈተናስ ለማለፍ ከእኛ የሚጠበቅብን ምንድን ነው?

14. በእንደዚህ አይነቱ ፈተና ሰው ተፈትኖ ሲያልፍ የሚጥመው ነገር ምንድን ነው?

    - አብርሃም ፈተናውን ካለፈ በኋላ የሆነለትን እና በያዕ. 5፡11 ላይ ስለ እዮብ የተጻፈውን አወዳድር።

## ጥናት ሠላሳ
## በትህትና የሚገኝ ሞገስ

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ 23፡1-20

መግቢያ፦ ጌታ የሰማይ እና የምድር ገዢ ሆኖ ሳለ፣ በትህትና ራሱን ዝቅ አድርጎ እንደመጣ እንዲሁም የደቀመዛሙርትን እግር ዝቅ ብሎ እንዳጠበ ሁሉ፣ ክርስቲያኖችም እንዲሁ ራስን ዝቅ የሚያደርጉ እና ትህትናን የተሞላ ልንሆን እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ትህትና ለብዙዎች የውርደት ምልክት ቢመስልም፣ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ግን፣ ትህትና የመክበሪያ እና በእግዚአብሔር እንዲሁም በሰው ፊት ሞገስን የማትረፊያ መንገድ ነው። በዛሬው ጥናታችን ትሁት መሆን እንዴት ሞገስን እንደሚያስገኝ እንመለከታለን።

ዓላማ፦ ያለንን የኑሮ ሁኔታ ምንም አይነት መልክ ቢኖረው፣ ከሰዎች ጋርም ሆነ ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረን ግንኙነት በትህትና እንድንመላለስ ማበረታታት።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ. 1-2 ባለው መሰረት የተፈጠረው ነገር ምንድን ነው? ነገሩ የተፈጠረበት ቦታ የት ነው?

2. ይህ ሁኔታ በተፈጠረበት በዚህ ቦታ፣ ከአብርሃም ሌላ በቦታው ይኖሩ የነበሩት ሰዎች እነማን ናቸው? (ቁ. 3፣ 5፣ 7፣ 10ን ይመልከቱ)።

3. በዘፍ 15፡ 18-21 ባለው ክፍል መሰረት፣ ይህ የኬጢ ልጆች (ኬጢያዊያን) የሚኖሩበትን ስፍራ እግዚአብሔር የሰጠው ለማን ነው?

4. በቁ. 6 መሰረት፣ አብርሃም በኬጢያዊያን ፊት የነበረው ተቀባይነት ምን ይመስል ነበር?

   - ይህስ እግዚአብሔር ለአብርሃም በዘፍ 12፡1-3 ላይ ከገባለት ቃል ኪዳን ጋር እንዴት ይያያዛል?

5. አብርሃም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያለው፣ በኬጢያዊያንም ዘንድ የተከበረ ከመሆኑ ሌላ፣ ኬጢያዊያንም በጊዜው እየኖሩ ያለውን ቦታ እግዚአብሔር ለዘሩ ሰጥቶታል።

   - አብርሃም ምንም ታላቅ ሰው ቢሆንም፣ በኬጢያዊያን ልጆች መካከል ግን ይኖር የነበረው እንዴት ባለ መንፈስ ነበር?

6. በቁ. 3 "አብርሃም ከሬሳው አጠገብ ተነሳ ለኬጢም ልጆች እንዲህ ሲል ተናገረ"፣ ቁ. 7 "አብርሃም ተነሳ፣ ለምድሩ ሕዝብም፣ ለኬጢ ልጆች፣ ሰገደ።"፣ ቁ. 12 "አብርሃምም በአገሩ ሰዎች ፊት ሰገደ... እንዲህም ሲል ተናገረ" በሚሉ ዓርፍተ ነገሮች መሰረት አብርሃም በዙሪያው ካሉት ሰዎች ጋር ይነጋገር የነበረው እንዴት ባለ ሁኔታ ነበር?

7. አብርሃም በተሰበረ እና ትሁት በሆነ መንፈስ የኬጢ ልጆችን ያነጋግራቸው በነበረ ጊዜ ይመልሱለት የነበረው እንዴት ባለ መንፈስ ነበር?

   - አብርሃም በመካከላቸው እንግዳ ሆኖ ሳለ እንደዚህ እንዲከበር ያደረገው ምንድን ነው ትላለህ? (በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ በምሳ 3፡34 እንዲሁም በያዕ 4፡6 ላይ የተጻፈውን ያገናዝቡ)።

8. በቁ. 8-9 ባለው ክፍል መሰረት፣ አብርሃም ኤፍሮን ከተባለው ኬጢያዊ እንዲሸጥለት የጠየቀው ምንድን ነው?

   - በቁ 11 ላይስ ኤፍሮን ለአብርሃም ሊሰጠው የወደደው ምንድን ነው? (አብርሃም የተሰጠው መልስ የተጠየቀውን ያህል ነው ወይስ በላይ?)

- በዚሁ ክፍል አብርሃም የጠየቀው የመቃብር ቦታ እንዲሸጥለት ሆኖ ሳለ፣ ኤፍሮን ግን እንዲሁ በነፃ ሊሰጠው እንዴት ሊያስብ ቻለ ብለህ ትገምታለህ?)

9. ከቁ. 13-16 ባለው ክፍል መሰረት አብርሃም በነጻ ሊወስደው የሚችለውን እንዲሁም እግዚአብሔር ለዘሩ በነጻ ሊሰጥ ቃል የገባለትን ቦታ በገንዘብ የወሰደው ለምን ይመስልሃል?

10. በቁ. 4 ላይ አብርሃም የጠየቀውን እና ከቁ. 17-18 ባለው ክፍል መሰረት አብርሃም ያገኘውን ቦታ አወዳድር። አብርሃም ከጠየቀው በላይ አግኝቶአል ትላለህ?

11. በዚህ ምዕራፍ መሰረት አብርሃም በፍጹም ትህትና በመመላለሱ አተረፈ ወይንስ ከሰረ? ትርፉስ መሬት ማግኘት ብቻ ነው ወይንስ ሌላ ያተረፈው ነገር አለ ትላለህ?

12. ዛሬስ በአንተ ሕይወት እንዲህ ያለውን ትሁት ልብ እና መንፈስ እንዴት ልትለማመደው ትችላለህ?

## ጥናት ሠላሳ አንድ
## መንገድን ለእግዚአብሔር አደራ የመስጠት በረከት

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 24፡ 1-67

**መግቢያ፦** ብዙ ጊዜ ጠዋት ከእንቅልፍ ስንነሳ፣ የቀን ስራችንን ስንጀምር፣ ወይንም አዳዲስ ምዕራፎችን በሕይወታችን ስንጀምር፣ ነገሮቻችንን ሁሉ ለእግዚአብሔር አደራ መስጠት እንዘነጋለን። ሆኖም ግን፣ ሁልጊዜ የምንጀምረውን የትኛውንም ጎዳና ለእግዚአብሔር አደራ መስጠት መልካም ነው፣ ለጅማሬአችን ስኬትን መስጠትና ፍጻሜን ማበጀት በእግዚአብሔር እጅ ነውና። በዛሬው ጥናታችን መንገዳችንን ለእግዚአብሔር የመስጠትን በረከት እናያለን።

**ዓላማ፦** በሕይወት ጎዳናችን ሁሉ ጅማሬአችንን ለእግዝአብሔር እንድንሰጥ እና እግዚአብሔርን እንድናስቀድም ማበረታታት።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቁ. 1-4 ባለው ክፍል፣ አብርሃም ለሎው የሰጠው ትዕዛዝ ምንድን ነው?

2. አብርሃም ልጁ ይስሐቅ በከንዓን ያሉትን ሴቶች እንዳያገባ የፈለገው ለምንድን ነው?

- ይስሐቅ አብርሃም ወዳደገበት አገር እንዳይመለስስ የፈለገው ለምድን ነው? (ቁ.7ን ያገናዝቡ)።

3. የአብርሃም ሎሌ እንዲሄድ ወደ ታዘዘበት ቦታ ሲደርስ በመጀመሪያ ያደረገው ነገር ምንድን ነው? (ቁ. 12 ን ያገናዝቡ)። ለምን እንደዚያ ያደረገስ ይመስልሃል?

4. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአብርሃም ሎሌ፣ ለጉዞው መሳካትን ሊሰጠው የሚችለው እግዚአብሄር ብቻ እንደሆነ መረዳቱን የሚያሳዩ ምን ምን ነገሮች አሉ? (በቁ.12፣ 21፣ 27፣ 44፣ 48 ላይ ሎሌው የተናገራቸውን እና ያደረጋቸውን ነገሮች አስተውል)።

5. ሎሌው እንደለመነው፣ እግዚአብሔር ያዘጋጃት ሴት (ርብቃ) ሎሌውን እና ግመልቹን ውሃ አጠጥታለች።

- በቁ. 28-32 እንዲሁም በቁ. 50-58 ባለው መሰረት እግዚአብሔር መንገዱን እንዳቀናለት የሚያሳዩ ምን ነገሮች አሉ?

6. በምሳ 3፡5-6 እንዲሁም በምሳ16፡3 መሰረት ሰው ስራውና መንግዱ እንዲቀናለት ሊያደርጋቸው ከሚገቡት ነገሮች አንዱ ምንድን ነው?

7. በቁ. 7 እንዲሁም በ ቁ. 40 መሰረት እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ለመፈጸም ሲል ለይስሐቅ የምትሆነውን ሴት ለማምጣት እና ለመልዕክተኛው ስኬትን ለመስጠት እግዚአብሔር ያደረገው ምንድን ነው?

8. በቁ. 26 እና 52 መሰረት ሎሌው እግዚአብሔር መንገዱን እንዳቀናለት ባወቀ ጊዜ ያደረገው ምንድን ነው?

- በዚሁ መሰረት እግዚአብሔር ነግሮችን የሚያደርገውና ለእኛም መሳካትን የሚሰጠን ለምንድን ነው ትላለህ?

9. እግዚአብሔር የሎሌውን መንገድ በማቅናቱ፣ ለአብርሃም እና ለልጁ የመጣው በረከት ምንድን ነው? (61-67 ያለውን አገናዝቡ)።

10. ዛሬ ባየነው መሰረት፣ በሕይወት መንገዳችን ለእግዚአብሔር አሳልፈን ልንሰጣቸው የምንችላቸው ምን ነገሮች አሉ?

### መደምደሚያ

የእግዚአብሔር ቃል "በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፣ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል።" (ምሳ 3፡5-6) ይላል። በዚህም መሰረት ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ታምነን እቅዳችንን፣ ስራችንን እንዲሁም መንገዳችንን ሁሉ ለእግዚአብሔር አደራ ሰጥቶ መጀመር መልካም ነው። እግዚአብሔርም በእውነት ታምነውበት መንገዳቸውን አደራ ለሚሰጡት እርሱ ስኬትን ይሰጣል።

## ጥናት ሠላሳ ሁለት
## ቃሉን የሚጠብቅ አምላክ

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 25:1-34

**መግቢያ፦** እግዚአብሔር እንደ ሰው አይደለም! ቆይቶም ይሁን በቶሎ ለሰው የሰጠውን የተስፋ ቃል በእርግጥ ይፈጽማል። በሰው ዘንድ ቃልን ማፍረስ የተለመደ ከመሆኑም በላይ፣ ሰው ቃሉን ለመፈጸም ሊያበቃው የሚችል ሙሉ ጉልበት የለውም። አንዳንዴ ሰው ታማኝ መሆን እንኳ ቢፈልግ ግን ነገሮች ከአቅሙ በላይ ይሆኑና ታማኝ ሳይሆን ይቀራል። በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ቃል ማፍረስ ከቶ የማይታሰብ ከመሆኑ በላይ፣ቃሉን ከመፈጸም ሊያግደው የሚችል ነገር የለም፤ ሁሉ በእርሱ ዘንድ ይቻላልና።

**ዓላማ፦** እግዚአብሔር በቃሉ የማይታማ ታማኝ አምላክ መሆኑን በመረዳት፣ በእርሱ ላይ ከሌላው ጊዜ ሁሉ የበለጠ እንድንደገፍበት ለማበረታታት።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ለመወያየት እንዲያመቸን የሚከተሉትን ሃሳቦች ለመከለስ እንሞክር
   - አብርሃምን እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሲጠራው የስንት አመት ሰው ነበር (ዘፍ 12፡4)?
   - እግዚአብሔር አብርሃምን በጠራው ጊዜ የሰጠው የተስፋ ቃላቶች ምን ምን ነበሩ (ዘፍ 12፡1-3)?
2. በዛሬው የንባብ ክፍላችን መሰረት፣ ላይ አብርሃም ሲሞት የስንት አመት ሰው ሆኖ ነው የሞተው? ቁ. 7ን አገናዝቡ።
   - በዚህ መሰረት ከዘፍ 12 -25 ባሉት ምዕራፎች ውስጥ የምናገኘው የአብርሃም ታሪክ የስንት አመት ታሪክ ነው?
3. ከቁ 1-4 የተጠቀሱት አብርሃም ከኬጡራ የወልዳቸው ልጆችና የልጅ-ልጆች እንነማን ነበሩ?
4. በቁ 5 እና 6 ላይ አብርሃም ያደረገው ነገር ምንድን ነው?
   - ውርስና ስጦታ የሚለውን ሃሳብ ስትመለከት/ከች በውራሹና በስጦታ ተቀባዮቹ መካከል ስላለው ልዩነት ምን ትላለህ/ለሽ? አብርሃምስ በሁለቱ መካከል ልዩነት ማድረግ ለምን አስፈለገው?
5. 7-10 መሰረት የአብርሃም ፍጻሜ ምን ይመስል ነበር?
   - “በመልካም ሽምግልና” የሚለው ሃሳብ ምንን ሲያመለክት ይመስለሃል/ሻል?
   - የቀብር ቦታው በግዢ መሆኑ ፣ “ይህንን ምድር ለአንተና ለዘርህ እሰጣለሁ” ከሚለው የተስፋ ቃል ጋር እንዴት ይታረቃል?
6. ከቁ 12-15 የተጠቀሱት የእስማኤል ልጆች እንማን ናቸው?
7. ከቁ 16-18 ያለውን የእስማኤልን የሕይወት ታርክ፤ ከምዕራፍ 17፡20-20፤ ከምዕራፍ 16፡12 ስለ እርሱ ከተነገሩት ሃሳቦች ጋር በማዛመድ፤ ስለእግዚአብሔር የምትረዳውን/ጂውን አካፍል/ፍይ።
8. በቁ 21 በይስሐቅና በርብቃ ኑሮ ውስጥ የነበረው ችግር ምንድን ነበር?

- ይስሐቅ ለችግሮ መፍትሄ ነው ብሎ የውሰደው እርምጃ ምንድን ነበር? ውጤቱስ?

9. በቁ 22 ላይ ርብቃ ያደርገችው ምንድን ነበር? በቁ- 23 ላይ ያለውስ የእግዚአብሔር ምላሽ ምንድን ነበር?

10. ከቁ 24- 26 በመመልከት የይስሐቅ ልጆች እንማን እንደነበሩና አወላለዳቸው ምን ይመስል እንደነበር ግለጥ/ጭ።

11. እስከዛሬ ባነበብነው መሰረት፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም በዘፍ 12፡ 1-3 ላይ የሰጠውን የተስፋ ቃል በሙሉ ፈጽሟል ብለህ ታስባለህ?

12. በዘፍ 12 እግዚአብሔር ለአብርሃም ከገባለት ቃል ኪዳኖች ውስጥ በአብርሃም ሕይወት ውስጥ ገና ያልተፈጸመው የተስፋ ቃል የትኛው ነው?

   - የሚፈጸመውስ መቼ እና እንዴት ነው?

   - ይህ ተስፋ ቃል በአብርሃም የሕይወት ዘመን አለመፈጸሙ የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያጎድላል ትላለህ?

13. አብርሃምን እግዚአብሔር በጠራው ጊዜ "ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ" ሲል የሰጠውን ተስፋ በዚህ ክፍል መሰረት እግዚአብሔር የፈጸመው እንዴት ነው?

   - ይህስ ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት ምን ያስረዳሃል?

### *መደምደሚያ*

በእርግጥ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን የተስፋ ቃላት በሙሉ በአንድ ሌሊት ባይፈጽምለትም፣ እግዚአብሔር ለቃሉ ታማኝ ነበር፤ ያለውን ሁሉ ለአብርሃም ፈጽሞለታ። መጽሐፍ ቅዱስም "የተስፋን ቃል የሰጠው (*እግዚአብሔር*) የታመነ ነውና" (ዕብ 10፡23) እንደሚለው እግዚአብሔር ከቶ በታማኝነት አይታማም። እኛም እግዚአብሔር ታማኝ እንደሆነ ካመንን፣ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርገን የቆየንበት ጊዜ ቢረዝምም እንኳን ታማኝ በመሆኑ ተማምነንበት ልንኖር ይገባናል።

## ጥናት ሠላሳ ሶስት
## እንደ ምህረቱ እንጂ እንደ እኛ ያልሆነ ጌታ

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 26፡1-17

*መግቢያ፦* አንድ ዘማሪ "እግዚአብሔር ሰው ቢሆን ከቶ ምን በዋጠን" እንዳለው፣ እግዚአብሔር እንደ ሰው ጽድቅና ታማኝነት መጠን የሚከፍል ቢሆን ኖሮ፣ ዛሬ መቆም የሚችል ሰው ባልተገኘ ነበር። እግዚአብሔር ግን ሰው አይደለም! ስናጠፋ እና ስንስትም እንደገና በምህረቱ አቁሞ እኛን በመባረክ ደስ የሚሰኝ አምላክ ነው።

*ዓላማ፦* የእግዚአብሔር በረከት እንደ እርሱ ምህረት ብዛት እንጂ እንደ እኛ ማንነት መጠን የሚሰጥ እንዳልሆነ ማስገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቀድሞው በአብርሃም ዘመን የነበረው የራብ ዘመን የተከሰተው መቼ ነው?

- አብርሃምስ ለደረሰበት የራብ ችግር ምላሽ የሰጠው እንዴት ነው? (ዘፍ 12፡10 ተመልከቱ)

- አብርሃም በራብ ከሚመጣ ሞት ወደ ግብጽ ሸሽቶአል፤ በሚስቱ ምክኒያት ሊመጣበት ከሚችለው ሞት ለማምለጥ ያደረገው ነገር ምንድን ነበር? (ዘፍ 12፡11-20)

- አብርሃም ስለሚስቱ የሚያደናግር ነገር የተናገረው ስንት ጊዜ ነው? መቼ እና መቼ?

2. በቁ. 1 መሰረት ይስሐቅ ድርቅ በመጣበት ጊዜ ያደረገው ነገር ምንድን ነው?

3. በቁ 2-5 ባለው መሰረት እግዚአብሔር ለይስሐቅ የገባለት የተስፋ ቃል ምንድን ነው?

- የትኞቹስ ኪዳኖች እግዚአብሔር ለአብርሃም ከሰጠው የተስፋ ቃል ጋር ይመሳሰላል?

4. እግዚአብሔር ለይስሐቅ ቃል ኪዳን ከገባለት በኃላ የፍልስጤም ሰዎች ስለ ሚስቱ ስለ ርብቃ ሲጠይቁት የሰጣቸው ምላሽ ምንድን ነው?

- ይስሐቅ እንዲዋሽ ያደረገው ነገር ምንድን ነው? ይህስ ይስሐቅ በእግዚአብሔር ላይ ስላለው እምነት ምን ያሳያል?

- ይስሐቅ ነፍሱን ለማዳን ከአገር አገር መሄዱን እና ስለ ሚስቱ መዋሸትን የተማረው ከማን ነው ትላለህ?

- ከዚህ በመነሳት ልጆች እግዚአብሔርን መፍራት እንዲማሩ ወላጆች በልጆች ሕይወት ሊጫወቱ የሚችሉት ሚና ምንድን ነው ትላለህ?

5. ይስሐቅ በእግዚአብሔር ባለመታመን ከመዋሸቱ ሌላ የፈጸመው ድርጊት በጌረራ አገር ሰዎች ላይ ሊያመጣ የነበረው ችግር ምንድን ነው (ቁ. 10)?

6. በአብርሃም ጊዜ እንደሆነው እግዚአብሄር በዚህ ጊዜ በአቢሜሌክ ላይ ያልተቆጣው ለምንድን ነው (ዘፍ 20፡2-3 ያለውን ያወዳድሩ)?

- አቢሜሌክስ የይስሐቅን ቃል ከሰማ በኃላ ለይስሐቅ ያደረገለት ምንድን ነው (26፡11)?

7. ምንም እንኳ ይስሐቅ ቢያጠፋም እግዚአብሄር ለይስሐቅ ያደረገለት ምንድን ነው (26፡12-13)?

- ይስሐቅ በእግዚአብሔር መታመን እያቃተው ባለበት ጊዜ በእግዚአብሔር እንዴት ሊባረክ ቻለ?

- ይህስ እግዚአብሔር እንደ በደላችን የማይከፍለን ስለ መሆኑ ምን ያስረዳል?

8. የይስሐቅ ከመጠን በላይ መባረክ በፍልስጤማዊያኖቹ ልብ ውስጥ የፈጠረው ነገር ምንድን ነው (ዘፍ 26፡14-17)?

- ፍልስጤማዊያኖች በአገራቸው በተቀመጠው እንግዳ በይስሐቅ እስከሚቀኑበት ድረስ እግዚአብሔር እንዲባርከው ሊያደርገው የሚችል ነገር በይስሐቅ ላይ ምን አለ?

- እኛስ ከእግዚአብሔር ምህረት በቀር ከእግዚአብሔር እንድንቀበል ሊያደርገን የሚችል ምን ነገር አለን?

## መደምደሚያ

እግዚአብሔር መልካም አምላክ ነው! እግዚአብሔር እንደ ጸጋው ብዛት እንጂ እንደ ስራችን መጠን ከፍሎን አያውቅም። ለዚም ነው ዳንኤል አንደ ጊዜ በጸሎቱ “አምላኬ ሆይ፣ በፊትህ የምለምን ስለ ብዙ ምህረትህ ነው እንጂ ስለ ጽድቃችን አይደለምና ጆሮህን አዘንብለህ ስማ…” (ዳን 9፡18) ብሎ ልመናውን ለማቅረብ የበቃው። በመጽሐፍ ቅዱስ ስመ ጥር የሆኑት ታላላቅ ሰዎች እንኳን ሳይቀሩ እንደሌላው ሰው ሁሉ አንዳንዴ በእግዚአብሔር መታመን የሚቸግራቸው፣የሚበድሉ ሰዎች ናቸው። ዛሬም እኛ መኖራችን እና አለን የምንለው ሁሉ ስለተገባን ያገኘውነ ሳይሆን እግዚአብሔር ምህረቱ ስለበዛ የሆነልን ነው። ስለዚህም እግዚአብሔን በየእለት ኑሮአችን ልናመሰግነው ይገባናል።

## ጥናት ሠላሳ አራት
## እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ…

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 26፡18-35

**መግቢያ፦** እግዚአብሔር ከጎኑ የሚቆምለት ሰው የተባረከ ነው! ሐዋሪያው ጳውሎስ እንዳለው "እግዚአብሐር ከእኛ ጋር ከሆነ"፣ የሚቃወመን ነገር ከቶ አይኖርም። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ የሚከፉብንን ለእኛ ከማዝገዛቱ ሌላ፣ መንገዳችንን ያቀናል፣ ስራችንን ይባርካል እንዲሁም በሰዎች ሁሉ ፊት ሞገስ ይሆነናል። በዛሬው ጥናታችን የእግዚአብሔር አብሮን መሆን በእኛ ሕይወት ውስጥ ሊያመጣ የሚችለውን ለውጥ እንማራለን።

**ዓላማ፦** የእግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆን ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፣ በኑሮአችን ሁሉ እግዚአብሔር በእኛ ጎን እንዲሆን ማድረግ የሚገባንን ማሳወቅ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ካለፈው ጥናት በም 26 ፡1-17 ባለው ክፍል ውስጥ የሆነው ነገር ምንድን ነበር?

- በቁ 12-14 ባለው መሰረት እግዚአብሔር ይስሐቅን ባርኮታል። እግዚአብሔር ለምን ባረከው ብለህ ታስባለህ?

- እግዚአብሔር ይስሐቅን በመባረኩ ምክኒያት ይስሐቅ የደረሰበት ነገር ምንድን ነው? (ቁ 14-17)።

2. ይስሐቅ የጌራራ ሰዎች እንዲሔድላቸው በጠየቁት ጊዜ የሔደው ወዴት ነው (ቁ. 17)?

- በሔደበትስ ስፍራ ያደረገው ነገር ምንድን ነው? (ከቁ. 18-19 ያለውን ተመልከቱ)።

- በቁ 18፣ 19፣ 21፣ 22፣ 25፣ 32 ላይ በመደጋገም የይስሐቅ አገልጋዮች የውሃ ጉድጓድ ሲቆፍሩ እናያለን። የውሃ ጉድጓድ ማስቆፈርስ ለምን ያፈልጋል ብለህ ታስባለህ?

3. ከቁ. 20-22 ባለው ክፍል መሰረት፣ ይስሐቅ የውሃ ጉድጓድ ያስቆፈረው ስንት ጊዜ ነው?

- በእያንዳንዱ ጊዜስ የሆነው ምንድን ነው?

- የውሃ ጉድጓዶቹን በተመለከተ፣ በቁ 15 እና ከቁ 20-21 ባሉት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

- የጌሬረራ ሰዎች እንዳሰቡት ይስሐቅ የውሃ ጉድጓድ ባይኖረው ሊደርስበት የሚችለው ነገር ምንድን ነው?

- የጌሬራ አገር እረኞች ለምን በይስሐቅ እንደዚህ ሊከፉበት ቻሉ ብለህ ታስባለህ? ቁ 14 ትንሽ ፍንጭ የሚሰጥህ ከሆነ ለማገናዘብ ሞክር።

4. በቁ. 23-24 ባለው መሰረት የጌረራ ሰዎች ምንም ቢከፉበት፣ እግዚአብሔር ግን ለይስሐቅ ተገልጦለት የሰጠው ሁለት የተስፋ ቃላቶች ምንድን ናቸው?

5. በቁ 26-29 ባለው ክፍል፣ ይስሐቅን ያባረሩት እና የተነሱበት ሰዎች ራሳቸው፣ መጥተው ከይስሐቅ ሰላምን ሲለምኑ ይታያል።

- አሳዳጅ እና ክፉ የነበሩት ሰዎች ፈሪ እና ምህረትን ለማኝ እንዲሆኑ የሚያደርገውን ለውጥ ያመጣው ምንድን ነው?

- በቁ. 23-24 እግዚአብሔር “አትፍራ” ብሎ ለይስሐቅ ያዘዘው ቃል እንዴት ነው የተፈጸመው?

- እግዚአብሔር “እኔ ከአንተ ጋር ነኝ” እና “እባርክሃለሁ” ብሎ የሰጠውስ የተስፋ ቃል እንዴት ነው የተፈጸመው? (ቁ. 28-29 ባለው ክፍል ያለውን ልብ ብለህ በመመልከት ሁለቱም የተስፋ ቃላቶች ተፈጽመው እንደሆነ ተመልከት)።

6. በቁ. 28 እና 29 ላይ የጌራራ ሰዎች ይስሐቅን “እኛ አንተን እንዳልነካንህ፣ በጎነትንም ብቻ እንዳሳየንህ፣ በደህናም እንደሰደድንህ…” ብለው የተናገሩት ነገር ምን ያህል እውነት ነው?

7. አቢሜሌክ፣ አማካሪው እና የሰራዊቱ አዛዥ ከይስሐቅ ጋር እርቅ ፍለጋ ሲመጡ ይስሐቅ የተቀበላቸው እንዴት ነው?

- ይህስ ስለ ይስሐቅ ምን ይነግርሃል?

8. እግዚአብሔር ዛሬ ከእኛ ጋር እንዳይሆን እና ሕብረት እንዳያደርግ ሊያደርገው የሚችል ምን ነገር ይኖራል ብለህ ታስባለህ? (1ኛ ዮሐ 1፡5-6 እንዲሁም ኢሳ 59፡1-2 ያወዳድሩ)።

9. እግዚአብሔር አብሮት ያለ ሰው ምን አይነት ሰው ይሆናል ብለህ ታስባለህ?

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር አብሮት በመገኘቱ ምክኒያት በሚከፉበት እና በሚጠሉት ሰዎች ፊት እግዚአብሔር ድል የሰጠው ሰው ሌላ ማንን ታስታውሳለህ?

- እግዚአብሔርስ አብሮን እንዲሆን ምን ማድረግ ይገባናል?

### *መደምደሚያ*

እግዚአብሔር በጣም ትልቅ አምላክ ቢሆንም፣ ግን ከሰዎች ጋር በመሆን ደስ የሚሰኝ አምላክ ነው። እግዚአብሔር አብሮን ሲገኝ ተስፋዬ ጋቢሶ አንዴ ሲዘምር “በከንቱ በሚጠሉኝ ፊት ሞገስን አጎናጽፈኸኛል” እንዳለው በኑሮአችን ስኬትን፣ የሚከፉብንንም ሰዎች እያሳፈረ ያኖረናል። ዛሬ በፊቱ በንጽህና እና እግዚአብሔርን በመፍራት ከሚመላለሱት ሁሉ ጋር አብሮ ሊሆን እግዚአብሔር ቃል ገብቷል። ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክ ሁሌም አብሮን ይሆን ዘንድ እንደ ፈቃዱ እንኑር።

## ጥናት ሠላሳ አምስት

## ለዚህ አለም የሚመች ሰው የመሆን ዋጋ

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 26፡34 - ዘፍ.28፡9

**መግቢያ፦** መጽሐፍ ቅዱስ ዓለምን ወይንም በዓለም ያሉትን እንዳንወድ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ እያደረግን እንድንኖር ያዛል። ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ወደ ጎን ትቶ ዓለምን እየወደደ እና ፈቃድዋን እየፈጸመ የሚኖር ከሆነ፣ ለጊዜው በአድራጎቱ ደስ ቢሰኝበትም ወደ ኃላ ግን ማልቀሱ አይቀሬ ነው። "የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሐር ጠላት ሆኖአል"ና (ያዕ 4፡4) ።

**ዓላማ፦** ለዓለም የሚመች ሰው መሆን ዋጋው አንዳንዴ የዕድሜ ልክ ለቅሶ እና ጸጸት እንደሆነ በመረዳት፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንድንኖር ማበረታታት።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በ 27፡1-4 ባለው መሰረት ይስሐቅ ዔሳውን ለመባረክ የፈለገው ለምንድን ነው? እንዲባርከውስ ዔሳውን ያዘዘው ምን ነበር?

2. የምናስታውስ ከሆነ ዔሳው በኩርናውን ለያዕቆብ የሸጠለት እንዴት ነበር (ዘፍ 25፡ 29-34)?

- በዚህ መሰረት፣ ዔሳው በኩርናውን ከሸጠ በኃላ ይስሐቅ እንደ በኩር ሊባርክ የሚገባው ማንን ነበር ትላለህ?

- ይስሐቅ በያዕቆብ ፈንታ ዔሳውን ሊባርከው የፈለገው ለምን ይመስልሃል? (ፍንጭ የሚሰጥ ከመሰለህ ዘፍ 25፡28ን ተመልከት)

- እግዚአብሔርስ የአብርሃም በረከት እንዲደርስለት የመረጠው ማንን ነው ዔሳውን ወይስ ያዕቆብን? (ዘፍ 25፡23ን ያወዳድሩ)።

3. ዔሳው የአባቱን በረከት እንደሚቀበል እርግጠኛ ሆኖ ለአደን ወደ ምድረበዳ ሲሄድ በቁ 5 ላይ እናያለን።

- ዔሳው ወደ አድን በሄደበት ጊዜ የታቀደለት ሴራ ምን ነበር? ቁ. 7-10።

- ዔሳው ምንም እንኳ ከያዕቆብ እኩል ልጇ ቢሆንም፣ በዔሳው ፈንታ ያዕቆብ እንዲባርክ ለምን የፈለገች ይመስልሃል? (ፍንጭ የሚሰጥ ከመሰለህ ዘፍ 25፡28ን ተመልከት)

- የይስሐቅን እና የርብቃን እንዲሁም የያዕቆብን እና የዔሳውን ግንኙነት በማወዳደር፣ የይስሐቅ ቤተሰብ ጥሩ ቤተሰብ ነው ብለህ ታስባለህ?

4. ከቁ 18-29 ባለው ርብቃ እና ያዕቆብ ተማክረው ባቀዱት ሸር መሰረት፣ ይስሐቅ ያዕቆብን እንደባረከው እናያለን።

- እግዚአብሔር አብርሃምን በዘፍ 12፡1-5 ባለው ክፍል በባረከው በረከት እና ይስሐቅ ያዕቆብን በባረከው በረከት መካከል ያለው ተመሳሳይነት ምንድን ነው? (ዘፍ 27፡28-29 እንዲሁም ዘፍ 28፡3-4 ያለውን ልብ ብለህ ተመልከት)

- የአብርሃም በረከት ወደ ያዕቆብ መወራረሱ የሚያስተምርህ ነገር ምንድን ነው?

5. ከቁ 30-40 ባለው ክፍል ዔሳው ከአደን ሲመለስ፣ በእሱ ፈንታ ያዕቆብ በተንኮል ተባርኮ ሲጠብቀው እናያለን።

- አገር ሰላም ብሎ በንጹን ልብ ለአደን የሄደው ሰው ሳይሳካለት በተንኮል ሸር የሰሩት የያዕቆብ እና የርብቃ አሳብ የተሳካው ለምን ይመስልሃል?

- በዕብ 12፡16-17 መሰረት እግዚአብሔር ለዔሳው መሳካትን ያልሰጠው ለምንድን ነው?

- በዚሁ ክፍል "ከዚያ በኃላ እንኳን በረከቱን ሊወርስ በወደደ ጊዜ እንደተጣለ ታውቃላችሁና" ሲል ዔሳው የተጣለ ሰው የሆነው ከመቼ ጀምሮ ነው?

- ዔሳውን "ለዚህ ዓለም የሚመች ሰው" ብሎ ሰጠራው፣ ለዚህ ዓለም የሚመች ሰው ምን አይነት ሰው ነው?

- ዔሳው ለዚህ አለም የሚመች ሰው እንደሆነ የሚያሳዩ ምን ምን ነገሮች መጥቀስ ትችላለህ? (ዘፍ25፡31-34፣ ዘፍ 26፡34-35፣ ዘፍ 27፡41 ዘፍ 28፡41 ን አወዳድሩ)

6. ከአባቱ በረከትን ለማግኘት ዔሳው በለቅሶ ይስሐቅን ሲጠይቀው ቁ.38 ላይ እናያለን።

- በዚህ መሰረት ከቁ. 39-40 ባለው ክፍል ይስሐቅ ያዕቆብን ባርኮታል ብለህ ታስባለህ? (ዕብ 12፡17 ላይ የተጻፈውን አወዳድር)።

7. በዛሬው ጥናት መሰረት፣ የዓለምንና የሲጋን ፈቃድ እየፈጸሙ የመኖር ውጤቱ ምንድን ነው ትላለህ?

### *መደምደሚያ*

ሐዋሪያው ዮሐንስ በመልዕክቱ እንደጻፈው፣ "ማንም ዓለምን ቢወድ  የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም"። ስለ ዓለም እና ስለ ስጋ ፈቃድ ሲል የእግዚአብሔርን ፍቅር የጣለ፣ እጅግ ምስኪን ሰው ነው ምክኒያቱም "ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ"ና። እነዚህ ሁሉ ያለፉ ጊዜ ዘላለዊው እግዚአብሔር በልቡ  የሌለ ሰው የተጣለ ከመሆኑ ሌላ ምንም ቢጸጸት እና ቢያለቅስ የሚለውጠው ነገር አይኖርምና። ስለዚህ አማኝ ሁልጊዜ ዓለምን እየጠላ የጌታን ህግ ሊጠብቅ ይገባል፦ "የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራልና" (1ኛ ዮሐ 215-17)።

## ጥናት ሠላሳ ስድስት

## እግዚአብሔር የማይተው እና የማይለይ አምላክ ነው።

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 28፡10-22

መግቢያ፦ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ያለ በመሆኑ ሁሌም ከአጠገባችን መሆኑ አንድ እውነት ቢሆንም አጠገባችን ሆኖ የማያግዘን፣ ጥፋት ሲመጣ አሳልፎ የሚሰጠን የቅርብ ተመልካች አይደለም፤ ነገር ግን ግድ ብሎት በኛ ሕይወት ውስጥ ጣልቃ የሚገባ የማይተው እና የማይለይ አምላክ ነው። ባናስተውለው ወይም ብንዘነጋው እንኳ እግዚአብሔር ግን ሳይዘነጋን ሁሌ አብሮን አለ። በዛሬው ጥናታችን በያዕቆብ የኩብለላ ጉዞ ላይ ተመርኩዘን እግዚአብሔር እንዴት ያለ የማይለይ ወዳጅ እንደሆነ እንመለከታለን።

ዓላማ፦ በማናስበውና በማንጠብቀው ሰአት እንኳ የማይለየን እና በሕይወታችን ሊያደርግ ያለውን እስኪፈጽም ድረስ የማይተወን አምላክ ሁሌ አብሮን እንዳለ በማወቅ እንድንበረታታ ማገዝ

የአስጠኚው ማስታወሻ፦ ከዘፍ. 28፡22 -- ዘፍ. 33፡20 ያለው ክፍል አንድ ወጥ አሳብ ሲሆን፣ ዔሳውን ፍራቻ ከአባቱ ቤት የኮበለለው ያዕቆብ በአጎቱ በላባ ቤት በሃያ ለሚቆጠሩ አመታት ከኖረ በኃላ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ ወደ ገባለት አገር ወደ ከነዓን ምድር በሰላም መመለሱን ያሳየናል። ያዕቆብ ወደ ላባ ቤት በሄደበት በመንገዱ እግዚአብሔር እንዲጠብቀውና ወደ አባቱ ቤት በሰላም እንዲመልሰው ለምኖ እና ተስሎ ነበር (ዘፍ 28፡20-22)። በዚህም መሰረት እስከ ዘፍ 33፡20 ባለው ክፍል እግዝአብሔር እንዴት እንደጠበቀው እና ወደ ከነዓን ምድር እንዴት እንደመለሰው ያሳየናል (ዘፍ 33፡18-10)። በዚህም መሰረት እግዚአብሔር ለያዕቆብ እንዴት ታማኝ እንደሆነለት እናያለን። ምንም እንኳን ይሔ ክፍል እንደ አንድ ጥናት መጠናት ያለበት ቢሆንም፣ ብዙ ምዕራፎች እና ቁጥሮችን የያዘ በመሆኑ በአንድ ጊዜ ማጥናት አስቸጋሪ በመሆኑ በትንንሽ ምዕራፎች እየከፋፈልን እንመለከታለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ባለፈው ጥናታችን ከዘፍ 26-34 -28፡9 ባለው ክፍል የተመለከትነው ምንድን ነው?

- ከባለፈው ጥናት በመነሳት፣ ያዕቆብ ወደ አናቱ ቤተሰቦች እንዲሔድ የሆነው በውዴታ ነው ወይስ በግዴታ?

- ያዕቆብ ቢሆንለት የት መሆን ነው የሚፈልገው ብለህ ታስባለህ? ( በዘፍ 28፡21 ላይ ያለውን አወዳድር)

2. ዛሬ ባነበብነው ክፍል መሰረት ከቁ. 10-11 ባለው ያዕቆብ ከወንድሙ ፍራቻ የተነሳ ሲኮበልል እናያለን።

- ያዕቆብ በዚህ ጊዜ በውስጡ ሊኖር የሚችለው ስሜት ምን ይሆናል ብለህ ታስባለህ? ለምን? (በተለይም ቁ. 20-21 ያለውን በመደገፍ የያዕቆብ ፍራቻ ምን ነበር?)

3. በቁ12 -15 ያዕቆብ በመንገድ መሃል ተኝቶ ሳለ ያለመውን ሕልም እና እግዚአብሔር የገባለትን የተስፋ ቃል ያሳየናል።

- ያዕቆብ እንደዚህ ባለ የስሜት ነውጥ ውስጥ እያለ እግዚአብሔር  እንደዚህ ያለ የተስፋ ቃል መስጠቱ  ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?

- እግዚአብሔር የገባለት ቃል፣ ይስሐቅ ያዕቆብን በባረከው ጊዜ ከባረከው በረከት ጋር ምን ያህል ይመሳሰላል?

- እግዚአብሔር ለአብርሃም ከገባለትስ ቃል ኪዳን ጋርስ?

4. እግዚአብሔር ለያዕቆብ የገባለትን የተስፋ ቃል በእርግጥ እንደሚፈጽምለት ያረጋገጠለት እንዴት ነው?

5. ያዕቆብ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ከሰማ በኋላ እንደተደናገጠ እና እንደፈራ በቁ.16 ላይ እናነባለን።

- ያዕቆብ እንደዚህ እንዲገረም እና እንዲፈራ ያደረገው ነገር ምንድን ነው?

- ዛሬ እኛም በማይመች ሁኔታ ውስጥ ስንሆን እና የእግዚአብሔር መኖር እንኳ ትዝ የማይለን ሁኔታ ውስጥ ስንሆን እግዚአብሔር እንዳልተለየን ይሔ ክፍል እንዴት ያስተምረናል ብለህ ትስባለህ?

6. ከቁ. 18-22 ባለው ያዕቆብ ለእግዚአብሔር የተሳለውን ስለት እናነባለን።

- ያዕቆብ የተሳላቸው ሶስት ስለቶች ምንድን ናቸው?

- ከዚህ በኋላ ያሉትን ምዕራፎች ሳታነብ፣ እስከዛሬ ባለህ እውቀት ብመደገፍ

*መደምደሚያ*

ዳዊት በመዝሙሩ አንድ ቦታ ላይ እንዳለው፣ ሰው ወደ ሰማይ ቢወጣ ወይንም ወደ ሲኦልም እንኳ ቢወርድ፣ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ አለ። ነገር ግን ሰዎች በመሆናችን በምናልፍበት ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር አብሮን እንዳለ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ መኖሩን ልንጠራጠር እንችላለን። ምንም አይነት ስሜት ቢሰማንም ግን እግዚአብሔር ሁሌም አብሮን አለ! አብሮን ከመሆኑም በላይ ባለንበትም ቦታ ዳዊት እንዳለው “በዚያ እጅህ ትመራኛለች፣ ቀኝህም ትይዘኛለች” (መዝ 139፡7-12) ።

## ጥናት ሠላሳ ሰባት

## ሰው የዘራውን ያንኑ ደግሞ ያጭዳል።

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 29፡1-30

**መግቢያ፦** የመዝራትን እና የማጨድን ስርዓት በተፈጥሮ ውስጥ ያስቀመጠው እግዚአብሔር ነው። ይህ የመዝራት እና የማጨድ ሕግ የሚሰራው በእህልና በሰብል ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በሰው የሕይወት አካሔድም ላይ ነው። ሰው በመልካም ሕይወት የሚመላለስ ከሆነ፣ እንደ አካሔዱ ከእግዚአብሔር ዘንድ መልካም ዋጋን ይቀበላል። በክፉ እና በጥፋት መንገድ የሚመላለስም እንዲሁ የጥፋቱን ዋጋ በጊዜው ይቀበላል፤ ሰው ያልለፋበትን እና ያልዘራውን አያጭድምና።

**ዓላማ፦** በአካሔዳች የምንዘራውን ዘር ወደ ኋላ ላይ መልሰን እንደምናጭደው በመገንዘብ አካሔዳችንን እና አድራጎታችንን ከወዲሁ እንድናሳምር ማሳሰብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከባለፈው ጥናታችን በመነሳት፣ ያዕቆብ ከወንድሙ ከዔሳው በመሸሽ ጉዞ የጀመረው ወዴት ነው?

- በዚህም ጉዞው ለእግዚአብሔር የተሳለው ስለት ምን ነበር?

- ያዕቆብ ለእግዚአብሔር ስለቱን ለመስጠት ቃል የገባው እግዚአብሄር ምን ቢያደርግለት ነው?

2. በዘፍ 28፡20 ላይ ያዕቆብ “እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን፣ በዚች መንገድ ቢጠብቀኝ፣ የምበላውን እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ…” በማለት ከእግዚአብሔር የሚፈልገውን ተናግሯል።

- በም. 29፡1-20 ባለው በመደገፍ፣ እግዚአብሔር ከያዕቆብ ጋር መሆኑን እና በመንገዱ እንደጠበቀው ያሳየው በምንድን ነው?

- የሚበላውንስ እንጀራ ለያዕቆብ ያዘጋጀለት እንዴት ነው?

3. በዘፍ 27፡43 እንዲሁም በዘፍ 28፡5 መሰረት ያዕቆብ ጉዞ የጀመረው በካራን ወዳለው ወደ አጎቱ ወደ ላባ ቤት ነው።

- በዘፍ 29፡1-6 ባለው ያዕቆብ ያለምንም ችግር አጎቱ ላባን ወደሚያውቁት ሰወች ዘንድ መድረሱ የእግዚአብሔር እጅ አለበት ብለህ ታስባለህ?

- በም 28፡2 መሰረት ከወንድሙ ከዔሳው ከመሸሽ ሌላ ያዕቆብ ወደ ላባ ቤት የሄደበት ምክኒያት ምንድን ነው?

- በዚህ መሰረት ያዕቆብ ያለ ብዙ ችግር ራሔልን በመንገዱ ማግኘቱ እግዚአብሔር መንገዱን እንዳቀናለት እንዲያስብ ሊያደርገው ይችላል ብለህ ታስባለህ?

4. ያዕቆብ የሚሰው ስም ትርጉሙ “አታላይ” ማለት ነው።  ያዕቆብ የስሙን ባህሪያት የሚገልጹ ያደረጋቸው የማታለል ድርጊቶች የትኞቹን ታስታውሳለህ? (ዘፍ 26፡36 አገናዝቡ)!

5. በቁ. 13-20 ባለው መስረት ያዕቆብ ከላባ ጋር ባደረገው ስምምነት ስለ ራሔል የተገዛው ሰባት አመት ነው።

- ሆኖም ግን ያዕቆብ ያልለፋላት ሴት (ልያ) ስትሰጠው የመለሰው ምላሽ ምን ነበር?

- እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ያዕቆብን እያሳካለት እና እየመራው እንዳልነበረ ሁሉ፣ አሁን ግን ሲታለል እግዚአብሔር ለምን ዝም ያለው ይመስልሃል?

- "ለጉልቤም ጉልቤ አለው" የሚለው አባባል ያዕቆብ ከገጠመው ገጠመኝ ጋር እንዴት ይሄዳል?

6. አታላዩ ያዕቆብ ሲታለል እግዚአብሔር ዝም ማለቱ እግዚአብሔር ለያዕቆብ "የነገርኩህን ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና" (ዘፍ 28፥15) ብሎ የገባለትን ቃል የዘነጋው ይመስልሃል?

## መደምደሚያ

እግዚአብሔር ለሰው የገባውን ቃል አይጥስም፤ አደርጋለሁ ያለውን ሁሉ በእርግጥ ያደርጋል! ሆኖም ግን እግዚአብሔር ለሰው ተስፋ ሰጠ ማለት ተስፋ የተሰጠው ሰው ሲያጠፋ እግዚአብሔር እንደፈለገ እንዲሆን ይለቀዋል ማለት አይደለም! ሰው ከእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ይኑረውም አይኑረው ለሚዘራው መልካምም ሆነ ክፉ ዘር ተመጣጣኙን ማጨዱ አይቀሬ ነው። ለዚህም ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ "አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና" ሲል የጻፈው (ገላ 6፥7)። ስለዚህ የኃጢአትን ስራ ከማድረግ ይልቅ መልካሙን ነገር ሁሉ ልናደርግ ይገባል። እንደገና ጳውሎስ እንዳለው "ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት" (ገላ 6፥9)።

## ጥናት ሠላሳ ስምንት
## የበጎ ስጦታ እና የበረከት ምንጭ እግዚአብሔር ነው!

**የምንባብ ክፍል፦** ዘፍ. 29፡31 - ዘፍ 30፡43

**መግቢያ፦** በሕይወት ዘመናችን ሰርተን ስናገኝ፣ ተምረን ሲሳካልን እና በተለያየ መንገድ ነገሮች ሲሰምሩልን፣ በራሳችን ጥረት እና ልፋት ብቻ ያመጣናቸው መስሎን ብዙ ጊዜ እንታለላለን። እውነታው ግን ሲመረመር ከምናገኛቸው ስኬቶች እና ከጥረታችን ሁሉ በስተጀርባ ስራውን የሚሰራው እግዚአብሔር ነው። በዛሬው ጥናታችን፣በያዕቆብ ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር ሰርቶ እንዴት እንደባረከው እንመለከታን።

**ዓላማ፦** ቢገባንም ባይገባንም ከሕይወታችን በስተጀርባ የሚሰራውና ስኬትን የሚሰጠን አምላክ እግዚአብሔር መሆኑን በመረዳት በእግዚአብሔር ተደላድለን እንድንኖር ማስገንዘብ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ከም 29፡31- 30፡24 ባለው እግዚአብሔር ያዕቆብን በልጆች እንዴት እንደባረከው እናያለን። በዚህም መሰረት ፦

- በም 29፡31 ላይ ለያዕቆብ ልጅን የሰጠው እግዚአብሔር መሆኑን የሚያሳይ ምን ነገር አለ?
- ከቁ 32-35 ባለው ልያ አራት ልጆችን ስትወልድ ለሁሉም ስም ያወጣችላቸውን ስም በመደገፍ ልጅን የሚሰጥ እግዚአብሔር መሆኑን የሚያሳዩ ምን ነገሮች አሉ?

2. ም 30፡1-2 እና 3፡22-24 በማወዳደር ባለትዳሮች አብረው ስለተኙ ብቻ ልጅ እንደማይመጣ የሚያሳየን እንዴት ነው? (መዝ 127፡3ን አገናዝብ)።

3. ለልያ ማኅፀንዋም የከፍቶ ልጅ የሰጣት እና ለራሔል ማኅፀንዋን ዘግቶ ልጅ የነሳት እግዚአብሄር እንደሆነ ክፍሉ በደንብ ይናገራል (ዘፍ. 29፡31 እንዲሁም ዘፍ 30፡2)።

- እግዚአብሔር ለአንዱ መልካም አድርጎ ለሌላው ዝም የሚለው ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?
- ራሔል ልጅ ያለማግኘቷ ምክኒያቱ እግዚአብሔር መሆኑን ማወቋ እንድትወስድ ያደረጋት እርምጃ ምንድን ነው? (ፍንጭ የሚሰጥ ከሆነ ዘፍ 30፡22ን አስተውለህ ተመልከት)።
- በዚህ መሰረት ዛሬ ከእግዚአብሔር አልተቀበልኩም ወይንም አልተሳካልኝም በምንለው ነገር ሁሉ መፍተሔ ለማግኘት  ማድረግ የሚጠበቅብን ምንድን ነው?

4. እስከ ዘፍ 30፡24 ያለውን በማገናዝብ እግዚአብሔር ለያዕቆብ የሰተው ልጆች ስንት ናቸው?

5. በዘፍ 30፡43 መሰረት ቤተሰብ ከመመስረት እና ልጆችን ከማግኘት ሌላ ያዕቆብ የተባረከው በምንድን ነው?

6. በዘፍ 30፡ 30 ላይ ያዕቆብ "አሁንም ለቤቴ የምሰራው መቼ ነው?" ብሎ በመጠየቅ ከዚያ ወዲያ ለራሱ ቤት ሲደክም እና ሲሰራ እናያለን።

- በዚህ መስረት ያዕቆብ የተባረከው እና ባለጠጋ የሆነው በራሱ ጥረት ነው ወይንስ እግዚአብሔር ባርኮት ነው?
- በዚሁ መሰረት የሰው ጥረት እና የእግዚአብሔር  በረከት አብረው የሚሰሩት እንዴት ነው? (መዝ 127፡1-2 ያለውን አወዳድሩ)

7. በዘፍ 30፡27-30 ባለው ላባም ሆነ ያዕቆብ በያዕቆብ ምክኒያት ላባን የባረከው እግዚአብሔር እንደሆነ አውቀዋል።

- ያዕቆብ እና ላባ የበረከቱ ምንጭ እግዚአብሔር እንጂ የያዕቆብ ስራ አለመሆኑን በምን ተረዱ?
- ዛሬስ በአንተ ሕይወት ውስጥ እየሰራ ያለው እግዚአብሔር እንጂ አንተ ብቻህን እንዳሆንክ በምን ታውቃለህ?

8. በዘፍ 30፡37-42 ባለው መሰረት ያዕቆብ ብርቱ የሆኑት እና ብዙ የሆኑት እንሰሳቶች የእርሱ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

- ያዕቆብ እንዳሰበው የበረከቱ እና የጠነከሩ እንሰሶችን ያገኘው በፈጠረው ዘዴ ነው ብለህ ታስባለህ? ለምን? (መልሱን ለማግኘት አዲሱ መደበኛ ትርጉም ላይ የተጻፈውን ማብራሪያ እና ዘፍ 31፡9 ላይ ያለውን ተመልከት)።

## *መደምደሚያ*

በምንደክምበት ድካም፣ በምንጥረው ጥረት እንዲሁም በልፋታችን ሁሉ ጣልቃ ገብቶ ለሕይወታችን ስኬትን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው። በመጀመሪያ ደረጃ፣ ለመስራት እና ለመጣር እንድንችል ጉልበቱንም ሆነ መሻቱን የሰጠን እግዚአብሔር ነው። ለሚገጥመን መልካም ነገር ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ምንጩ እግዚአብሔር ራሱ ነው። ስለዚህም ሰው በለፋበት ልፋት ሁሉ ስኬትን ሲያገኝ “እኔ በጉልበቴ ብርታት” ያመጣሁት ነው ብሎ አይታበይ፣ የሚመካ ቢኖር በእግዚአብሔር እንዲመካ ይገባልና (1ኛ ቆሮ 1፡29)።

## ጥናት ሠላሳ ዘጠኝ

## ጸንቶ የሚታገሰውን እግዚአብሔር ይታደጋል!

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 31፡1-55

መግቢያ፦ ሰው ጥፋት ሰርቶ ለጥፋቱ ተመጣጣኝ የሆነ መከራን ሲቀበል፣ የሚያልፍበትን መከራ መታገስ ብዙ ላይከብድ ይችላል። ነገር ግን ምንም ባላጠፋበት ምድር በደልን ታግሶ መኖር ከባድ ነው። በተለይም ደግሞ በእንደዚህ አይነቱ ሰዓት ታማኝ ሆኖ መስራት የበለጠ አስቸጋሪ ነገር ነው። ሆኖም ግን የእግዚአብሔር ቃል ያለጥፋታችን የሚመጣብንን በደል እና መከራ እግዚአብሔርን በማሰብ መታገስ እንዳለብን አጥብቆ ያስተምራል። እግዚአብሔር የምናልፍበትን በደል ሁሉ የሚመለከት አምላክ በመሆኑ አንድ ቀን ምላሽ እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ በትዕግስት ታማኝ ሆነን እንድንኖር ያዛል። ለምሳሌ አጋር በአብርሃም ቤት ሳለች ከሣራ በታች ሆና ከባድ እና የመረረ መከራ ገጥሟት በሸሸች ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ያዘዛት የምታልፍበትን ታግሳ እንደገና ከእመቤቷ እግር ስር እንድትገዛ ነበር። በእርግጥም ደግሞ የሚያይ እግዚአብሔር ስንታገስ አንድ ቀን መልስ ይሰጣል፤ ያኔ ልክ እንደ አጋር እግዚአብሔር ባለፍንበትመንገድ ሁሉ እግዚአብሔር ባለፍንበት መንገድ ሁሉ ሲያየን እንደነበረ እንረዳለን።

ዓላማ፦ ሰዎች ሲጎዱንና ሲያሳዝኑን እግዚአብሔር ተስፋ በማድረግ ብንታገስ ብድራታችን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደማይጠፋ ለመገንዘብ፡

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በአዲሱ መደበኛ ትርጉም መሰረት በቁ. 1 ላይ የላባ ልጆች “ያዕቆብ የአባታችንን ሀብት እንዳለ ወስዶታል፣ ይህ ሁሉ እርሱ ያካበተውም ሀብት ከአባታችን የተገኘ ነው” ሲሉ ያዕቆብ ሰምቷል።

- ይህ ምን ያህል እውነት ነው ትላለህ? በተለይ ቁ. 7-9 ያለውን ተመልከት።

- የያዕቆብስ ሀብት እውነተኛው ምንጭ  ማን ነው ትላለህ? ቁ.9 እና 10ን አወዳድር።

2. በቁ. 38 እንዲሁም 41 መሰረት፣ ያዕቆብ በላባ ቤት የከረመው እና ያገለገለው ለሃያ አመታት ነው።

- በእነዚህ አመታት ሁሉ ያዕቆብ ለላባ ታማኝ ሆኖ መስራቱን የሚያሳዩ ምን ነገሮች ከክፍሉ ማየት ትችላለህ? (ቁ. 6ን አወዳድር)

- ከቁ 38-42 ያለውን በመመልከት ያዕቆብ በትጋት ማገልግሉን የሚገልጹት ቃላት እና አባባሎች ምንድን ናቸው?

3. ያዕቆብ በታማኝነት እና በትጋት ላባን ለሃያ አመታት ያህል ሲያገለግለው ላባ በእነዚህ አመታት ሁሉ ያዕቆብን የተቀበለው እንዴት ባለ ሁኔታ ነው?

- በተለያዩ ቁጥሮች ውስጥ ያዕቆብ በላባ እንደ ተበደለ ደጋግሞ ይናገራል። ያዕቆብ በላባ የተበደለው እንዴት እንዴት ነው? (ቁ.7፣ 39፣ 41ን ተመልከቱ)

4. በቁ.2 መሠረት ከሃያ አመታት በኃላ የላባ አመለካከት የተለውጠ ይመስልሃል?
5. የላባ ፊት በያዕቆብ ላይ በተለወጠበት ሰዓት እግዚአብሔር ለያዕቆብ የሰጠው መመሪያ ምንድነው? ቁ.3፣ 13

- ይህስ ጊዜው ነው ትላለህን?

- በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ለያዕቆብ የሰጠው መመሪያ በም 28፡13-15 ባለው ክፍል እግዚአብሔር ለያዕቆብ ከሰጠው ተስፋ ጋር እንዴት የመሳሰላል?

6. እግዚአብሄር በሰጠው መመሪያ መሰረት ያዕቆብ ከሚስቶቹ ጋር ተማክሮ እና የላባን በአከባቢው ያለመኖር አጋጣሚ ተጠቅሞ ያዕቆብ ኮብልሏል።

- ያዕቆብ በዚህ አይነት መልኩ ባይሸሽ ኖሮ ሊገጥመኝ ይችላል ብሎ ያሰበው ነገር ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? (ቁ. 31 እና 42ን አወዳድር)።

7. በላባ ሁኔታ የተመረረው ያዕቆብ ሸሽቶ ቢሄድም ላባ ግን ተከታትሎት እንደ ሄደ እናያለን (ቁ.22-25)

- ከላባ እጅ እና ክፉ አሳብ እግዚአብሔር ያዕቆብን ያስጣለው እንዴት ነው? (ቁ. ቁ.29፣ 42)

8. ያዕቆብ ከሃያ ጽኑ የመከራ አመታት በኃላ እግዚአብሔር አስቦታል። በእነዚህ ጊዜአት ሁሉ ያዕቆብ ሲበደል እግዚአብሔር የት ነበር? (ቁ. 12፣ 42 አወዳድሩ)

9. እግዚአብሔር በሚያስመርር ሁኔታ ውስጥም እንድኳ ታማኝ ታጋሽ ሆነን እንድናገለግል የሚፈልገው ለምንድን ነው ትላለህ? (1ኛ ጴጥ 22፡19ን አወዳድር)።

10. እግዚአብሔር የሚያይ እንዲሁም የሚታደግ አምላክ መሆኑ ዛሬ በስራ ቦታም ይሁን ሰዎች በማይመች ሁኔታ ነው የሚቀበሉኝ በምትላቸው ቦታዎች ሁሉ እንዴት መኖር እንዳለብህ ምን ያስተምርሃል?

## መደምደሚያ

መታገስ ደስ የሚያሰኝ ነገር አይደለም፤ ነገር ግን መልካም እግዚአብሔርም የሚወደው ነገር ነው። እግዚአብሔርን እያሰቡ በመልካም ሕይወት እየታገሱ እና እግዚአብሔርን እየጠበቁ የሚኖሩ ሁሉ አንድ ቀን ከእግዚአብሔር መልካምን መልስ ይሰጣቸዋል። አብርሃም ታግሶ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል አግኝቷል፣ ያዕቆብ ታግሶ ከላባ ጭቆና ነጻ ወጥቶአል፣ ኢዮብ ታግሶ ከመከራ ጽኗል፣ በአዲስ ኪዳን ደግሞ መታገስ እንዳለን የእግዚአብሔር ቃል ያስተምራል (ያዕ 5፡7)። ስለዚህ በምናልፍበት ሁሉ እንደ ጌታ ልጆች ታማኝ እና ታጋሽ ሰዎች እንድንሆን ይገባናል።

## ጥናት አርባ
## ሰላምና ዕርቅን ፍለጋ መውጣት

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 32፥1-33፥20

መግቢያ፦ መጽሐፍ ቅዱስ ቢቻላችሁስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ ብሎ ሲመክረን፣ ከዚህ በኃላ ቢሚኖረን ሕይወት ከሰው ጋር በሰላም እንድንኖር ብቻ ሳይሆን፣ ከዚህ በፊት ከሌሎች ጋር ሻካራ የሆነ ግንኙነት ኖሮን ከነበረ ሰላምን እንድንፈጥር የሚመክረን ክፍልም ነው። ሆኖም ግን ብዙ ጊዜ ሰዎች የሚያስታርቅ ሰው በመሃል ካልገባ ወይንም ሌላኛው ወገን በራሱ መጥቶ ይቅርታ ካልጠየቀ በራሳችን ደፍረን ሰላምን ለመፍጠር፣ እንዲሁም ይቅርታን ለመጠየቅ እንፈራለን። ወደ ያዕቆብ ሕይወት እንደገና መለስ ብለን የያዕቆብን ሕይወት ስናጠና ግን፣ በራሳችን አነሳሽነት ሰላም እና ዕርቅ ፈላጊዎች መሆን እንዳለብን እንማራለን።

ዓላማ፦ በሚኖረን ቀሪ ዘመን በራሳችን አነሳሽነት ከሌሎች ጋር በሰላም ለመኖር የምንችለውን እርምጃ ሁሉ መውሰድ እንዳለብን ማሳሰብ፡

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በም 32፥1 ላይ "ያዕቆብም መንገዱን ሄደ" በማለት የጀመረውን ጉዞ እንደቀጠለ ይነግረናል።

- እስካሁን ድረስ ባየናቸው ክፍሎች ላይ በመደገፍ የያዕቆብ ጉዞ ከየት ወደ የት ነው? (ዘፍ 31፥17-18 ያለውን አወዳድር)

- ያዕቆብ ወደ አባቱ ወደ ከነዓን ምድር ሲሄድ ይገጥመኛል ብሎ በልቡ ይፈራው የነበረው ነገር ምንድን ነው? ለምን? (ዘፍ 32፡3-7 እንዲሁም ቁ. 11 ላይ ያለውን አስተውለህ ተመልከት)።

2. ከላይ እንዳየነው፣ የያዕቆብ ጉዞ ወደ አባቱ ምድር ወደ ከነዓን እንጂ ወደ ዔሳው አገር ወደ ሴይር አልነበረም።

- ነገር ግን ያዕቆብ ዔሳው ወደሚኖርበት ወደ ሴይር ከተማ መልዕክት መላክ እና ከዔሳው ጋር መገናኘት ለምን ያስፈልገዋል ብለህ ታስባለህ?

- ያዕቆብ ከዔሳው ጋር ሳይታረቅ፣ እንዲሁ ወደ ከነዓን ምድር ሄዶ መኖር ቢጀምር ሊፈጠር የሚችለው ችግር ምንድን ነው ትላለህ?

- አንተስ ዛሬ ባለህበት ሕይወት ከሌላው ወንድም ወይንም እህት ጋር ሰላም ሳትፈጥር ወደ ሌላው ጉዳይህ መሄድ የሌለብህ ለምንድን ነው ትላለህ? (ማቴ 5፡23-26 ተመልከት)

3. ያዕቆብ ዔሳው ሊገናኘው ከአራት መቶ ሰዎች ጋር እንደሚመጣ ሲሰማ፣ እጅግ ፈርቶ እንደተጨነቀ አንብበናል።

- በዘፍ 32፡7-12 ባለው ክፍል መሰረት ዔሳው መጥቶ አደጋ እንዳይጥልበት ለማድረግ ሲል ያደረጋቸው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

- እነዚህ ሁለት እርምጃዎች ከሌሎች ጋር እርቅ ለመፍጠር በሚደረገው ሂደት ውስጥ ስለ ሰው ድርሻ እና ስለ እግዚአብሔር ድርሻ ምን ያስተምረሃል?

4. ያዕቆብ ወንድሙ ሊገናኘው እየመጣ የመሆኑን ዜና እንዴት ባለ ሁኔታ ነበር ያስተናገደው? በዝርዝር ተመልከቱት፡ (ቁጥር 1-4)

- ይህውስ አድራጎቱ በያዕቆብ ልብና ሃሳብ ውስጥ ምን እንዳለ ያመለክተናል?

5. ያዕቆብ ምንም ነገር ቢመጣ፣ የሚመጣውን ሁሉ ከፍሎ ከወንድሙ ከያዕቆብ ጋር ለመታረቅ የቆረጠ መሆኑን የሚያሳዩ ምን ነገሮች አሉ?

6. በዘፍ 33፡4 መሰረት ዔሳው የበደለውን ወንድሙን ያዕቆብን አቅፎ ሲስመውና ሲላቀሱ ያሳየናል።

- ይሔ አይነቱ ነገር ይሆናል ብሎ ያዕቆብብ ያሰበ ይመስልሃል? ያሰበ ወይንም ያላሰበ መሆኑን በምን ታውቃለህ? (ቁ. 8-10 ያለውን ተመልከት)

7. ከቁ. 16-20 ያለውን በመመልከት ከዚህ እርቅ እና ሰላም በኃላ ያዕቆብ መኖር ስለጀመረው አዲስ ምዕራፍ ምን ያሳያል።

- ያዕቆብ ከዔሳው ጋር ሰላም ባይፈጥር ኖሮ የጀመረውን አዲስ የኑሮ ምዕራፍ በምን አይነት መልኩ ነበር የሚኖረው ብለህ ታስባለህ?

8. ያዕቆብ ያለ ሽማግሌ በራሱ አነሳሽነት ከወንድሙ ጋር እርቅ መፈለጉ ዛሬ በዚህ ዘመን ላለነው ሰዎች ይሚሰጠን ምክር ምንድን ነው ትላለህ?

## መደምደሚያ

በምሳ 16፡7 ላይ "የሰው አካሄድ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው እንደሆነ በእርሱ እና በጠላቶቹ መካከል ስንኳ ሰላምን ያደርጋል" እንደሚለው፣ ዕርቅ እና ሰላምን ፍለጋ የምንሄድበት መንገድ ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ ስለሚያሰኘው ይጎዱናል፣ አይመቹንም ከምንላቸው ሁሉ ጋር እንኳ ሰላምን እንደሚሰጥ ቅዱስ ቃሉ ያስተምረናል። ስለዚህም በምንኖረው ኑሮ ሁሉ ጤነኛ ያልሆኑ ሻካራ ነገሮች እንኳን ሲፈጠሩ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው መንገድ እኛው በራሳችን አነሳሽነት፣ የምንችለውን ሁሉ አድርገን እና ጸልየን ወደ ዕርቅ መሔዳችን መሆኑን በማወቅ የመጀመሪያውን እርምጃ የምንወስደው እኛ እንድንሆን ይገባል። ከሁሉም በላይ የእግዚአብሔር ቃል "ሰላምን እሻ ተከተላትም" (መዝ 34፡14) ብሎ እንደሚያዘን ልናስታውስ ይገባናል።

ጥናት አርባ አንድ

## የጠላትን ሽንገላ እና ማታለል እምቢ በሉ

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 34፡1-35፡10

**መግቢያ፦** ከተሰወረ ወዳጅነት ግልጽ የሆነው ጠላትነት የሚመረጥበት ምክኒያት አለው ፡ ዓይኑን አፍጥጦ ሊጎዳው ከሚመጣበት ጠላቱ እራሱንም ሆነ የእርሱ የሆነውን ከመከላከል ከጥቃት በመጠበቅ ፈንታ ዝም ብሎ የሚመለከት ሰው አይኖርም። እንዳውም ጠላቱ እንዳይጎዳውና እንዳያገኘው አቅሙና ችሎታው የፈቀደውን ሁሉ ከማድረግ ወደ ኃላ የሚልም የለም ፡ ይሁን እንጂ ብዙን ጊዜ ሰው ጠላት በለሰለሰ የወዳጅነት ቃል ወይንም በጥቅማ ጥቅም በመደለል አልፎም ተርፎም በሽንገላ በማባበልና በማታለል ወጥመዱ ውስጥ በቀላሉ በመያዝ ለጠላት ጥቃትና ጉዳት ሰለባ ለመሆን የሚዳረግበት አጋጣሚዎች አያሌ ናቸው፡ ሌላው ከዚህ ጎን ለጎን ተያይዞ ልብ ሊባል የሚገባው እውነታም በዚህም መልኩ የሚመጣው የጠላት ጥቃት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን መዘንጋት የለበትም።

**ዓላማ፦** ወዳጅ መስሎ ተሰውሮ በቀላሉ ሊያጠምደንና ጠላልፎ ሊይዘን ለሚመጣ የጣላት ሃሳብ እጅ ሳንሰጥ በየዕለቱ እንቢ እያልን በድል እርምጃ እንዴት መራመድ እንዳለብን ለማስገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቁ.1-4 ባለው መሰረት፣ያዕቆብ በሴኬም ድንኳኑን ተክሎ መኖር እንደ ጀመረ በሴት ልጁ በዲና ላይ በምድሩ ከሚኖሩት ሰዎች መካከል ሴኬም የተባለው ወጣት የፈጸመባትን አስነዋሪ ነገር እንመለከታለን፡

- በቁ. 5 ያዕቆብ እንዲሁም ልጆቹ በቁ. 13 በዲና ላይ የተፈጸመባትን ድርጊት ከሰሙ በኃላ ከዝምታ ሌላ የተለየ ነገር ሊያደርጉ ይችላሉ ነበር ትላለህ?

- ያዕቆብ ልጆቹ እስኪመጡ ታግሶ ከመቆየቱና ከመጠበቁ እንዲሁም ልጆቹ የሆዳቸውን በሆዳቸው ይዘው በሰላም ከሴኬምና ካባቱ ጋር መነጋገር መቻላቸውን ስትመለከት ስለ ትዕግስት ምን ታስተውላለህ ?

- በቁጣ ግፊት ቸኩሎ እርምጃ በመውሰድ ችግር ውስጥ የገባ ሰው አይተህ ታውቃለህ? የትእግስትና የመረጋጋት ፍሬስ ከምንወስደው እርምጃ አንጻር ምድነው ትላለህ፡?

2. ከቁ.6-7 የዲና ወንድሞች በእህታቸው ላይ የተፈጸመውን ነገር ከሰሙ በኃላ እንዳዘኑና ክፉኛ አምርረው እንደተቆጡ እንመለከታለን፡ ከቁ. 13 በማነጻጸር ተመልከቱት

- የሃዘናቸው ጥልቀትና ምሬት ሊያከብደው የቻለው እህታቸው ስለሆነች ብቻ ነው ትላለህ? በእስራኤል ላይ የተፈጸመ አስነዋሪ ድርጊት ማለታቸው ምን ያመለክታል ቁ.7?

- አንተስ በህይወትህ የሚሆነው ነገር አንተ ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት አንጻር ብቻ ነው ምታየው ወይንስ ከእግዜብሔር ጋር ያለህን ነገር ይነካል ብለህ ታስባለህ? ምሳሌ ማቅረብ ይቻላል

3. ቁ.8-13 እንዲሁም ቁ.21-24 ሴኬም አባቱና በምድሩም የሚኖሩት ሰዎች ለያዕቆብና ለልጆቹ በዲና ላይ ስለተፈጸመው በደል የእርቅ ሃሳብ አቅርበው ነበር?

- ያዕቆብ ልጆቹ ለመድሩ እንግዳ ከመሆኑ አንጻር ስትመለከተው የቀረበላቸው ሃሳብ የሚገፋ ይመስልሃል? እንዲያውም ተቀባይነትና ብዙ ትርፍ ለማግኘት ጥሩ አጋጣሚ አይመስልም?

- የቀረበለትን ሃሳብ ቢያስተናግድ ወደፊት ሊገጥመው የሚችለው ችግር ምን ይመስልሃል?

- ከሴኬምና ካገሩ ሰዎች ንግግር አንጻር ስትመለከት ከጋብቻ ጥያቄ ውጭ ሌላ አጀንዳ እንዳላቸው የሚያመለክት ነገር ታያለህ?

- አንተስ  ጥሩ መስለው የሚቀርቡልህ የጠላት ሽንገላዎች ለጊዜው ከሚያስገኙት ትርፍ ይልቅ ሊያስከትሉ የሚችሉት ጉዳት ምን ሊሆን ይችላል?

4. በመጨረሻም ከተሳካ በጋብቻ አለያም በጥቅማ ጥቅማ ወጥመድ ተብትቦ በመያዥ ወደ እግዜብሔር ሃሳብ እንዳይርሱ ሊያስቀራቸው ከነበረው ወጥመድ የያዕቆብ ልጆች አምልጠው የጠላትን ሽንገላ ማባበል እንቢ በማለት በድል ሲገዙ እንመለከታለን፡ ከቁ.25-31

- ለእግዜብሔር ዓላማና ሃሳብ ብቻ ተለይቶ ለመኖር የእንቢታ ተጋድሎ ማድረግ እንዳለ ከዚህ ክፍል የተረዳኸው እውነት አለ?

- ዛሬ ለአንተስ የጠላት ሽንገላ ማባበልና ማታለል ከምን አቅጣጫ ነው የሚመጣው ?

- ቁርጥ ውሳኔም ሆነ የእንቢታ እርምጃ ልትወስድባቸው የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ካለ ምንም ጊዜ ሳታጠፋ  ለጸሎትና ለምክር እንዲመች ለህብረቱ ማካፈል ትችላለህ?

5. ከዚህ ዓይነቱ እርምጃ በኃላ በም35፡ 1 እግዜብሔር ያዕቆብን ወደ ቤቴል እንዲወጣ በዚይም መሰዊያን እንዲሰራ ያዘዋል።

- እርሱም ሆነ ልጆቹ ራሳቸውን ለእግዜብሔር ሃሳብ የመለየታቸውን ሂደት እንዴት ባለ ሁኔታ ነው ቀጥለው ይምንመለከተው ከቁ.2-10 ተመልከቱ

- የጽድቅን እምጃ ስትራመድ እግዜብሔር በሰዎች ፊት ሞገስ እንደሚሆንህ ምን ተማርክ? ቁ.5

### *መደምደሚያ*

ንቁ ጠላታችሁ ዲቢሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚገሳ አንበሳ ወዲያና ወዲህ እንደሚዞር አንበሳ እንደሆነ የእግዜብሔር ቃል ያሳስበናል (1ጴጥ 5፡8) ጠላት ወዳጅ በመምሰል የሚጠቅመን የሚመስል ሃሳብን እያቀረበ ህይወታችንን በወጥመዱ ጠላልፎና ተብትቦ በመያዝ የራሱ ሊያደርግ እንደሚተጋ አስተውለን ምንም እንኮን የምንኖረው በዚህ ዓለም ቢሆንም ነገር ግን የምንዋጋው በዚህ ዓለም ስልት አይደለም ስለዚህ ውጊያችንም ቢሆን ስጋዊ አይደለምና በሚያባብልና ቃልና በወዳጅነት ተሰውሮ የሚመጣውን የጠላትን በመቃወም ምሽግንም ለማፍረስ ብርቱ የሆነውን የጦር ዕቃ በማንሳት እግዜብሔር ከሰጠን ህይወትና በረከት ሊያጎድለንም ሆነ ሊያስጥለን የሚመጣውን የጠላትን ሃሳብ እንቢ ማለት ያስፈልገናል።

## ጥናት አርባ ሁለት

## እግዚአብሔርን የሚፈልግ ሕይወት

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 35 - 36

*መግቢያ፦* ሁልጊዜ የሚጠማና እግዚአብሔርን የሚፈልግ ሕይወት ካለን በሕይወታችን ዘመን ምንም እንኳን የተለያዩ ነገሮች ቢገጥሙን ወይም ቢደርሱብን እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ካለን ችግሮቻችንን በቀላሉ ልናልፋቸው እንችላለን። እግዚአብሔርም ደግሞ ይረዳናል በእርግጥም በኤርሚያስ 29፡11 ላይ እንደሚናገረው እግዚአብሔርን ከልባችን ካሻነው ለእኛ ይገኝልናል።

*ዓላማ፦* በሕይወት ዘመናችን ወደ ኋላ ከሚጎትቱን ነገሮች ተላቀን እግዚአብሔር ወደ አሰበልን ለመድረስ ልባችን እግዚአብሔርን የሚፈልግ እንዲሆን፡

*የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በቁ.1 ላይ እግዚአብሔር ያዕቆብን ውጣ ሲለው እንመለከታለን።
   - እግዚአብሔር ያዕቆብ እንዲሄድ የፈለገበት ቦታ የትነው?
   - እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ተነስተህ ውጣ ብሎ ይናገራል?
   - እግዚአብሔርስ ውጣ እንዳለው ያዕቆብ በምን አወቀ ትላለህ?

2. ከቁ.2-4 እንግዶችን አማልክት ከመካከላችሁ አስወግዱ ይላልና።

   - እንግዶችን አማልክት ሲል በአሁኑ ዘመን ምን ማለቱ ይመስልሃል?

   - ልብስ ለዉጡ ንጹሐን ሁኑ ሲል ከገዞአችን ጋር ምን ያገናኘዋል?

   - ያዕቆብ ቤተሰቦቹ እንዲጸዱ አድርጓል ይህ ከአንተ ጋር በምን ይገናኛል?

3. ቁ.5 የእግዚአብሔር ፍርሃት በዙሪያቸው ባሉት ሁሉ ላይ ወደቀ ሲል ምን ማለቱ ነው?

   - ዛሬስ እግዚአብሔር ጠላቶችህን እንዳስፈራራ በምን ታውቃለህ?

   - የእግዚአብሔር ጥበቃ ከአንተ ጋር መሆኑን በምን ታውቃለህ?

4. ያዕቆብና ቤተሰቦቹ ወደ ከነዓን እንዲደረሱ ይናገራል

   - ያዕቆብ እዚያ ስፍራ መሰዊያ መስራቱ ስለ ያዕቆብ ምን ይናገራል?

5. ከቁ. 9-10 እግዚአብሔር ለያዕቆብ ከሁለት ወንዞች መካከል ከሶሪያ እንደተመለሰ በኋላ እንደገና እንደተገለጠለት እና እንደባረከው እናነባለን።

   - እግዚአብሔር ለያዕቆብ ለምን መገለጥ አስፈለገው?

   - ያዕቆብስ ስም ለምን መለወጥ አስፈለገው?

   - በአንተስ ሕይወት የስም ለውጥ የሚያስፈልግ ይመስልሃል? እግዚአብሔር እንድንለውጥ ሚፈልግብን ነገር ምንድነው?

6. ከቁጥ.11-15 እግዚአብሔር ለያዕቆብ ሌላ የእግዚአብሔር ስም ሲናገር እናነባለን።

- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ በሚል ስም መጠራቱን ያዕቆብ እንዲያውቅ ለምን አስፈለገ?

- የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት በሕይወትህ እንዴት ትረዳዋለህ?

7. ከቁ16-20 ያዕቆብ የሚወዳት ራሔልን እንዳጣ ይናገራል።

- ስለ ማግኘትና ማጣት ምን ትማራለህ?
- የተቀበለውስ ወይም ያገኘውስ ምንድነው?
- ቀጥሎ የምንመለከተው ጥናታችን ካለፈው ጥናት ጋር የተያያዘ ነው፡ ኤሳው ብኩርናውን በትንሽ ነገር በመሸጥ እንዴት እንዳቃለላት በኋላም ደግሞ በዕብ.12፡15-17 ባለው ክፍል እንደሚናገረው ተግቶ እንኳ ቢፈልገው ሊያገኘው አልተቻለውም ።

8. ቁ.36 ቁ.1 ላይ የኤሳው ትውልድ እርሱም ኤዶም ነው ይላል።

- ይህ ኤዶም የሚለው ሐሳብ ከየት የመጣ ይመስልሃል?

- የኤሳው ትውልድ ከወንድሙ ከያዕቆብ የሚለው በምንድነው?

9. ቁ.2 ላይ ዔሳው ከከነአን ልጆች ሚስቶችን አገባ የሚል እናነባለን።

- ይህ የኤሳው ጋብቻ ትክክል ይመስልሃል?

- ዘፍ..26፡34 በማንበብ ስለዚህ ክፍል ተናገር?

10. በቁ.6-8 ኤሳው ከወንድሙ ከያዕቆብ እንደተለየ እናያለን፡

- ኤሳው ከወንድሙ ከያዕቆብ የተለየበት ምክንያት ምንድነው?

- ዘዳ..2፡12 በመመልከት ኤሳው የሄደው ወዴት ነው?

11. ከቁ.15-19 የዔሳው ልጆች አለቆች በማለት ስም ይዘረዝራል፡

- ዘፍ.27፡40 በመመልከት የምትረዳውን ተናገር?

## መደምደሚያ

እግዚአብሔርን የመፈለግ ሕይወት እጅግ ደስ ያሰኛል መጨረሻውም ያማረ ነው። ስለዚህ የሁል ጊዜ ሕይወታችን እግዚአብሔርን የመፈለግ ቢሆን እራሳችንንም ሆነ ቤተሰቦቻችንን ማትረፍ እንችላለን።

## ጥናት አርባ ሶስት
## ቅን እና ታዛሽ ሕይወት

**የምንባብ ክፍል ፦** ዘፍ. 37

**መግቢያ፦** ቅንና ታዛዥ መሆን አንዳንድ ጊዜ ምንም እንደማያውቅ ያስመስላል፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ሁል ጊዜ እርስ በእርሳችን ቅኖችና ሩህሩሆች እንድንሆንና ከክፋት ወይም ከቅናት እንድንርቅ ይመክረናል። ከዚህም በላይ ቅን መሆን ለጊዜው የሚጎዳ ይመስላል። ፍጻሜውን ገና ላላየ ሰው ቅንነት እጅግ የሚጎዳ የሚመስልበት ጊዜ አለ። ሆኖም ግን ቢሳካልንም ባይሳካልንም፣ ለጊዜው ጥቅሙ ቢታየንም ባይታየንም ግን ቅኖች እና አለነውር የምንኖር እንድንሆን ጌታ ከእኛ ይፈልጋል። በዛሬው ጥናታችን ዮሴፍ ምንም እንኳን ለጊዜው ቢጎዳበትም በእግዚአብሔር ፊት ግን በቅንነት እና በንጽሕና እንዴት እንደተመላለሰ እንመለከታለን።

**ዓላማ፦** በሕይወት ዘመናችን ወደ ኋላ ከሚጎቱቱን ነገሮች ተላቀን እግዚአብሔር ወደ አሰበልን ለመድረስ ልባችን እግዚአብሔርን የሚፈልግ እንዲሆን፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ዮሴፍ የአስራ ሰባት ዓመት በሆነ ጊዜ ከወንድሞቹ ጋር በጎችን እንደሚጠብቅ ይናገራል
   - ይህ ክፍል ስለ ዮሴፍ ምን ይነግረናል?
   - መታዘዝ ከመስዋዕት እንደሚበልጥ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል አንተስ የመታዘዝ ሕይወት አለህ?
2. ቁ.3 እስራኤል ዮሴፍን ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ይወደው ነበር ይላል።
   - እስራኤል ዮሴፍን ከልጆቹ ይልቅ የወደደበት ምክንያት ምን ይመስልሃል
   - ለያይቶ መውደድ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ትክክል ነው?
   - በዚህስ ምክንያት የተፈጠረው ችግር ምንድነው?
3. ቁ.5 ላይ ዮሴፍ ለወንድሞቹ ሕልሙን መናገሩ ትክክል ነው ትላለህ?
   - ማድረግ የነበረበትስ ምንድነው?
   - አንተስ የህልሙ ባለቤት ብትሆን ምን ታደርግ ነበር?
4. ከቁ.9-11 ዮሴፍ ሌላ ሕልም እንዳለመ ይናገራል።
   - ወንድሞቹ ለዚህ ሕልም የሰጡት ምላሽ ምንድነው?
   - አንተስ ሰዎች ያንተን ሕልም ባይቀበሉ ምን ታደርጋለህ?
   - ወንድሞቹስ ለዮሴፍ ያላቸው አመለካከት እስከምን ሄደ?
   - ወንድሞቹ ለምን የፈሩ ይመስልሃል?

5. ቁ. 11 ወንድሞቹ ቀኑበት ይላል?

    - ቅናት ምንድነው?

    - አንተስ ወንድሞችህ እንደቀኑብህ ብታውቅ ምን ትላለህ?

6. ከቁ. 14-24 ወንድሞቹ በዮሴፍ ላይ ያደረጉት ምንድነው?

    - በመልካም ፊንታ ክፉ ማድረጋቸው ከምን የተነሳ ነው?

    - አንተስ ሰዎች በመልካም ፈንታ ክፉ ቢያደርጉብህ ምላሽህ ምንድነው?

    - ቅናት እስከምን እንደሚያደርስ ትመለከታለህ?

7. ከቁ.25-28 ዮሴፍ እንደተሸጠ እናነባለን።

    - ዮሴፍ ከመሞት የተረፈው ማነው ትላለህ?

    - እግዚአብሔር ለቅኖች መልካም እንዲሆን እንዴት ትገነዘባለህ?

8. ከቁ.29-36 የዮሴፍ ወንድሞች ያደረጉት ምንድነው?

    - በአባታቸው ሕይወት የፈጠሩት ችግር ምንድነው?

    - እንዲህ ዓይነት ስነምግባር በአሁን ጊዜ ያለ ይመስልሃል?

9. እስካሁን ባለው ብቻ በመመልከት ቅን መሆኑ ለዮሴፍ ጠቅሞታል ብለህ ታስባለህ?

## መደምደሚያ

ለክርስቲያን ቅን መሆን ከጌታ የተሰጠው ትዕዛዝ እንጂ ሰው በፈቃዱ የሚመርጠው ምርጫ ብቻ አይደለም። ይህንን የጌታ ትእዛዝ እየፈጸሙ ሰዎች ሲኖሩ ለጊዜው ሊጎዱበትም ሆነ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። በምናልፍበት መንገድ ውስጥ ቢሰራልንም ሆነ ባይሰራልን፣ እንድ ጌታ ቃል ታዛሽ ቅን እና መልካም መሆን ግን ግዴታችን ነው። የእግዚአብሔርን ቃል  የምናደርገው እና የምንኖረው፣ ነገ ያተርፍልኛል ብለን ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል መኖር በራሱ ትርፋችን ነው ብለን ነው።

## ጥናት አርባ አራት
## እንዳይፈረድብህ አትፍረድ

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 38

**መግቢያ፦** አንዱ ሰው በሌላው ሰው ላይ መፍረዱ የተለመደ ነገር ነው። የሚገርመው ነገር ግን እፈርዳለሁ ብሎ የሚነሳውም ሰው ደካማ እና እሱም ራሱ ሊያስፈርድንት ከሚችል ጥፋት ነጻ የሆነ አለመሆኑ ነው። ነገሩ ልክ ዘማዊቷን ሴት እንድትወገር ጌታ ፊት ያመጧትን ሰወች አይነት ነገር ነው። እነሱ ኃጢአተኛ ሆነው ሳሉ የሌላውን ሰው ኃጢአት ለመቁጠር አንደኛ ነበሩ። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ እንዳንፈርድ የእግዚአብሔር ቃል ያዛል። እውር ዲዳውን እንዲፈርድበት አይገባም እሱም ችግር አለበትና። ስለዚህም መፍረድ ተገቢ ነገር አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ "አትፈረዱ" ሲል ያዛልና።

**ዓላማ፦** አንዳችን በሌላችን እየፈረድን ከመኖር ይልቅ፣ እየተደጋገፍን እና እየተሳሰብን እንድንኖር ማሳሰብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቁ 1- 5 ባለው መሰረት ይሁዳ ያገባው ማንን ነው? ከእሷስ የወለደው ስንት ልጆች ነው?

2. ይሁዳ በራሱ ፈቃድ ከወንድሞቹ (የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሆኑት ከያዕቆብ ልጆች) ተለይቶ ከነዓናዊት ሴት ማግባቱ ትክክል ነው ትላለህ? (ዘፍ 24፡3-4 እንዲሁም ዘፍ 28፡1-2 ባለው ክፍል የአብርሃም እና የይስሐቅን ፍራቻ አስተውል)።

3. በቁ 6 ላይ ይሁዳ የመጀመሪያ ልጁን ለትዕማር አንዳጋባት እንመለከታለን።

   - ይሁዳ ልጁን ለትዕማር ካጋባ በኋላ በልጆቹ እና በትዕማር መካከል የተፈጠረው ችግር ምንድን ነው? (6-10 ያለውን ይመልከቱ)
   - በቁ 7 እና 9 መሰረት ለሁለቱ የይሁዳ ልጆች መሞት ምክኒያት የሆነው ነገር ምንድን ነው?
   - በዚህ መሰረት ትዕማር ለልጆቹ መሞት ምክኒያት እንዲሆን ያደረገችው ክፉ ነገር አለ ወይ?
   - በይሁዳ አስተሳሰብ መሰረት ለሁለቱ ልጆቹ መሞት ምክኒያት የሆነው ምንድን ነው (ፍንጭ የሚሰጥ ከሆነ ቁ 11ን ተመልከት)።

4. በቁ 11 መሰረት ይሁዳ ሦስተኛ ልጁን ለትዕማር ላለማጋባት በመወሰኑ ትዕማርን በድሏታል ብለህ ታስባለህ?

5. ከቁ. 12-23 ባለው መስረት፣ የሚገባትን መብት ይሁዳ ስለነፈጋት ትዕማር የወሰደችው እርምጃ ምንድን ነው?

   - ምንም እንኳን ይሁዳ ትዕማርን ቢበድላት ለተበደለችው በደል የመለሰችው አጸፋ ትክክል ነው ብለህ ታስባለህ?

   - በቁ 24 መሰረት ትዕማር ያቀደችው ተንኮል ያስከተለው ምንድን ነው?

6. በቁ 25 መስረት ይሁዳ ትዕማር እንደጸነሰች ሲሰማ በእሳት እንድትቃጠል ሲያዝ እንመለከታለን።

   - ይህ ታሪክ በዮሐ 8፡ 1-11 ካለው ታሪክ ጋር በምን ይመሳሰላል?

7. ራሱ ኃጢአተኛ ሆኖ ሳለ ይሁዳ በትዕማር ላይ ሲፈርድ አይተናል። ይሁዳ በድብቅ የሰራውን ኃጢአት ለማያውቅ ሰው የይሁዳን ፍርድ ሲሰማ የሚስማማ ይመስልሃል?

8. ዛሬ በዚህ ዘመን ላለን ሰዎች በሌላው ጥፋተኝነት ላይ ወይንም ደግሞ ድካም ገብተን መፍረድ የሌለብን ለምንድን ነው?

## መደምደሚያ

ሁላችንም ኃጢአተኞች እና ደካማ ፍጡር ነን! ስለዚህ ልክ እንደማያጠፋ ሰው ማንም በሌላው ላይ ሊፈርድ አይገባም። እንዲያውም የሌላውን ኃጢአት እና ጥፋት ከመቁጠር እና ከመፍረድ ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ "በወንድምህ አይን ያለውን ጉድፍ ለምን ታያለህ፣ በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ አትመለከትምን? ወይም ወንድምህን ፦ ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆም በዓይንህ ምሰሶ አለ። አንተ ግብዝ ፣ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ፣ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ (ማቴ 7፡3-5)። በማለት በመጀመሪያ ራሳችንን እንድናይ ይመክረናል። ስለዚህ አንፈረድ ነገር ግን የራሳችንን ድካም እየቆጠርን ራሳችንን ለማረም ብሎም ሌላውን ለመርዳት እንነሳሳ።

## ጥናት አርባ አምስት
## ሁኔታዎች ሲለወጡ በጌታ ያለህ ሕይወት አይለወጥ!

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 39፡1-23

መግቢያ፦ በሰው ሕይወት ውስጥ ለውጥ ያለ ነው። አንዳንዱ ለውጥ መልካም ቢሆንም አንዳንዱ ግን የሚያስቆጭ ነው። በክርስትና ውስጥም ሰዎች በጌታ ያላቸው ሕይወት ሲለዋወጥ፣ አንዳንዱ ሲበረታ ሌላው ግን ሲደክም ማየት የተለመደ ነገር ነው። ክርስቲያን በነገሮች መለዋወጥ ለሁኔታዎች የሚሰጡት ምላሽ ሊለዋወጥ ቢችልም፣ በጌታ ያላቸው ሕይወት እና ጽናት ግን ከቶ ሊለወጥ አይገባም። የክርስትና ሕይወት እንደ አየር ሁኔታ የሚለዋወጥ ነገር ሳይሆን በከፍታም ቢሆን በዝቅታ ክርስቲያኖች በትጋት ሊኖሩት የሚገባ ሕይወት ነው። በዛሬው ጥናታችን የዮሴፍን ሕይወት በመደገፍ የእግዚአብሔር ሰው እንዴት በሚለዋወጡ ነገሮች ውስጥ የእግዝዚአብሔር ሰውነቱ ሳይለወጥ እንዴት መኖር እንዳለበት እንመለከታለን።

ዓላማ፦ በየዕለቱ በሚገጥሙን መልካም እና ክፉ ገጠመኞች ሳንለወጥ ለጌታ መኖር እንዳለብን ማሳሰብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ.1 ዮሴፍ በግፍ ወደ ግብጽ ተውስዶ እንደ ዕቃ ሲሸጥ እንመለከታለን፡ በዚህ በዮሴፍ ላይ እየደረሰበት ባለው ነገር ውስጥ የእግዚአብሔር ሃሳብ ይኖራል ብሎ ማሰብ ይቻላል?

2. በቁ.2-8 ባለው ክፍል እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር መሆኑን የሚያመለክቱትን ነጥቦች ምድን ለይተህ በማውጣት ተነጋገሩባቸው?

   - የምታልፍበት ሁኔታ የእግዚአብሔር ይኖርበታል ብለህ የማትገምተው ቢሆንም ከዚህ ክፍል ታሪክ የምትማረው እውነታ ምድነው

3. የጌታው ሚስትም አይኖን ጣለችበት የሚለው አባባል የሚመለክትን ዮሴፍ መልከ መልካም ስለነበረ ብቻ ነው ትላለህ?

4. ቁ.9-18 የጌታው ሚስት ዮሴፍን ቢቻል በፈተና ካልሆነም በወጥመዶ ለመጣል ያደረገችውን ተመልክተናል።

   - ዮሴፍን በዚህ በከፋና በፈጠጠ ፈተና ውስጥ በጽናት እንዲቆም ያደረገው ምድን ነው ትላለህ?

   - ዮሴፍ የገጠመውን ጉዳይ ለማስተናገድ ሊሰጠው የሚችለው ምክንያት ይኖረዋል ትላለህ?

   - አንተስ ከሰይጣን የሚቀርብልህን ፈተና ለማስተናገድ የምታቀርባቸው ምክኒያቶች ከዮሴፍ ጋር ሲነጻጻር ምድነው ትላለህ?

5. ቁ.19 አሁን ደግሞ ዮሴፍ ለሁለተኛ ጊዜ ከተደላደለና ከሞቀ ህይወት ውስጥ ወደ አዘቅት ሲጣል እንመለከታለን።

   - ቁ.20- 23 ባለው ክፍል እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር መሆኑን የምናውቅበት ምልክቱ ምድነው?

   - ቸርነቱን አበዛለት ሞገስንም ሰጠው የሚለውን እንዴት ትረዳዋለህ?

- አንተስ በከፋና በመረረ ጉዳይ ውስጥ ነው እያለፍክ ብትሆንም እግዚአብሔር ግን ሁኔታው ሳይቀየር አንተን መቀየር እንደሚችል ምን እውነት ከዚህ ክፍል ጨብጠሃል?

## መደምደሚያ

በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ በህይወታችን ውስጥ የሚከሰቱና የሚሆኑትን ስንመለከት ከምገምተውና ከምጠብቀው ውጭ ስለሚሆንበን አንዳዴ እግዚአብሔር የተጣላን የተውን የሚመስለን ሰዓት ብዙ ነው፡ ነገር ግን የቱንም ያኽል ነገሮቻችን የጨላለሙ የተዘጋጉ ቢመስሉም እንኳን የማይለወጠው የታመነው ጌታ ከእኛ ጋር እንዳለ በማስተዋል በምናልፍባቸው ጎዳናዎች ሁሉ በፊታችንን ያለውን ጌታ እያሰብን በነገር ሁሉ ታጋሾችና ታማኞች በመሆን መመላለስ ይገባናል። በእርግጥም ደግሞ ለሚታገሱት እግዚአብሔር መልስ አለው።

ጥናት አርባ ስድስት

## እግዚአብሔር በሚሰጠን ጸጋ ሌሎችን ማገልገል

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 40

**መግቢያ፦** እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናል፤ ስለዚህም እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበትመጽናናት በመከራ ያሉትን ማጽናናት (ማገልገል) እንችላለን ብሎ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራልና እኛ ያለንበትን ሁኔታ ማሰብ ትተን ሌሎች ያሉበትን ሁኔታ በመረዳት ሌሎችን ለመጥቀም ስንተጋ እግዚአብሔር ደግሞ ለእኛ ይተጋል።

**ዓላማ፦** በምንም ሁኔታ ውስጥ ብናልፍ ከራሳችን አልፈን ሌሎችን ሰዎች ማገልገል እንደምንችል መገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. የጠጅ አስላፊና የእንጀራ አበዛዎቹ ፈርኦንን በድለው ዮሴፍ ወደ ነበረበት እስር ቤት እንደወረዱ ይነግረናል

    - ለምን ይመስልሃል (ሰዎቹ እስር ቤት የገቡት ንጉሱን ስለበደሉት ብቻ ነው ወይንስ በጉዳዩ የእግዚአብሔር እጅ አለበት ብለህ ታስባለህ?)

2. ቁ.4 የዘበኞቹም አለቃ ለዮሴፍ አሳልፎ ሰጣቸው እርሱም ያገለግላቸው ነበር ይላልና

    - የዘበኞቹ አለቃ ለዮሴፍ አሳልፎ ሰጣቸው ሲል ምን ማለቱ ነው?

    - ዮሴፍ እራሱ በዚህ ቦታ ምንድነው?

    - እርሱም ያገለግላቸው ነበር ሲል ምን ማለቱ ነው?

3. ከቁ. 5-8 ዮሴፍ ከእርሱ ጋር በግዞት ቤት የነበሩትን ስለምን አዝናችኋል ብሎ ጥያቄ ጠየቃቸው

    - ዮሴፍ ስለ እነዚህ እስረኞች ለምን ያስባል ትላለህ?

    - ሰዎቹስ በምን ሁኔታ ውስጥ ነበሩ?

    - ያገኙት መፍትሔ ምንድነው?

    - የነበሩበትን ሁኔታ/ሕልማቸውን እንዲያውቁ የቻሉት ከማን የተነሳ ነው? ዮሴፍስ ከየት እንዴት መተርጎም ቻለ?

4. ከቁ. 9-13 ዮሴፍ ሕልምን ሲተረጉም እናያለን

    - በራስህ አባባል ሰዎቹ መፍትሔ ያገኙ ይመስልሃል?

    - ዮሴፍስ በምን ሁኔታ ያለ ይመስልሃል?

    - እውነተኛ ምህረት ከየት ነው ብለህ ታስባለህ?

    - ሁኔታዎች ቢከብዱብህ ዓይንህን ወዴት ታነሳለህ?

5. ቁ. 23 የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ ግን ዮሴፍን አላስበውም ረሳው እንጂ ይላልን

- ይህ አባባል በዮሴር ውስጥ ቢያሳድር የሚችለውን ተናገር?

- አንተ ለሌሎች እያስብክና እያገለገልህ ብትረሳ ምን የምታስብ ይመስልሃል?

- ይህስ ስለ አገልግሎት ምን ያስተምረሃል?

## መደምደሚያ

አገልግሎት የምንሰጠው ጌታን ስለምንወድ እና ስለጌታ ብለን እንጂ ዛሬ ከምናልፍበት የማይመች ሁኔታ ለመውጣት አይደለም። ቢመችም ባይመችም፣ ሰው ቢያስታውሰንም ባያስታውሰንም፣ አገልግሎታችንን ሰዎች ቢቆጥሩትም ባይቆጥሩትም፣ እንድናገለግልው የሚፈልገው ጌታ በሁሉ ሁኔታ ውስጥ በታማኝነት ስናገለግለው፣ እሱ በጊዜው ያስበናል። ስለዚህም በሁሉ ሁኔታ ውስጥ ዛሬ ከምናልፍበት ሁሉ አልፈን ሌላውን በማገልገል፣ ጌታን ደስ እናሰኝ።

ጥናት አርባ ሰባት

## ለሌሎች የመዳን ምክኒያት መሆን

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 41

*መግቢያ፦* ልንኖርበት እና ልናልፍበት በማንፈልገው ሁኔታ ውስጥ ስንገኝ፣ እግዚአብሔር የተወን እና ብቻችንን የቀረን የሚመስለን ጊዜ ብዙ ነው። ሆኖም ግን የማይተውን አምላክ፣ ብቻችንን የሆንን እንኳን ሲመስለን አብሮን አለ። በማይመችን ሁኔታ ውስጥ እንኳን ስንሆን በዚያ ሁኔታ ውስጥ አብሮን ከመሆን ሌላ ሁኔታችንን ለውጦ ለብዙዎች የመዳንና የመጽናናት ምክኒያት ሊያደርገን እግዚአብሔር ይችላል። ስለዚህም ምንም እንኳን ባይመቸን እንዲሁም በማናውቀው ነገር ምክንያት መከራን ብንቀበል በእግዚአብሔር ሐሳብና ዕቅድ ውስጥ እስካለን እና ቃሉን እየተከተልን የምንኖር እስከሆንን ድረስ በአካባቢያችን ለሚኖረውና ለሚፈጠረው ችግር እግዚአብሔር የመፍትሔ ምክንያት ሊያደርገን ይችላል።

*ዓላማ፦* በሚመችም ይሁን በሚያስለቅሰው የዛሬው ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር በእኛ ሊሰራው የሚፈልገው ቁም ነገር እንዳለ እንድናታውስ መርዳት።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከም1-8 ባለው ክፍል ንጉሱ ለሕልሙ ትርጉም ማግኘት እንዳልተቻለው ይናገራል።
    - ሕልም የሚመጣው ከየት ነው? ወይም ሕልም ምንድነው?
    - ሕልም ሁሉ ትክክል ነው ብለህ ታምናለህ?
    - የግብጽ ጠቢባን ሕልሙን መፍታት ለምን አቃታቸው?
2. ከቁ.9-13 “ እኔ ኃጢአቴን ዛሬ አስባለው” ብሎ ይናገራልና
    - ይህ ክፍል ስለ ምን የሚናገር ይመስልሃል? ስለ እርሱ ወይስ ስለሌላ ሰው?
    - ለምን ይህ ሰውስ ከረጅም ጊዜ በኋላ ኃጢአቱ ትዝ ሊለው ቻለ?
    - አንተስ ሰው አደራ ያለህን ነገር ትዘነጋለህ?
    - ስለ ሰውስ ምን ያህል ግድ የሚልህ ይመስልሃል?
3. ቁ. 14 ፈርኦን አስጠራው ይላልና
    - ይህ ክፍል ምን እንድታስብ ያደርግሃል?
    - ዮሴፍ በእውነት የታሰበው በማን ነው?
    - ዮሴፍስ ከእስር ቤት እንዲወጣ ያደረገው ምክንያት ምንድነው?
4. ከቁ.15-24 የለውን በማንበብ የሆነውን ተናገር
    - ለህልም ተርጓሚዎችም ሕልሜን ነገርሁ የሚተረጉምልኝም አጣሁ?
    - ሕልም የሚሰጥ ማነው ትላለህ?
    - ሕልምስ መተርጎም የሚችል ማነው?

- ሁሉ ሰው ሕልም መተርጎም ይችላል ትላለህ?

5. ከቁ.25-40 ለነበረው ችግር መፍትሔ እንደተገኘ ይናገራል

   - በራስህ አገላለጽ መፍትሔውን የሰጠው ማነው ትላለህ?
   - በአንተስ ሕይወት ጌታ ተጠቅሞ ይሰራል ብለህ ታምናለህ?
   - ሕልም መፍታት ለሌሎች ከብዶ ለዮሴፍ የተቻለበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
   - ዛሬስ ለሌሎች ያልተቻለው ለእኔ ይቻላል ትላለህ?

6. 40-47 እግዚአብሔር ዮሴፍን ተጠቅሞ ግብጽን እንዳተረፋቸው እናያለን

   - ዮሴፍ በእግዚአብሔር ፈቃድ ባይሄድ ይህ የሚሆን ይመስልሃል?
   - አንተስ ይህንን በመገንዘብ ለሕይወትህ ምን ያህል ትጠነቀቃለህ?

7. ቁ. 47 አገሮችም ሁሉ እህል ይገዙ ዘንድ ይላልና

   - በዚህ ክፍል መሰረት ራብ ይት ነበር ትላለህ?
   - እግዚአብሔር በእኔም ተጠቅሞ ሰውንም አገርንም ያድናል ካልክ ምን ማድረግ እንዳለብህ ተናገር?

## መደምደሚያ

“እግዚአብሔር ሳይደግስ አይጣላም” እንደሚባለው የአገራችን አባባል፣ እግዚአብሔር በእኛ የዛሬው ሁኔታችን ውስጥ የሚሰራውን ቁም ነገር ሳያስብ እንዲሁ አለምክኒያት ለግፍ እና ለመከራ አይሰጠንም። ስለዚህም ዛሬ ያለንበትን ስናስብ፣ እግዚአብሔር ሊሰራ ያቀደውን መልካም ስራ ለመፈጸም የሚጠቀምበት እንደሆነ በማሰብ በሁሉ ሁኔታ ውስጥ ደስ ልንሰኝ እና ልንጽናና ይገባናል።

## ጥናት አርባ ስምንት
## እግዚአብሔር ያቀደው ከመሳካት ፈጽሞ አይቀርም!

**የምንባብ ክፍል፦** ዘፍ. 42

**መግቢያ፦** እግዚአብሔር ይሆናል ያለው ነገር ሁሉ ከመፈጸም ከቶ አይቀርም። ስለዚህም እሱ ያለውን እና ያቀደውን በሚቃረን መልኩ ምንም ነገር ማድረግ ትርፉ ድካም እና ጉዳት ነው። እግዚአብሔር ስለ ያዕቆብ ሲናገር ታላቁ ለታናሹ ይገዛል ሲል ቃል ገብቶ ነበር፣ ነገር ግን ያዕቆብ በላባ ቤት በነበረ ጊዜ ያ የተስፋ ቃል ይፈጸማል ብሎ ማሰብ ዘበት ይመስል ነበር። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ብሏል እና ጊዜውን ጠብቆ ሁሉም ተፈጽሟል። በዮሴፍም ሕይወት የሆነው ነገር ይህንኑ እውነት የሚያጠናክርልን ነገር ነው። እግዚአብሔር ለዮሴፍ በሕልም ቃል ገባ፣ ያ ተስፋ ግን ምንም የቆየ ቢመስል ጊዜውን ጠብቆ ተፈጽሟል። በዛሬው ጥናታችን የእግዚአብሔር ቃል እና አላማ ምንም ብዙ ተቃውሞ ቢገጥመው ግን መሳካቱ እና መፈጸሙ እንደማይቀር እንመለከታለን።

**ዓላማ፦** ለጊዜው ባይመስልም፣ እግዚአብሔር ድንቅ በሆነ አሰራሩ ቃሉን እና እቅዱን እንደሚፈጽመው መረዳት።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በም 42፡1-9 ባለው፣ የዮሴፍ ወንድሞች እህል ለመሸመት ወደ ግብጽ እንደወረዱ፣ እንዲሁም ዮሴፍ ባያቸው ጊዜ እንዳወቃቸው እና ድሮ ያየውን ሕልም እንዳስታወሰ ይነግረናል።

    - በዚህ መሰረት ዮሴፍ ያስታወሰው ሕልም ምን ነበር? (ምዕራፍ 37፡5-11 ተመልከቱ)

    - የዮሴፍ ወንድሞች ስለ ሕልሙ በሰሙ ጊዜ የተሰማቸው ነገር ምን ነበር? (37፡8)

    - በዘፍ 37፡18-20 ባለው ወንድሞቹ ሊገድሉት እና ሊሸጡት ያሰቡበት ዋነኛው ምክኒያት ምንድን ነው?

    - በዘፍ 42፡9 ላይ ዮሴፍ ይህንን ሕልም እንዲያስታውስ ያደረገው ነገር ምንድን ነው?

2. ዮሴፍ ከተሸጠ በኃላ ያልፍበት በነበረው ከባድ የሕይወት ጎዳና ላይ ሆኖ ሳለ ያየው ሕልም አንድ ቀን ይፈጸማል ብሎ ያስብ ነበር ብለህ ታስባለህ? ለምን?

3. በ42፡1-5 ባለው ክፍል የያዕቆብ ልጆች እህል ሸመታ ወደ ግብጽ እንዲሔዱ ምክኒያት የሆናቸው በጊዜው የመጣው ድርቅ እና ራብ እንደሆነ ዘፍ 41፡ 53-57 ያለው ክፍል ይነግረናል።

    - በዚህ መሰረት፣ ይህ የራብ ዘመን እንዲመጣ ያደረገር እንዲያው የተፈጥሮ ነገር ነው ወይስ እግዚአብሔር ነው? (ዘፍ 41፡25፣28፣እንዲሁም 32 ተመልከቱ)።

    - ይህ የራብ ዘመን እንዲመጣ እግዚአብሔር ለምን የፈቀደ ይመስልሃል?

    - የዚህ የራብ ዘመን እና የዮሴፍን ሕልም የሚያገናኛቸው ነገር ምንድን ነው?

4. በዘፍ 42፡8 ላይ ዮሴፍ ወንድሞቹን ባያቸው ጊዜ እነማን እንደሆኑ ቢያውቅም ወንድሞቹ ግን አላወቁትም።

- የሴፍን ለማወቅ እንዳይችሉ ምክኒያት ሊሆኑ የሚችሉ ምን ምን ነገሮችን ማውጣት ትችላለህ? (ዘፍ 41፡14 እንዲሁም ዘፍ 42፡23 በመመልከት የአዲሱ መደበኛ ትርጉም ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ አገናዝብ)!

5. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዮሴፍ ከወንድሞቹ ጋር ሲገናኝ እና ከዚያ በኃላ በነበረው ሁኔታ፣ የዮሴፍ ሕልም መፈጸሙን የሚያመለክቱ ምን ምን ነገሮች አሉ? (በተለይም ቁ.6፣ እና 10 ተመልከቱ)።

6. በቁ. 11 እና 31 ከአንድም ሁለት ጊዜ የዮሴፍ ወንድሞች "እውነተኞች ነን!" ሲሉ ተናግረዋል።

   - ይህ ምን ያህል እውነት ነው? የዮሴፍ ወንድሞች ከዚህ በፊትም ሆነ በዚህ ክፍል ውስጥ እንደዋሹ ያስተዋልከው ነገር አለ?

   - የዮሴፍ ወንድሞች በውሸታቸው አባታቸውን እንዳታለሉ በዚህ ክፍል ውስጥ እነሱ ራሳቸው የተታለሉት እንዴት ነው?

   - ይህ ክፍል ማጭበርበር መልሶ ለራስ መታለል እንደሚያመጣ የሚያተምረን እንዴት ነው?

7. የዛሬውን ክፍል በመመልከት እግዚአብሔር ለዮሴፍ በሕልም የተናገረውን እንዲፈጸም አድርጓል ትላለህ? እንዴት?

   - በሰው አይን የማይመስለውን ሁኔታ ለዋውጦ ያቀደውን ነገር እግዚአብሔር እንደሚፈጽም ይሔ ክፍል የሚያስተምረን እንዴት ነው?

8. ዛሬ ከዚህ ክፍል ለኛ የምንማረው ነገር ምንድን ነው?

*መደምደሚያ*

እግዚአብሔርን ታማኝ አምላክ ከሚያሰኙት ባህሪያት አንዱ ያለውን መፈጸሙ ነው። ሰው ደካማ በመሆኑ እንዲሁም ሁሉን ማድረግ የሚችል ጉልበት ስለሌለው፣ ከአቅም በላይ የሆኑ ነገሮች ገጥመውት ያለውን ለመፈጸም ያቅተዋል። ስለዚህም በሰው መታመን አይቻልም። እግዚአብሔር ግን ብንታመነው ይታመናል፣ ከተናገረ ይፈጽማል፣ ካቀደ ያደርገዋል።

## ጥናት አርባ ዘጠኝ
## በስጋት አትመላለስ!!

የምንባብ ክፍል፦ ዘፍ. 43

**መግቢያ፦** ብዙ ሰዎች በፍርሃት እና በስጋት ተሞልተው የሚመላለሱ መሆናቸው ግልጽ ነው። አንዳንዱ ከዚህ በፊት የሰራውን ክፉ ልቡ ስለሚያውቅ ከዛሬ ነገ ተያዝኩ እያለ ሲሰጋ፣ ሌላው ገና ለገና ክፉ ይመጣብኛል ብሎ ይሰጋል። ሆኖም ግን በሰቀቀን እና በስጋት እንድንኖር አልተጠራንም!! ያጠፋም ስህተቱን አርሞ፣ ያላጠፋውም ሁሉን በሚችል አምላክ ተማምኖ በሰላም እና በደስታ ሊኖር ይገባዋል። በዛሬው ጥናታችን፣ የዮሴፍ ወንድሞች እና አባቱ የነበራቸውን ስጋት የተሞላ ሕይወት በመመልከት በዛሬው ሕይወታችን ያለ ፍርሃት እንዴት መኖር እንዳለብን እንማራን።

**ዓላማ፦** ሕይወታችንን በእግዚአብሄር ፊት አስተካክለን እና በእግዚአብሔር ተማምነን ያለ ስጋት እንድንኖር ማበረታታት።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቁ. 1-3 ያለውን በመደገፍ፣ ያዕቆብን እና ልጆቹን ስጋት ውስጥ ሊጨምራቸው የሚችል ምን ነገር አለ?
   - ከዚህስ ስጋት ለመዳን ያሰቡት መፍትሔ ምንድን ነው?
   - ወደ ግብጽስ ሲወርዱ ስንተኛ ጊዜአቸው ነው?
2. ከቁ 4-5 ባለው መሰረትስ የያዕቆብ ልጆች የነበራቸው ስጋት ምንድን ነው?
   - የያዕቆብ ልጆች ወደ ግብጽ ባደረጉት የመጀመሪያ ጉዞአቸው፣ ዮሰፍ ፊቱን ዳግመኛ አታዩም ያላቸው ለምንድን ነው?
   - ይህ የዮሴፍ ቃል በልባቸው የፈጠረው ስጋት ምንድን ነው?
3. ከቁ. 6-7 ባለው መሰረት የያዕቆብን ንግግር ስትመለከት በያዕቆብ ውስጥ የነበረው ስጋት ምንድን ነበር?
   - በዚሁ ክፍል ውስጥ "ሌላ ወንድም አለን ለምን አላችሁ?" በማለት ያዕቆብ ሲጠይቃቸው እውነትን መናገር እንዳልነበራቸው ለማመልከት ፈልጎ ነው ብለህ ታስባለህ?
   - የዮሴፍ ወንድሞች በጊዜው ለዮሴፍ እውነቱን ባይናገሩ ኖሮ ሊገጥማቸው የሚችለው ነገር ምንድን ነው?
   - ብዙ ጊዜ ሰዎች እውነትን የማይናገሩት ለምንድን ነው?
4. ከቁ 11- 14 ያለውን ስትመለከት፣ ያዕቆብ የዮሴፍን ልብ ለማራራት እንዲሆን ልጆቹ እንዲጠቀሙ ያደረገው ምንድን ነው?
   - ያዕቆብ ይህንን ሃሳብ ማቅረቡ በልቡ ስላለው ስጋት ምን ይነግርሃል?
5. ከቁ 17-18 ባለው የዮሴፍ ወንድሞች ስጋታቸው ምን ነበር?
   - በቁ 23 ላይ የቤቱ አዛዥ "አትፍሩ" ማለቱ ስለ ፍርሃታቸው ምን ይነግርሃል?
6. በቁ 26 ላይ እየፈሩ እና እየደነገጡም ቢሆን ዮሴፍ ባየው ሕልም መሰረት፣ ወንድሞቹ እጅ እየነሱት ሳያውቁት ሕልሙን ሲፈጽሙ ይታያሉ።

- ይህስ የኛ ፍርሃት እና ድንጋጤ እግዚአብሔር ካቀደው ነገር እንደማያስጥለን ምን ያስተምረናል?

7. ከዛሬው ትምህርት ምን ተማርክ?

*መደምደሚያ*

ያዕቆብን እና የዮሴፍን ሕይወት ስንመለከት በእያንዳንዱ የሕይወታቸው እርምጃ ውስጥ ብዙ ፍርሃት እና ድንጋጤ እንዳለ እናያለ። ለዚህ አይነቱ ሕይወት አንደኛው ምክኒያት የፈጸሙት ግፍ ቢሆንም፣ ሌላው ግን የሕይወታችን ስር እና መሰረት እግዚአብሔር መሆኑን መዘንጋት ነው። ስናጠፋ፣ ሕይወታችንን እናርም … ከዛሬ ነገ ችግር መጣብኝ እያልን ስንሰጋ እንዳንኖር! በሌላ በኩል ግን የሕይወት ሁሉ ጌታ እግዚአብሔር ሕይወታችንን እንደያዘ በማወቅ በእርሱ ተማምነን ሁሉን ለሱ ሰጥተን ያለ ስጋት እንኑር።